# ማኅርሚሳቢብ

© ከአሰግድ መኮንን

2004 ዓ.ም
አዲስ አበባ

የመጀመሪያ እትም

2004 ዓ.ም

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

ዋና አከፋፋይ ፍሬው መጽሐፍት መደብር አድራሻ፡-
ቦሌ መድኃኔዓለም ፊት ለፊት ስልክ፡- 0911 54 92 94
አዲስ አበባ

የኮምፒተር ጽሑፍና የገጽ ቅንብር እልፍ ሐብቴ
አድራሻ፡- አዲስ አበባ
ስልክ፡- 0912 16 49 65

"እግዚአብሔር ስምህን ማጕርሚሳቢብ እንጂ ጳሳኮር ብሎ አይጠራህም። እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና እነሆ ለራስህና ለወገኖችህ ሁሉ ፍርሃት አደርግሃለሁ።"

ትንቢተ ኤርምያስ ምእራፍ 20ቁ 3-5

ስጀምር ከፊቴ ነበርክ አሁንም ከፊቴ ነህ!
ወደፊትም ከፊቴ ነህና በአንተ ዘወትር ደስ ይለኛል።
አሜን!

ስለመጽሐፉ ያለዎትን አስተያየት በዚህ ስልክ ደውለው ደራሲውን ማነጋገር ይችላሉ።

0118 60 22 72
አዲስ አበባ

## የደራሲው ቀደምት ሥራዎች

1. ኮብላይ
2. ጥብቅ ምሥጢር
3. ነፀብራቅ

### እና አሁን ያለው ማጉርሚሳቢብ ያልታተሙ ሥራዎች

1. ጥብቅ ምሥጢር ክፍል ሁለት
2. ነፀብራቅ ክፍል ሁለት
3. ስውር ሕሊና
4. ዱር ሱልጣን

"ሞክረን ካልተሳኩት ይልቅ
ገና ያልሞከርናቸው ይቆጩናል"
አጼ ቴዎድሮስ

## *ባሌስትራ*

መኪናዬ ሰብራ ባሌስትራ፤
ልገዛ ሄድኩኝ ሱማሌ ተራ፤
ብጠይቅ ከየመደብሩ እየገባሁ፤
ባሌስትራ አለኝ የሚል አጣሁ።
መቼም አንዳንድ ቀን አይጠፋምና፤
ጠራኝ ጠቀስ አደረገና፤
ምን አጥተው ነው የተቸገሩት፤
ሱማሌ ተራን በሙሉ የሚዞሩት፤
ብሎ ሲጠይቀኝ ለመርዳት።
ባሌስትራ ልገዛ መጥቼ፤
ይኸው እዞራለሁ አጥቼ፤
ብዬ ችግሬን ብነግረው፤
የኮረኮሩትን ያህል አሳቀው።
ካበቃ በኋላ ስቆ ተንከትክቶ፤
በሹክሹክታ ነገረኝ ከጆሮዬ ተጠግቶ።
ሲፈተሽ ዘመኑ ባፈራው ቤተሙከራ፤
ወርቅ ሆኖ ስለተገኘ ባሌስትራ፤
ማዕድን ቢሮ እውቅናን አግኝቷል፤
ስሙ ተቀይሮ ዋጋው እጅግ ንሯል።
የጥራት ደረጃው ተረጋግጦ በሚገባ፤
ባሌስትራ ከዋናው ግምጃ ቤት ስለገባ፤
ይሂዱና እዚያው ከሚገኝበቱ፤
ወርቅ ብለው ባሌስትራን ይሸምቱ።

*ማጉርሚሳቢብን እንብቤዋለሁ የተሰማኝን በማጥም እንድገልጽ ደራሲውን ጠይቄ ስለፈቀደልኝ ይህችን ስንኝ ቋጠርኳት።*

*ጆቢር*

## *ከሕይወት ልምዶች*

የምድር ታላቅ ደስታ . . . መስጠት
ከልምዶች ሁሉ ጉጂ . . . ጭንቀት
የሚያኮራ ሥራ . . . ሌሎችን መርዳት
አስቀያሚ ባህሪ . . . ራስ ወዳድነት
ትልቅ የተፈጥሮ ሀብት . . . ወጣትነት
ትልቅ መሣሪያ . . . ብርታት
ልንፈታው የሚገባን ችግር . . . ፍርሃት
ውጤታማ የእንቅልፍ ኪኒን . . . የአእምሮ ዕረፍት
መጥፎ ፀባይ . . . ይሉኝታ
ቆንጆ ጌጥ . . . ፈገግታ
አደገኛ ስብከት . . . አሉባልታ
ትልቅ ስጦታ . . . ምክር
የሕይወት ኃይለኛ ጉልበት . . . አእምሮ
የሰው ልጅ እንቆቅልሽ . . . ኑሮ
አደገኛ መሣሪያ . . . ምላስ
ራስን የመጉዳት ዘዴ . . . ማልቀስ
በኃይል የተሞላ ቃል . . . እችላለሁ
ታላቅ ተስፋ . . . እኖራለሁ
ውድ ሀብት . . . እምነት
ኃይለኛ የመገናኛ መሣሪያ . . . ፀሎት
መጥፎ የውድቀት በሽታ . . . በስህተት ይቅርታን አለመጠየቅ
መጥፎ ልማድ . . . መስረቅ

ትናንት ታሪክ ነውና ተርከው
ዛሬ ቁም ነገር ነውና ተጠቀምበት

ነገ ምስጢር ነውና ድረስበት
ለመነሳት ከፈለግህ
መውደቅህን አምነህ ተቀበል



# ምእራፍ አንድ

"ይህ ዶቼ ቬሌ የጀርመን ድምጽ ነው።
እንደምን ዋላችሁ አድማጮቻችን።
በቅድሚያ የዓለም እርእሰተ ዜናዎችን እናሰማለን።
ኢትዮጵያ:
"በኢትዮጵያ ውስጥ ከአለፈው ወር ጀምሮ የተለያዩ ሀገራት ዜጎች እየተሰወሩ ነው" ተባለ ኢትዮጵያ በበኩሏ "በሀገሬ ውስጥ የተሰወረ የውጭ ሀገር ዜጋ የለም" ትላለች።

ዜናውን በዝርዝር፣

አንድ የእስራኤል የሕዝብ መገናኛ ብዙኃን በኢትዮጵያ ውስጥ ይኖር የነበረ የእስራኤል ዜጋ በአሳለፍነው ሳምንት ውስጥ በድንገት የደረሰበት መጥፋቱን ገልጿል።

ዘገባው እንደሚለው ከሆነ ግለሰቡ በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ የመንግሥት ዩንቨርስቲ ውስጥ ይማር ነበር ብሏል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ግለሰቡ በሀገሪቱ የቴሌቪዥን ጣቢያ ቀርቦ ከጋዜጠኞች ጋር ቃለ ምልልስ ማድረጉን አስታውሶ በራሱ ፈቃድ ዩንቨርስቲውን ለቅቆ ተሰውሮ ሊሆን ይችላል ሲል የመላምት ግምት ሰጥቷል።

ተማሪው የሚኖርበትን ቤት ከአንዲት አዛውንት በትንሽ ብር የተከራየው ሲሆን የግል ንጽኅናውን ጭምር የማይጠብቅ በመሆኑ ጋዜጠኞቹ ለቃለ መጠይቅ ወደ ጎጆዋ ገብተው በነበረበት ወቅት አፍና አፍንጫቸውን በጨርቅ ሸፍነው እንደ ነበር ምስሉ ያሳያል።

ቤቱን ያከራዩት ሴት ስለግለሰቡ ለጋዜጠኞቹ ሲናገሩ የቤት ኪራዩን በወቅቱ የሚከፍልና ጨዋ ነው ማለታቸውን ምንጮችን ጠቅሷል።

ይህ በእንዲህ እንዳለም የእንግሊዝ እና የአሜሪካን መንግሥታትን ጨምሮ በርካታ የአውሮፓ አገራት በተለይም ቻይና እና ጃፓን ዜጎቻቸው ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ እየተሰወሩ በመሆናቸው የዜጎቻቸውን መሰወር ለኢትዮጵያ መንግሥት እያሳሰቡ መሆኑን ቀደም ሲል በደረሰን ሪፖርት መዘገባችን ይታወሳል። ግብጽና ሳውዲ አረቢያም ተመሳሳይ ስሞታ በቅርቡ አሰምተዋል። ከምንጮቻችን በሚደርሰን ዜና መሠረት የበርካታ አገሯት ዜጎች ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ

> የሚሰወሩበት ምሥጢር እስከ አሁን ድረስ ምክንያቱ ሊታወቅ ያለመቻሉን ምንጮቻችን የጠቀሱልን ሲሆን ይህንን እንቆቅልሽ በርካታ የምዕራብና የደቡብ አፍሪካ ሀገራትም ዜጎቻቸው ወደ ኢትዮጵያ በሚገቡበት ወቅት ማንኛውንም ጥንቃቄ እንዲያደርጉ እየመከሩ መሆናቸው ተጠቁሟል።
>
> ኢትዮጵያ "ውቅያኖስ አልባዋ ቤርሙዳ" ስለሆነች ወደዚያ የሚደረግ ማንኛውም ጉዞ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል ይላሉ። በሌላ በኩልም ከኢንተርፖል የተውጣጣ የደኅንነት ቡድን ለመላክ የውስጥ ስምምነት አድርገዋል የሚል ያልተጣራ ወሬ እየተናፈሰ ነው"።

"ጋዜጠኛው" ቀሪውን በዜና መጽሔት እንደሚያቀርብ ጠቁሞ ወደ ሌሎች ዜናዎች ስለተሸጋገረ የመረጃ መኮንኖቹ እርስ በርሳቸው በጥያቄ ተያዩ።

"ምንድነው?" የመረጃ መኮንኑ ዘሩባቤል አሰምስገድ ተኮሳትሮ ተመለከተው።

"ምኑ?" የደኅንነት ሹሙ። መልሶ ጠየቀው።

"የምንሰማው ዜና" አንገቱን በዝግታ እየነቀነቀ ተመለከተው።

"ምን አዲስ ነገር አለ? የማንኛውም አገር ዜጋ ይሰወራል" ትከሻውን ነጠር አድርጎ መለሰለት ምንተስኖት ኃይለ ልዑል።

"እንደዚህ ያለውን ችግር እኛ ካልተከታተልነው ማን ባለጉዳይ ሆኖ ሊከታተለው ነው? የዚህችን ሀገር ደኅንነት ያስጠብቃል ተብሎ ኃላፊነት የተሰጠው በአላፊነት የምትመራው ተቋም አይደለም እንዴ?" አለ የመረጃ መኮንኑ።

"ሁሉም ነገር በትኩሱ ስትሰማው የትም አገር ተደርጎ የማያውቅ መስሎ ሊሰማህ ይችላል። እየቆየህ ስትሄድ ሁሉንም ነገር ትለምደዋለህ። የራሳችንም ዜጎች በተለያዩ አገራት የውሃ ሽታ እየሆኑ ቀርተዋል" ነገሩን ቀለል ለማድረግ ሞከረ የደኅንነት ሹሙ።

"እሱ ራሱን የቻለ ጉዳይ ነው።" የመረጃ መኮንኑ ኮስተር አለ።

"ምንም ራሱን የቻለ ሌላ ጉዳይ አይደለም" የምጸት ፈገግታ አሳየው ምንተስኖት።

"አገራችን የነበራትን መልካም ስምና ዝና ከማጣቷም በሌሎች አገራት የተለየ ቅርጽና መልክ ተሰጥቷት ለሰው ልጆች በፍራቻና በጥርጣሬ የምትታይ አገር እየሆነች ነው" እሩቅ እያሰበ መለሰለት።

"የፈራና የተጠራጠረ ዜጎቹን በዚያው ሰብስቦ መያዝ ይችላል። በራሳቸው ጊዜ ራሳቸውን ሰውረው ለጠፉ እብዶች የነበረው ዝናዬ ይጠፋል ብላ ኢትዮጵያ ሰማይ ይታሰስ ፍለጋ ትቀጥላለች ብለህ አትጠብቅ።"





"ተሰወሩ የሚባሉት ግለሰቦች ለወሲብና ለሕገ ወጥ ሥራ ገብተው እየጎዱን ያሉ አደገኛ ግለሰቦች ናቸው።"

ትከሻውን ጭምር በኃይል እየናጠ መለሰለት ምንተስኖት።

"የራሳችንም ዜጎች እኮ በተመሳሳይ መንገድ እየተሰወሩ ናቸው። የራሳችን የመረጃ ሠራተኛም እንደተሰወረ ነው ያለው። ይህ ሁሉ ከምን የመጣ ይመስልሃል?" በአግራሞት ተመለከተው ዘሩባቤል።

"በርግጥ በዜጎቻችን በኩል ያነሳኸው ከምንም በላይ ያሳስበናል። ሌላው ጀሃነብ!" እጆቹን አወናጨፈለት።

"አልገባኝም" አለ የመረጃ መኮንኑ። "የምትለው በትክክል አልገባኝም። ስለምንድን ነው ጀሃነቡ?" ደሙ ከውስጥ ወደ ውጭ ገንፍሎ ሲወጣ ታወቀው።

"ቀስ እያለ ይገባሃል" የደኅንነት ሹሙ። ኮስተር ብሎ ተመለከተው።

ከቀኑ አሥራ አንድ ሰዓት ከሩብ ሆነና የዜና መጽሔቱ በጋዜጠኛው መተንተን ጀመረ። የዜና መጽሔቱ ከዜናው ጋር ተመሳሳይ ስለነበር ወደራሳቸው ውይይት ተመለሱ።

"ባልታወቀ ምክንያት እራሳቸውን በራሳቸው እያጠፉ ያሉ ሰዎች አሉ። እንደሚመስለኝ ግለሰቦቹ ከማይወጡበት ማጥ ውስጥ ገብተው ሞትን እንደ አማራጭ ወስደውታል የሚል ግምት አለ። ሌላው ዜጎቻቸው የተሰወሩባቸው መንግሥታት ነገሩን በቀላል እንደማያልፉት አምናለሁ። ይህ ደግሞ ለኛ መስሪያ ቤት ፈተና ነው። በቅርብ ቀንም በዚህ መሥሪያ ቤት ላይ አንድ ዓይነት እርምጃ እንደሚወሰድ ይሰማኛል። በአሜሪካን ባለ ሙያዎች የሰለጠኑ የመረጃ ሠራተኞች ወደ ሀገር እንደተመለሱ በጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ ስር እንዲሠሩ ተደርገዋል። በአሁኑ ሰዓት እየሠሩ ያሉት ከነዚህ ኃያላን ሀገራት የስለላ ሠራተኞች ጋር በጥምር በመሆን ነው። የመረጃና የደኅንነት ባለሙያዎቹ የሚታዘዙት ለአገሪቱ የደኅንነትና የጸጥታ ቢሮ መሆኑ ቀርቶ በጠቅላይ ሚኒስቴሩ ቢሮ ስር እንዲሆን ለምን ተፈለገ? መልሱ በጣም አጭር ነው። የጠቅላይ ሚኒስቴሩ ቢሮ በዚህ መሥርያ ቤት ኃላፊዎች ላይ የነበረው እምነት በተለያየ መንገድ ጥርጣሬ ውስጥ በመግባቱ ነው። የመረጃ ሥራውን በጠቅላይ ሚኒስቴሩ ቢሮ ስር ያደረጉት የአገሪቱን የመረጃና የደኅንነት ቢሮ ወደዚያ በመውሰድ የጠበቀ ምሥጢር ያለው የደኅንነት ተቋም ለመፍጠር ይመስለኛል።"

"በምታስበው መንገድ ባይሆንስ? ምናልባት በጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ ብቻ የሚታዘዝ የምሥጢር ደኅንነት ሊፈጥሩ ይችሉ ይሆናል። አንተ እደምትለው ሁሉንም..." አላስጨረሰውም።

"እኔ ከምለው ውጭ ሊሆን አይችልም።" ሴል ተወራጨ። "በፍጹም። እየተደረገ ያለው አጠቃላይ ለውጥ ነው።"

የደኅንነት ኃላፊው በእልህና በብስጭት ፊቱ እየተቀያየረ ሲመጣ

የመረጃ መኮንኑ አንድ ዓይነት ጥርጣሬ ገባው።

"በሁሉ ነገር ግድየለሽ መስዬ ልታይህ እችላለሁ። ነገር ግን ምክንያት አለኝ። 'አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ' ሆኗል ነገሩ" የመምሪያው ኃላፊ በሚሠራው ስህተት የጥቃቱ ቀስት ወደኛ አነጣጥሯል። ሥራችንን በትክክል እንዳንሠራ ጫናው በርክቶ እንደሚገኝ ታውቃለህ። አንድን የመረጃ ሥራ ለማግኘት ለፍተን ከጫፍ ስንደርስ በተልካሻ ትእዛዝ ይበትኑታል። መሥሪያ ቤቱ ህልውናውን የሚያጣው በርግጥ እኔ ባሰብኩት መንገድ ላይሆን ይችል ይሆናል። ቢሆንም የደኅንነት ኃላፊነቱ ቀስ በቀስ ከእኛ እየወጣ እንደ ሆነ በእርግጠኝነት መተንበይ እችላለሁ። በአንድ ሰው ስህተት ይህች ሀገር በአደጋ ውስጥ ገብታለች ለማለት ያስደፍራል።"

የመረጃ መኮንኑ ከተቀመጠበት ተነሳና ወደ በሩ አቅጣጫ ሁለት ጊዜ ተራምዶ መለስ አለና አስተዋለው። በእልህ እንደተለዋወጠ በዓይኑ እየተከተለው ስለነበር በእይታ ተገጣጠሙ። እጅግ በጣም አሳዘነው።

ሰፊውን የመተላለፊያ ኮሪደር በሚያልፍበት ወቅት እርምጃዎቹን አንድ ሁለት እያለ የሚቆጥር ይመስል ነበር። ወደመጨረሻ ከቀሩት ተባራሪ ሠራተኞች በስተቀር በግቢው የብዙ ሰው ትርምስ ባለመኖሩ ሁሉም ነገር ጸጥ ብሏል። በመቶዎች የሚቆጠር ሕዝብ ሰላም የሚነሳው ግቢ ረጭ ብሎ ሲመለከት የሱንም ልብ ረፍትና ጸጥታ የተሰማው ያህል የበለጠ እንደተረጋጋ የቢሮውን በር ከፍቶ ወደ ውስጥ ገባ። ዘሩባቤል አለምሰገድ።

ክፍሉም እንደዚሁ ጸጥ ብሎ ነበር የጠበቀው። ጸሐፊዋን በዓይኑ ቢፈልጋትም የለችም። ሰዓቱን አየና ራሱን አወዛወዘ። ለአሥራ ሁለት አሥር ጉዳይ። የሥራ ሰዓቷን ጨርሳ ወጥታለች።

ከጠረጴዛው ላይ በርካታ ፋይሎች ከምራለት ነው የሄደችው። ከወንበሩ ላይ አረፍ አለና ስለ ደኅንነት ሹሙ ሁኔታ በጥልቀት ያስብ ጀመር። በጀርባው ችግር አዝሏል።

"ከወጥመድ ልትገባ እየተቃረብህ መሆኑን ያልተረዳህ እንስሳ። ውስኪ እየተጎነጨህ ከልጃገረዶች ጋር መዳራትና ራቁታቸውን በሚደንሱ ሴቶች መደሰት ከትንሽ ጊዜ በኋላ ያበቃል። ለወሲብ ጥመኞች፣ አላፊዎችና ለሕገወጥ ወንበዴ ነጋዴዎች ኢትዮጵያ ስፍራ አይኖራትም። ሁሉም ነገር ያከትማል..." ፋይል የተከመረበትን ጠረጴዛ የጎንዮሽ ገረመመው። የማይጠቅም ጥርቅም የመግለጫ ግባስ እየተራገመ ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ ገላ መታጠቢያው ክፍል አመራ። መታጠብ ያስፈልገዋል። አእምሮው ውስጥ ከተከመረበት ያልረባ ቅራቅንቦ ውኃው ሊፈውሰው ይችል ይሆናል። አንጐሉን ወጥሮ የያዘውን ቆሻሻ ለመገላገል መታጠብ አለበት። የውኃ መዘውሩን ሲከፍተው ከሲሊንደሩ የተጠራቀመው ቀዝቃዛ ውኃ አናቱ ላይ ተቾለለበት...። "በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ . . ."

ያሰበውን ስሜት ስጥቶታል። በዚህች ሀገር ውስጥ እየተደረገ ያለው





ነገር ምንድነው ሲል አሰበ። ሰውን ያህል ፍጥረት በቀላሉ እየተሰወረ የደረሰበት መጥፋት እጅግ አሳሳቢ ጉዳይ ነው። የውጭ መንግሥታት የደኅንነት መሥሪያ ቤቱን ወጥረው ይዘውታል። የደኅንነት መሥሪያ ቤቱ መልስ ማግኘት አልቻለም። ሰዎች ባልታወቀ ምክንያት ራሳቸውን ያጠፋሉ። ምክንያቱም ግልጽ አይደለም። እነዚህ ሁሉ ችግሮች ለሀገር ሰላምና ደኅንነት ለሕዝቦች ሰላምና መረጋጋት ለፍትህ አሰራር እንቅፋት ናቸው። ይህችን አገር እያሸበራት ያለው ምሥጢር ምን ይሆን? ለጥያቄው መልስ ማግኘት ከበደው። ብቻ አንድ አደገኛ የሆነ ነገር ተፈጥሯል። ችግሩ የዓለም ሕዝቦችን ትኩረት ስቧል። መንግሥታትንም ረብሿቸዋል። የውጭ ኃይላትም ሰበብ አግኝተው እያተራመሷት ሊያሸብሯት ሙከራ ላይ ናቸው። አንድ ነገር ታወሰውና ራሱን ነቀነቀ።

ዓመተ ምሕረቱ እንደ ፈረንጆቹ አሥራ ጠዘኝ መቶ ሰባ በኢትዮጵያ ደግሞ በአሥራ ዘጠኝ ስድሳ ሁለት ነው።

የአሜሪካን አየር ኃይል የጦር ጀት ለቅኝት ወጥቶ ወደ ሰሜን ሲበር በድንገት ይሰወራል። የግንኙነት ራዳሩ የተቋረጠባቸው የጦር ኃይሉ የበረራ ኦፊሰሮች ተደናግጠው የሚይዙት የሚጨብጡት ይጠፋባቸዋል። ከአብራሪው ጋር የነበረው የመገናኛ መስመር ከተቋረጠ ደቂቃዎች ይቆጠራሉ። ሁኔታውን ለፔንታጉን ሪፖርት ያደርጋሉ።

ምናልባትም ተጠልፎም ከሆነ አለዚያም አደጋ ደርሶበት ፍለጋ እንዲደረግ ፔንታጉን ያዝዛል። የጦር ጀቶችና ሔሊኮፕተሮች ለፍለጋ ይሰማራሉ። ጀቱ የደረሰበት ይጠፋል። ሁኔታው ከፍተኛ ድንጋጤን ፈጥሮ በነበረበት ሰዓት የተሰወረው የጦር ጀት በሰላም ወደ ጦር ሰፈር ተመልሶ ያርፋል።

በሁኔታው ግራ የተጋቡት የአሜሪካን የአየር ኃይል ባለ ሥልጣን የት ደርሶ እንደመጣ ይጠይቁታል። ፓይለቱ የሰጣቸው መልስ ፍጽም አምነው ሊቀበሉት ያልቻሉ ሕልም ዓይነት መልስ ነበር።

"ከጦር ሰፈሩ የተነሳሁት ለቅኝት ተፈቅዶልኝ ነው። ያለምንም ችግር የተወሰነ ማይልስ በርሬ ነበር። ከተወሰነ እርቀት በኋላ አውሮኘላኗ በተለየ ብርሃን ተሞላችና የኤሌክትሪክ መሳሪያዎቹ በሙሉ ጠፉ። ማንኛውም ነገር አይሰራም። በአውሮኘላኑ ውስጥ የነበሩት ማሽኖች ስልክና ሰዓቶቹ ሳይቀሩ ሥራቸውን አቁመዋል። በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለሁ አውሮኘላኗ በረራዋን አላቆመችም። የምትበርረው ኮምፓሷ እንደተስተካከለ በመሆኑ ግራ ተጋባሁ። የተለየው ብርሃን አልጠፋም። ከአንድ ተራራ ጫፍ ስደርስ አውሮኘላኔ ዝግ ብላ መውረድ ጀመረች። አወራረዷ በጣም የተረጋጋ በመሆኑ ንቅናቄ የላትም። ወደ ተራራው እየተጠጋች በነበረበት ወቅት አስገራሚ የሆነ ነገር ተመለከትሁ። ተራራው ለሁለት እየተከፈለ ነው።

አውሮኘላኗም መውረዷን አላቆመችም። ተራራው ሲከፈት ውስጡ በኳስ ሜዳ ቅርጽ ይታየኛል። በጣምም ይሰፋል። ስፋቱም ከአንድ አውራጃ የሚሰፋ መሰለኝ። እርግጠኛም ነኝ። በጣም ሰፊ አገር ነበር። እጅግ የሚያምርና በተለየ የብርሃን ድምቀት የተሞላ ስፍራ ነው። በጣም ያምራል። አውሮኘላኔ ዝግ እያለች ከተራራው አናት ወደታች ስትርቅ የተከፈተው ተራራ መልሶ ሲገጥም ይታየኛል። በዚህ አስገራሚ ክስተት ውስጥ ብሆንም አልፈራሁም። ልቤ በሆነ ነገር እንደተማረከ ገባኝ። እንደዚያ ባይሆን ኖሮ በጭንቀት በሞትሁ ነበር።

አውሮኘላኔ እየተንሳፈፈች ወርዳ ያረፈችበት ሜዳ እንደ አልማዝ የሚያብረቀርቅና የተለየ ብርሃን የሞላው ነበር። ሁሉም ነገር ከነጭ አልማዝ የተሰራ ነው። ያረፍንበት ሜዳ ሳይቀር የተነጠፈው በሚያንጸባርቅ የአልማዝ ጠጠር ነው። አውሮኘላኗ የተከፈተችው ያለምንም ትእዛዝ ነው።

አካባቢው ነጭ በለበሱና ነጭ የብርሃን ጨረር በሚያንጸባርቁ አጫጭርና በጣም የሚያምሩ ሰዎች የተሞላ ነው። ፍጡራኑ በጣም የሠለጠኑ ናቸው። ሁሉም እንቅስቃሴያቸው በብርሃን አማካኝነት ነው። ሲፋጠኑ እርስ በእርሳቸው ያለመጋጨታቸው አስገረመኝ። ከአውሮፕላኗ የወረድኩት በእነሱ ታጅቤ ነበር። ሁሉም ነገራቸው ተመችቶኛል። ብርሃኑም ለዓይኔ ሳይቀር የተመጠነ ይመስል ምንም አላንጸባረቀብኝም። ከአውሮፕላኗ አውርደው ይዘውኝ የሄዱት ከመሰብሰብያ አዳራሻቸው ነበር። አዳራሹ በጣም ሰፊ በመሆኑ የዓለም ሕዝብ በአንድነት ተሰብስቦ የሚሞላ አልመሰለኝም። መቀመጫዎቹ በሙሉ ከአልማዝ የተሠሩ ወንበሮች ናቸው። የመነጋገርያ ማይኮቹ፣ የመድረክ ጠረጴዛዎቹ፣ በአዳራሹ የበሩት አምፖሎች ሁሉም የተሠሩት ከአልማዝ ነው። በሮቹና መስኮቶቹ ሳይቀሩ የተሠሩት ከነጭ አልማዝ ስለሆነ ልዩ ብርሃን ይሰጣል። ሁሉም ነገር ብርሃን ይረጫል። የሰዎቹ ሰውነትም እንዲሁ ብርሃን የሚረጭ ነው። ከዓይናቸው የሚወጣው የብርሃን ጨረር ድምቀት አለው። ሁሉም ነገር የሚንቦገቦግ ግራጫ ብርሃን ይፈነጥቃል። የቆዩሁት የተወሰኑ ደቂቃዎች መሆኑን ያወቅሁት እዚህ ከተመለስሁ በኋላ ነው። ብዙ ነገሮችን ስለጎበኘሁ ዓመት የቆየሁ መስሎኝ ነበር። ከዋናው የመድረኩ መሪ አጠገብ የተቀመጡትም የክብር አለባበስ ለብሰዋል። ንጉሥ የመሰለው ሰው የተቀመጠው ከአራቱ መካከል ነው። የዚያች ሥልጡን ሀገር ንጉሥ እንደሆነ አልተጠራጠርኩም። እነሱ የሚናገሩት ባይገባኝም እኔ የምለው ይገባቸዋል። በኔ ቋንቋ ነው ያነጋገሩኝ። ለጥያቄዬ መልስ ቢሰጡኝም ከነገሩኝ አንድ እንኳን የያዝኩት ቃል የለም። ከስብሰባ አዳራሹ ወጥቼ ብዙ ነገሮችን ጐብኝቻለሁ። ወደ አውሮፕላኔ ሲመልሱኝ ብዙ ቀናት የቆየሁ ያህል ተሰምቶኝ ነበር። ግን አልነበረም። ይህንን ያወቅሁት ወደ ጦር ሰፈር የተመለስኩት ከጠፋሁ ከትንሽ ጊዜ በኋላ መሆኑ ሲነገረኝ ነው።





የአውሮፕላኗ በር ሲዘጋ ረጋ ብላ ሽቅብ ተንሳፈፈችና ተራራው አናት ደረሰች። የተራራው አናት ከውስጥ ሲታይ እንደ ቤት ጣርያ አለዚያም እንደ ሰማይ ቅርጽ ነበር። የተራራው አናት ሲከፈት አውሮፕላኗ ወጣች። እስከ አሁን ምንም አይነት የኤሌክትሮኒክስ መሳርያ ድምጽ የለም። ከተራራው ብዙ ከፍታ ከወጣሁ በኋላም ሞተሩ አልተነሳም። በረራው ግን የደቡቡን አቅጣጫ ይዞ ስለነበር ወዴት እየሄድኩ እንደሆነ ገባኝ። የምድር ክልል በነበረበት ስፍራ ስደርስ የአውሮላኗ ሞተር ሠራ። ይህንን ያለው የተጠለፈው ፓይለት ነበር።

የአየር ኃይል ባለ ሥልጣኖቹ ባያምኑትም ተቀብለውታል። ተቀብለውት ግን ለማመን አልቻሉም።

በዚህ ውዥንብር ውስጥ እንዳለም የአሜሪካን የጦር ኃይል የበረራ መስርያ ቤት ሌላ ፈተና መጣበት። ነገሩ እንዲህ ነው።

በአሜሪካን አንድ ግዛት በሚኖሩ ከብት አርቢዎች ላይ ከፍተኛ ሽብር ወረደባቸው። በግዛቱ የነበሩ እንስሳት በረቀቀ መንገድ የውስጥ አካላቸው እየተመዘበረ በየቦታው ጥንባቸው ወደቀ። የእንስሳቱ የውስጥ አካል ዝርፊያ የሚከናወነው በጠራራ ፀሐይ ቢሆንም ድርጊቱ ሲከናወን የከብቶቹ ጠባቂዎች ማየት አልቻሉም። የሚመለከቱት የእንስሳቱ ጥንብ መውደቁን ብቻ ነው። የከብቶቹ አካል እየተከፈተ መልሶ የተሰፋ ቢሆንም በወደቁበት ቦታ ጠብታ ደም አይገኝም። ከከብቶቹ አካላት የውስጥ ክፍላቸው ጉበትና ሳንባ፣ ኩላሊትና ጣፊያ፣ ዓይናቸውና የጆሮ ታምቡራቸው ተወስዷል። ይህ ሁሉ ሲከናወን የደም ጠብታ ከመሬት አይፈስም። የአሜሪካን የመከላከያ መስሪያ ቤት ዘመናዊ መሣሪያዎችን በየስፍራው ቢተክልም የእንስሳቱን የውስጥ አካል የሚዘርፉትን ሌቦች ሊደርስባቸው አልቻለም። አሜሪካን በዚህ ሽብር ውስጥ በነበረችበት ወቅት ኢትዮጵያም አንድ የሽብር ታሪክ አስተናግዳ አገሪቷ በሽብር ተናጠች።

ወቅቱ በአሥራ ዘጠኝ መቶ ስድሳ ሁለት በፈረንጆች አሥራ ጠዘኝ ሰባ በመላ አገሪቱ የሰዎች ደም እየመጠጠ የሚወስድ ፍጡር መጣ ተብሎ ሕዝብ በከፍተኛ ሽብርና የስነ-ልቦና ትርምስ ውስጥ ገባ። በርግጥም ሰዎች ተገድለው እየወደቁ ተገኝተዋል። የሰዎቹ አወዳደቅ ከአሜሪካኖቹ እንሰሳዎች ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም ተወሰደ በተባለው የሰውነት አካል ይለያያል። ኢትዮጵያ ውስጥ ድርጊቱ ተፈጸመባቸው የተባሉት ሰዎች ሲሆኑ የተወሰደው አካላቸው ሳይሆን ደማቸው ነው። ድርጊቱ የተከናወነውም በሴቶችና በሕፃናት ላይ ሲሆን በረቀቀ መንገድ ደማቸው እየተመጠጠ ተወስዷል። ለዚህ እንደምክንያት ተሰጥቶ የነበረውም አውሮኘላንና የእሳት ወፍጮ የሚሰራው በሰው ደም ስለሆነ ለዚያ ተግባር ሊያውሉት ነው የሚል ነበር። “ጭራቅ” የተባለው አስፈፊ የኃሳብ ፍጡር ከዚያ በፊት ይነገር አይነገር በውል ባይታወቅም እሱም ሌላው አሸባሪ ሆኖ ቆይቷል። እስከ

አሁንም ጭራቅ ለመጥፎ ሰዎች ምሳሌ ነው፡፡

የሰሜኑ ገበሬዎች የጉበዝ አለቃ መርጠው በየተራራው አናት ቃፊር አቆሙ፡፡ ጥበቃው በዚህ መልኩ ከተደላደለ በኋላ ሴቶች ወደ ገበያና ወደ እንጨት ለቀማ እንዳይወጡ ሕፃናትም ለከብት ጥበቃ እንዳይሰማሩ ተደረገ፡፡

በዚህ ጥበቃ ላይ እንዳሉም ኤፍራታ ግድም በተባለው የሰሜን ሸዋ ወረዳ በይፋት አውራጃ ውስጥ ከማጀቴ ከተማ በስተደቡብ ገሌ ወንዝ ከሚባለው ሸለቆ አንድ ሴት ብቻዋን ወደ ገበያ ስትሄድ በደም መጣጩ አውሬ ትያዛለች፡፡ ከአውሬው ግብግብ ስትገጥም በቃፊር ይጠብቁ የነበሩት ገበሬዎች ጨርሶ ጉዳት ሳያደርስባት ቢያተርፏትም አንገቷ አካባቢ በሹል ስለት ተወግታ ነበር፡፡

ሴትየዋን ሊያጠቃት የያዛት ፍጡር ሰው ቢመስልም ገበሬዎቹ በደረሱበት ወቅት ራሱን ወደ ድመትነት ለውጧል፡፡ በውርርድ ተኩሰው ክር መበጠስ እንደሚችሉ የሚነገርላቸው ሰዎች በፍጥነት ለመምታት ያደረጉት ሙከራ አልተሳካም፡፡ አውሬው እየሸሸ ነው፡፡ ብዙ ጥይት አውርደውበት መውደቅ አልቻለም፡፡ የይፋት በረሃማ አካባቢዎችን እያቆራረጠ ሽሽቱን ወደ ደቡብ አደረገ፡፡ ገበሬዎቹም ተከተሉት፡፡ የአንዱ አካባቢ ለሌላው እያቀበለ አውሬውም ወደ ፊቱ እየሸመጠጠ በቅወት ማፋድ ወረዳ ውስጥ ሲደርስ ከአንድ ዛፍ ላይ ወጥቶ ተቀመጠ፡፡ አልሞ ተኳሾች ሞከሩ አልመቱትም፡፡ በወንጭፍ ድንጋይ ተደብድቦ ተገደለ፡፡

በመጀመሪያ ሰው ቀጥሎ ድመት የሆነው ፍጡር በሞተበት ሰዓት የሰው የመሰለ አካል ያለውና ሰውነቱ በፀጉር የተሸፈነ መሆኑ በገበሬዎቹ ተነገረ፡፡ ከዚህም ፍጡር ሞት በኋላ ህዝቡ በመጠኑ ቢረጋጋም ጭራቅ መጣ የሚለው የማሸበሪያ ጦርነት ለብዙ ጊዜ ቆይቷል፡፡ አሁንም ጭራቁ አለ፡፡ ደም እየመጠጠ የሚወስደው ሰውም አልፎ አልፎ ይታወሳል፡፡ ሰዎችም ይጠፋሉ፡፡

የአሜሪካን የደኅንነትና የመከላከያ መሥሪያ ቤት በተፈጠረበት ሽብር ዘመናዊ ሳይንስ ወለድ መሣሪያዎችን የተጠቀመ ቢሆንም ሊደርስበት አልቻለም፡፡ የወቅቱ የአሜሪካን አስተዳደር በዚህ ውጥረት ውስጥ እንዳለ ለወቅቱ የአሜሪካ ፕሬዚደንት ከሳይንቲስቶች ጥያቄ ቀረበላቸውና ሰውን በጀኔቲክ መንገድ መፍጠር የሚለው ጽንሰ ሃሳብ የተወጠነው አሜሪካን በተለያዩ አሸባሪ ፍጡራን ተደጋጋሚ ትንኮሳ ከተደረገባት በኋላ ቢሆንም ወደ መጨረሻ ተቀባይነት ማግኘት አልቻለም፡፡

የመረጃ መኮንኑ ከጠለቀበት የሃሳብ ባህር የወጣው ስልኩ ሲጮህ ነበር፡፡ ከወዲያኛው የስልክ ጫፍ የመጣው ድምጽ የተረጋጋ ቢመስልም ልቡን አሸበረው፡፡

"ዜናውን ሰማኸው?" ሲል ጠየቀው ደዋዩ፡፡

"የትኛውን ዜና? . . ." ተደነጋገረ፡፡





"በጀርመን ድምጽ የተላለፈውን ዜና አልሰማሁም እንዳትለኝ፡፡"

"ሰምቻለሁ፡፡"

"ባስቸኳይ እንድትመጣ እፈልጋለሁ" አለና መልስ ሳይጠብቅ በጆሮው ላይ ጠረቀመበት፡፡

ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጊዜያዊ የደኅንነት ቢሮ የተቀበለው ሰው እንደቆሰለ አውሬ ተቅበጠበጠ፡፡

"ምን እየተፈጸመ ነው ያለው? እናንተስ ምን እያደረጋችሁ ናችሁ?" ጥያቄ በጥያቄ ላይ ደራረቦ አፍጥጦ ተመለከተው፡፡

"ዜናው የተሰማው እኮ ዛሬ ነው ፡፡"

"የሀገርን ደኅንነት የምትጠብቁት ከውጭ በሚመጣላችሁ ዜና ነው እንዴ?" ሳቅ አለ ሰውየው፡፡

"እንደሱ አላልኩም፡፡ የጠየቁኝ በቀጥታ ስለ ዜናው ስለሆነ ነው ያንን የመለስኩት፡፡"

"የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው ምን እየሠራ ነው?" ሲል ጠየቀው፡፡

"ለብዙ ነገሮች እንቅፋት ይፈጥራል፡፡ ዜናውን ስንሰማም ያየሁበት ግዴለሽነት ነበር፡፡"

"ለምን ይመስልሃል?" አለው ባለ ሥልጣኑ፡፡

"አልገባኝም" አለው ባጭሩ፡፡

"ሊገባህ ይገባል፡፡ ሁሉንም ነገር የማወቅና የመረዳት የሙያ ኃላፊነት አለብህ፡፡ ሰውዬው በአደገኛ ነገር ውስጥ ራሱን ዘፍቋል፡፡"

"ምን አሉኝ?" ቀና ብሎ ተመለከተው ባለ ሥልጣኑን፡፡

"ሰውየው ያለው በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ ነው፡፡"

የመረጃ መኮንኑ ግራ በመጋባት ቀና ብሎ ጣራውን ተመለከተ፡፡

"ሰዎቹ እየተሰወሩ ያሉት በምን ምክንያት ይመስልሃል?" አለው፡፡

"ለኔ ግልጽ አይደለም አለው ብዙ ነገሮችን እያብሰለሰለ፡፡

"አንድ አደገኛ ሁኔታ ተፈጥሯል" አለውና ሲጋራ አቀጣጠለ፡፡

"የምን አደገኛ ሁኔታ ነው የተፈጠረው?" በትኩረት ተመለከተው፡፡

"ሰዎች ከነ ሕይወታቸው መሰወር ጀምረዋል፡፡ ሌላም ችግር አለ፡፡"

"አምን ትልቅ ችግር አለ፡፡"

"መፍትሔው ምንድን ነው ትላለህ ታድያ?" አለ ባለሥልጣኑ፡፡

"ለኔ ግልጽ አይደለም፡፡"

"ምኑ ነው ግልጽ ያልሆነልህ፡፡"

"በአሁን ሰዓት ማንኛውንም መመሪያ እያወጣ ያለው ጊዜያዊው የፀጥታው መስሪያ ቤት ስለሆነ ለእኛ እየከበደን ነው፡፡"

"አልገባኝም" አለው ባለሥልጣኑ፡፡

"ማንኛውንም ነገር እንዲከታተል የተፈቀደለት ከጊዜያዊው የጸጥታው

መሥሪያ ቤት በመሆኑ ዋናው መሥሪያ ቤት ንብ የሌለው ቀፎ ሆኗል።"

"ለምን ይመስልሃል እንደዚያ የተደረገው?" በምፀት ጠየቀው።

"ኃላፊነቱን የመወጣቱ ጥንካሬው ስለወደቀ ይመስለኛል።"

"አዎን። በአሁኑ ሰዓት ዋናው መስሪያ ቤት አገልግሎት እየሰጠ አይደለም።"

ለበርካታ ሰዓት ያለረፍት ተወያይተው ሲለያዩ የመረጃ መኮንኑ አናቱ እንደ ድንጋይ ከበደውና ቡና ከሚጠጣበት ካፌ ገባ። እንዳለውም ከፍተኛ ነገር እየተፈጠረ ነው። ቡናውን እየጠጣ ለማሰብ ሞከረ። የሕዝብ ኃላፊነት የተጣለበት መስሪያ ቤት ከነቀዘ የዚህ ሕዝብ ምርኩዝ ምን ሊሆን ይችላል?





# ምእራፍ ሁለት

ዶክተር ሪቻርድ ዊንገር ለእንግዶች ከተፈቀደው ቦታ መኪናውን አቁሞ ወደ ሕንፃው ሁለተኛ የመግቢያ በር ሲያመራ ጭር ያለውን ግቢ ግራ ቀኝ በእይታው እየማተረ እያንዳንዱን ነገር በጥንቃቄ እየተመለከተ ነበር። ሰፊው የሕንፃው ግቢ ብዙ ትርምስ አይታይበትም። ወደ ውስጥ እንደገባም ከመተላለፊያው ላይ ዕድሜው በሃምሳዎቹ መገባደጃ ላይ የሚገኝ ኢትዮጵያዊ ምሁር እየጠበቀው አገኘው።

ተያይተው ሳይነጋገሩ ተግባብተዋል። ወደ ሕንፃው በር እንዲያመራ በግንባሩ ምልክት ሰጠው ኢትዮጵያዊው። አራት ያህል ሰዎች አሳንሰሩ ተመልሶ እስኪመጣ እየጠበቁ ነበሩ። በአሳንሰሩ በኩል በነበረው ሰፊ ኮሪደር በዝግታ እየተራመዱ ወደ ግራቸው ታጠፉና የተዘጋ በር አጠገብ ደረሱ። ስፍራው ጭር ያለ ነው። ማለፍ የተከለከለ መሆኑን የሚጠቁም ማስታወቂያ ከግድግዳው ላይ ተለጥፏል። ወደዚህ መግባት የተከለከለ ነው" የሚለውን ጽሑፍ ዶክተር ሪቻርድ በጥንቃቄ አነበበው። ቀጥሎ ያለው በርም "ታሽጓል" የሚል ጽሑፍ ተለጥፎበታል። ሁሉም ነገር በማስጠንቀቂያ የተሞላ በመሆኑ ዶክተሩ አልተደነቀም። ጽሑፎቹን በጥንቃቄ ደጋግሞ አነበባቸው።

ኢትዮጵያዊው ዶክተሩን ከተመለከተ በኋላ ከኪሱ ቁልፍ በማውጣት ማስጠንቀቂያ የተለጠፈበትን በር ከፈተው። ወደ ውስጥ እንደገቡም በሩን ቆልፎት ዶክተሩን በፈገግታ አየው። ቀጥሎ ሌላ የተዘጋ በርም ነበር። በበሩም ላይ "መግባት ፈጽሞ የተከለከለ ነው።" የሚል ማስጠንቀቂያ ተለጥፎበታል። ሌላ ቁልፍ አወጣና ከበሩ እጀታ ዝቅ ብሎ በአለው የቁልፍ ማስገቢያው ላይ ከተተና ፊቱን ወደ ዶክተሩ መለሰ። እንግዳው ምሁር ሁሉንም ነገር በጥንቃቄ እየተመለከተ ነው። ሦስት ጊዜ ያህል አሽከርክሮ ቋ-ቋቋ ከአደረገው በኋላ እጀታውን ይዞ ሲስበው ተከፈተ። ሶሥት በሁለት የሚያካልል ስፋት ያለው አነስተኛ ክፍል ነበር የጠበቃቸው። በውስጡ ምንም ዕቃ አልነበረም። ከዚያ አልፎ የሚሄድ የመተላለፊያ በርም የለም። ሁለቱ ምሁሮች እንደተለመደው በዓይናቸው ብቻ ተያይተው ተነጋገሩ። ኢትዮጵያዊው እንደመሳቅ ብሎ የመብራት መቆጣጠርያ የሚመስለውን ሳጥን በጥንቃቄ ሲያሽከረክር መክደኛው ተከፈተ። ከዚያም ወደ ዶክተሩ ፊቱን መልሶ በተለመደው መልኩ አስተዋለው። ዶክተሩ ፈገግ ብሎ አጸፋውን በማድነቅ መለሰለት።

የኪቦርድ መጫወቻ የሚመስሉ ትናንሽ በተኖች ተደርድረዋል። ተራ በተራ ሲጫናቸው የተለያየ ከለር ያለው መብራት ሰጥተው አካባቢውን አደመቁት። የሳጥኑን መክደኛ እንደነበር ، ሲዘጋው የበተኖቹ መብራት ጠፉና በእግራቸው የቆሙበት የሴራሚክ ወለል እንደመንገጫገጭ ብሎ

የግድግዳውን ጥግ በአራቱም መዓዘን ለቅቆ ሁለቱን ሰዎች እንደተሸከመ ቁልቁል ሲንሸራተት የእንግዳው ልብ እንደመከዳት አደረገው። አውሮኘላን ሲነሳ የሚሰማው ዓይነት ስሜት ውስጡን አሸበረው።

ከመጀመሪያው የምድር ቤት ሳሎን ሲደርሱ እንግዳው ዶክተር አንገቱን በዝግታ ነቀነቀ። ሊፍቱ ፍጥነት ስለነበረው በአዳራሹ የነበሩትን ነገሮች ለማየት ዕድል አልነበረውም። የሚቀጥለው አዳራሽም እንደዚሁ በመብራት ኩሬ የተሞላ ነበር። ሶሥተኛውና የመጨረሻው አዳራሽ ሲደርሱ የአሳንሱሩ መቆጣጠርያ ዜሮን አሳየና እንደመነቃነቅ ብሎ በአለበት ቆመ። ሁለቱ ሰዎች ከአሳንስሩ እንደ ወጡም ሽቅብ እየተምዘገዘገ ወደ ነበረበት ተመለሰ። በዚች ደካማ አገር እንደዚህ የተራቀቀ የቴክኖሎጂ ውጤት በማየቱ ሳይገርመው አልቀረም እንግዳው። ሁሉም ነገር በቴክኖሎጂ የዳበረ ከሚገባው በላይ የተራቆቀ ያልጠበቀው ጉዳይ ሆኖበታል። የልማቷ ሳይሆን የጥፋቷ ቴክኖሎጂ በመቅደሙ ኃዘን የተሰማው ነው የሚመስለው። ምን እየተሰራበት እንደሆነ ያውቃል። የዓለም የመጨረሻው የጥፋት መከራ እየተዘጋጀ ነው የሚለው ሃሳብ አእምሮውን ወጥሮ እንደያዘው ሁሉንም ነገር ይቃኛል።

አዳራሾቹ እያንዳንዳቸው አራት መቶ ካሬ ስኩየር ሜትር ስፋት ያላቸው እንደሆኑ እየተረከለት ነው። ቤተ ሙከራዎች ወይም የምርምር ሥራዎች የየራሳቸውን ተግባር የሚያከናውኑባቸው የምሥጢር ሥፍራዎች ያሏቸው ናቸው። በነዚህ ቤተ ሙከራዎችም ሌትና ቀን ምርምሮቻቸውን የሚያከናውኑ አሥራ ስምንት ምሁሮች አሉ። ትልቁና በርካታ ተመራማሪ ሳይንቲስቶችን የያዘው ቤተ ሙከራ የሰውን ልጅ በልዩ ዘዴ የማራባት ሥራ ጥናት የሚከናወንበት ቤተ ሙከራ ነው። በዘርፉም ሁለት ሳይንቲስቶች አስር ፕሮፌሰሮች እና ስድስት ዶክተሮች በጠቅላላው አሥራ ስምንት ተመራማሪዎችን አጠቃልሎ የያዘ ሲሆን ከተመራማሪዎቹ መካከልም ሁለት ኢትዮጵያውያንና አንድ እስራኤላዊ ጨምሮ የተለያዩ አገራት ዜጐች ምሁራንን አጠቃልሎ ይዟል። ዶክተሩና ኢትዮጵያዊው ሳይንቲስት ወደ ቤተ-ሙከራው ክፍል ሲገቡ ከማሽኖች ድምጽና ከሳህኖቹ መንኳኳት በቀር ሌላ የሚሰማ የንግግር ድምጽ አልነበረም። በመሬት ውስጥ በተገነባው የምርምር ተቋም ሕይወት በዚህ መልኩ ቀጥላለች። ዶክተሩ በተገርሞ በዝግታ ራሱን ያነቃንቃል።

በሴራሚክስ ግድግዳ እየተከፋፈለ የተሰራው የቤተ ሙከራ ክፍል ውበትና ጽዳቱ ዓይንን ይማርካል። ሰፊውን አዳራሽ ለሁለት የሚከፍለው የመተላለፊያ ኮሪደርም በነጭ ሴራሚክስ የተነጠፈና እንደታጠበ ሲኒ የሚያብለጨልጭ ነው። በኮሪደሩ ግራና ቀኝም እያንዳንዳቸው አሥራ ሁለት በድምሩ ሀያ አራት ክፍሎች አሉት። የግድግዳውም ሆነ የጣራው ቀለም ነጭ ነው። የኬሚካሎች ሽታ ከመሽተታቸው በቀር አጠቃላይ





ንጽህናው ውብ ተብሎ የሚጠቀስ ነው። ከክፍሎቹ በመጀመሪያ ላይ የሚገኘውን በር ከፍተው ወደ ውስጥ ሲገቡ በርካታ ፎቴ ወንበሮች ያጣበቡት መለስተኛ ሳሎን ነበር የጠበቃቸው። በጥቁር ቆዳ የተሸፈኑት ፎቴዎች የክፍሉን ዙሪያ ግድግዳ ይዘው የተደረደሩ ሲሆን ከመስታወት የተሰሩ ትናንሽ ጠረጴዛዎችም አሉ። የኮሪደሩ ማብቂያ ፊት ለፊት የመታጠቢያ ክፍሎች ቀጥሎ የጅምናዝየም መሥርያ፣ የቴንስ ሜዳና የክብደት ማንሻ ይገኛል። ከነሱ በቀኝ በኩልም የመዋኛ ገንዳ፣ የመልበሻ ክፍልና መዝናኛ ክበብ የሚገኝ ሲሆን ሁሉም ሚሰራው ከኤሌክትሪክ በተገጠመለት መሳርያ ነው። በታይፕ የተተየቡና ያልተተየቡ የእጅ ጽሑፎች በጠረጴዛዎቹ ላይ ይታያሉ። እንግዳውና ሳይንቲስቱ ከፎቴዎቹ ላይ አረፍ አሉ። በረፍት ሰዓት ወደ አዳራሻቸው ሲሰበሰቡ ዶክተሮቹ አዲሱን ሳይንቲስት የተመለከቱት በደስታ ነበር። ኘሮፌሰሩ በተለይ በጣም ተደስተዋል።

ከተሰዓት በኂላ ያለውን ጊዜ በጉብኝት አሳለፈ። የጄኔቲክ የምርምር መምሪያ አላፊው ለአዲሱ ምሁር ማስረዳት የጀመሩት ቀዝቀዝ ባለ ስሜት ቢሆንም ቀደም ሲል የነበራቸውን ጓደኝነት አንስተውበታል። ፈልገው የጠሩትም በዚያው ምክንያት ነው።

ሥራው ሰማኒያ በመቶ ወደ መጠናቀቁ ነበር። የአረባብ ዘዴውን በተመለከተም ከቀደመው የሰው ልጅ አስተሳሰብና የአእምሮ ምጥቀት በብዙ እጥፍ እንዲበልጥ ለማድረግ ብዙ የተደከመበት ነው። በዚህ መልኩ የተገኘው ፍጡር በሰው ልጅ ልብ ውስጥ ያሉትን አስተሳሰቦች ያለምንም መሳርያ ማወቅና መረዳት የሚችል ከመሆኑም በተጨማሪ ከመሬት አካል ውጭ አሉ የሚባሉትን እንደ ዩፎና በራሪ ዲስኮች የመሳሰሉትን ፍጡራን በአካል እየተቀራረበ በማነጋገር ስለነሱ መረዳት ይቻላል የሚል እምነት አሳድሯል። እነሱ የሚያከናውኑትን ማንኛውንም ነገር መስራት ይችላል ብለው ያምናሉ ሳይንቲስቶቹ? ጠቅላላ ባህሪያቸውን በመረዳትም አኗኗሩንም ሆነ አስተሳሰቡን ከእነሱ ማዛመድና ምሥጢራዊ የሆኑትን የተፈጥሮ ድብቅ ባህርያትን ጭምር በቀላሉ መርምሮ መረዳት እንዲችል ይደረጋል ባይ ናቸው።

የተለየ ዘር የመፍጠሩ ዘዴ የሚካሄደውም ከአንዱ የሰውነት ክፍል የተወሰነውን ሴል ቆርጦ በመውሰድ ሲሆን በተዘጋጀለት የላቦራቶሪ ብልቃጥ ውስጥ እንዲያድግ ይደረጋል። በዚህ መልኩ ያደገውን ሴል እንደገና እራሱን በራሱ እንዲያራባ ተደርጐ ከተባዛ በኂላም በተለየ ዘዴ ወደ ሴት ማኅፀን ገብቶ በጽንስ መልክ እንዲፈጠር ማድረግ ነው። ከሴቷ ማኅፀን ክፍል በዚህ መልኩ የሚቆየው ሰው ሰራሽ ጽንስ በሚወለድበት ሰዓት በተለመደው መልኩ እንደ ሕፃን ደረጃ በደረጃ የሚያድግ መሆኑ ቀርቶ የተለየ የባህርይ ይ፱ እንዲመጣ የተደረገ ነው። ይህም ማለት እንደ መደበኛው ፅንስ

ዘጠኝ ወራትን ስለማይጠብቅ እንደ አሁኑ የሰው ዘር አዝጋሚ አይሆንም። በአስተሳሰቡም ሆነ በአካሉ በምድር ላይ ከሚኖረው የሰው ልጅ ስነ ባህርይ ጋር እንዳይመሳሰል በየትኛውም ተግባሩ የተለየ ሆኖ እዲወጣ የተደረገ ነው ማለት ነው። የማይታየውንና በጣም የመጠቀውን ስልጡን ፍጥረት ያለምንም መሳሪያ መገናኘትና ማየት ይችላል። ፍጡራኑ የሚሰሩትን ተግባራትም ማከናወን ይችላል።

ከማይታዩት መናፍስት ጋር የተወራረሰ ባህርይ ያለው ሊሆን ስለሚችልም የቀደመውን ማለት አሁን ያለውን የሰውን ልጅ ዝርያ እንደ ባርያ ቀጥቅጦ የሚገዛ ሊሆን ይችላል የሚል ስጋትም በተመራማሪዎቹ ዘንድ ማሳደሩ አልቀረም። ሰዋዊ ባህሪውን እንደተላበሰ ቢቀጥልም እንኳን የአሁኑ ሰው መናፍስት የሚላቸውን ረቂቅ ፍጡራን ጸብ ጫሪነት ይጸናወተውና ከየአሉበት እያደነ ጦርነት ሊገጥማቸውና ድል ሊመታቸው ይችላል። አለዚያም ማብቂያ የሌለው ጦርነት ይፈጠራል የሚል ስጋትም ያሳድራል። የሰው ልጅ በሚያደርሱበት ተጽኖ ዝርያው ሙሉ በሙሉ ሊወገድና ሊጠፋ ይችላል አለዚያም እየተዳቀለ ምድር እጅግ በሠለጠኑ ፍጡራን ትመላለች የሚል መቋጫው የማይተነበይ የግምት መላምት አሳድሯል። አዝጋሚ የሰው ልጅ የሥልጣኔ እድገትም በአዲሳኑ ስልጡን ፍጡራን በዚህ መልኩ ከተተካ በኋላ ያለው ውጤት ቀስ በቀስ የሚታይ እንጂ አሁን ላይ ግምት እየተሰጠበት መተንበይ አይቻልም የሚል መደምደሚያ ሰጥተውበታል።

ሳይንቲስቶቹ ለእንግዳው ምሁር ገለጣቸውን ያቀረቡለት ከላይ የተዘረዘረዉን እንደመነሻ በማድረግ ሲሆን ስለምርምሩና ከምርምሩ ስለሚገኘው አዲስ የሰው ፍጡር ሲያስረዱትም ለዚች ዓለም ስልጣኔ ምን ያህል ሊጠቅማት እንደሚችል ብቻ ሳይሆን ቀርፋፋውንና አዝጋሚ የነበረውን የሰው ዘር ስልጣኔ በአዲስ ስልጡን መተካት በእርግጠኝነት መቻሉን በማብሰር ነበር።

ምሁራኑ እንደሚሉትም ሆነ ዓለም በተጨባጭ እንደምታስረዳው ለረጅም ዘመን የሰው ልጅ በኖረባቸው ጊዜያት አንደኛው ሌላውን ከመጫን በዘለለ መልኩ የእኩልነት መንፈስ አድሮበት አያውቅም። ጠንካራው ደካማውን ሲያጠቃው ሲቻለውም ሲሸጠው ሲለውጠው ቆይቷል። በአስተሳሰብ የተሻለው ዝቅተኛውን እንደ ዕቃ ሸጦና ለውጦ ተጠቅሞበታል። እንደ እነሱ እምነት በዚህ የሰው ልጅ ግኝት አለቃና ምንዝር ብሎ ነገር የለም። ሁሉም እኩል እያሰበ እኩል ማንኛውንም ነገር ማከናወን የሚችል ፍጡር ይሆናል። በሰለጠነ ማህበረሰብ ውስጥ ጌታና ሎሌ ተብሎ ነገር የለም። በአዲስ የሰው ዝርያ ተተክቶ እራሱን በራሱ መምራት አለበት ባይ ናቸው። የሰው ልጅ።





ስቃይ እንደተሸከመ የሚመጣውንም ብዙ ሚሊዮን ዓመታት መቀጠል የለበትም ብለዉ ያምናሉ። እነሱ እንደሚያስቡት በዚህ ምርምር የሚገኘው ሰው መሰል ፍጡር አሁን በምድር ላይ ለአለው የሰው ዘር በየትኛውም መንገድ ተስማሚ ሊሆን ይችላል እንጂ በምንም መልኩ ይቃረናል ወይም ይጣላል የሚለውን ግምት አይቀበሉትም። በገለጻቸው እንዳስረዱትም አሁን ከአለው የሰው ዘር ጋር ተመሳስለውና ተቀራርበው በተመሳሳይ ሂደት ሊጓዙ የሚችሉ ፍጡራን ናቸው የሚል ነው። የነሱ ጥረት ሰውን ሙሉ በሙሉ መለወጥ ሳይሆን አሁን ከአለው አዝጋሚ የሰው ልጅ የሥልጣኔ መንገድ ማስገኘት እንደሚሆን አብራርተውለታል።

“ውጤቱ ይህ ብቻ ይመስላችኋል?” አለና ሁሉንም ተመለከተ።

“በርግጥ ያቀረብከው ጥያቄ ተገቢና አሁን ላይ ሊነሳ የሚገባውና እንደ አንተ ከአለ ምሁር የሚጠበቅም ነው። ውጤቱ ምንም ይሁን ምን ምርምሩ እስከ መጨረሻው ቀጥሎ የሚከተለውን ሁኔታ ከተግባሩ ማየትና መረዳት ያስፈልጋል” ይህንን ያለው እስራኤላዊው ነበር።

“እንደዚህ ያለ ግምታዊ ትንበያ መስጠት የለብንም። ከዚህ ምርምር የምንጠብቀው አሁን ካለበት ደረጃ የሰውን አስተሳሰብ ሙሉ በሙሉ አውጥቶ ገና ወደ አልተደረሰባቸው ፕላኔቶችና በዓይን ለማየት ከማይችሉ ፍጥረታት ጋር እንዲተዋወቁና እንዲዛመዱ ማድረግ ነው። በሚልዮን በሚቆጠረው ረጅም የትውልድ ሽግግር ጉዞው የተሻለ ለውጥ ሳያመጣ ኖሯል። አሁንም ላይ በዚያው በጥንት ልማዱ እየዳኸ ይገኛል። እየተቀባበለ ሲወራረስ ይዞት የቆየው ራስ ወዳድነትንና ስግብግብነትን ብቻ ነው።

ፍጡራን ከፍጡራን ጋር እንዲተዋወቁ ማድረግ ምቀኝነት፣ ጥቅመኝነት፣ የበላይና የበታችነት ስሜትን ማስወገድ የሚችል ትውልድ ያስፈልጋል። ቀድመን መጥፎውን ጎን አጉልተን የምንመለከት ከሆነ የትም አንደርስም። ቀድሞ በመጥፎው መተንበይ የስንፍና ምልክት ነው። እንደዚያ የምናስብ ከሆነ ያለፈውን ድንቁርና ለተተኪው ትውልድም ማውረስ ነው የሚሆነዉ። በተሰጠን እዉቀት ለውጥ ሰርተን በተግባር ማየት ይጠበቅብናል።” እንግሊዛዊውን ተመራማሪ መለስ ብሎ ሲመለከተዉ ቀሪውን አንተ ቀጥል የሚል መሆኑ ስለገባው ባልደረባዉ ረጋ ብሎ ቀጠለ።

“ወንድሜ እንዳስቀመጠው በምንኖርባት ፕላኔት ላይ አሁን ባለው ቀርፋፋ የሰው ልጅ ጉዞ ምትክ የመጠቀና የሠለጠነ አዲስ ሰው መተካት ነው። የሚደረገው የለውጥ ሂደትም ረጅምና አዝጋሚ የለውጥ ሽግግር ሳይሆን በአንድና በሁለት ትውልድ ወደ ሠለጠነው ዝርያ መለወጥ የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይሆናል። እንደዚህ ለአለው አዲስ ነገር ማንኛውንም አስተያየት ሰጭ በጎውን ጎን ይተነብያል ብለን አንጠብቅም። የምንጠብቅ ሞኞችም አይደለንም። ቀደምት የምርምር ሰዎች አሁን ለአሳዩት የሥልጣኔ ፍንጣቂ አያሌ ትችትና ነቀፋ እንደገጠማቸው

ይታወቃል። የሰው ልጅ በባህሪው ተቃዋሚ እንጂ ደጋፊ ሆኖ አያውቅም። የለውጡ ቅድሚያ ተጠቃሚው ራሱ መሆኑ ግን ግልጽ ነው። የበላይ ገዥነታቸው እንዳይቀር የሰጉ ወገኖች የእኛን ሥራ አጥብቀው መኮነን ብቻ አይደለም አህጉር ጥለን እንድንሰደድ ፈርደውብናል።”

ንግግሩን ገታ ሲያደርግ ተመልክቶ እንግዳው ጣልቃ ገባ።

“በርግጥ ይህ ሁኔታ ማንኛውም ሰው ሊቀበለው የሚገባና አስፈላጊም የለውጥ መንገድ ነበር። ይህንን ስል የሰው ልጅ የሥልጣኔ ለውጥ ሰው በሰውነቱ ሰው ሆኖ የሚሰለጥንበትን ለውጥ ማለቴ ነው። ምናልባትም የአሁኑ የምርምር ለውጥ ከዚህ በተለየ ማለትም ሰው በእውቀት ራሱን አበልጽጐ ሳይሆን እራሱን ወደ ሌላ አዲስና ያልታየ ፍጡርነት ለውጦ የሚመጣ ለውጥ ከሆነና ሰው የነበረበትን ይዘት አጥቶ በሌላ በማይታወቅ ፍጡር ከተካ ተለወጠ ሳይሆን የሚባለው እሱ ጠፍቶ እራሱን በሌላ ፍጥረት ተካ ነው።

የሰው ልጅ በነበረበት የማይቀጥልና ቀስ በቀስ ራሱን እያከሰመ በሰው ግንኙነት ሰው ያልሆነ ሰው መሰል ፍጥረት የሚተካ ከሆነ ለዚህኛው የሰው ልጅ ፍጥረት የሚሰጠው ቀጥተኛ ትርጉም ራሱን ወደ ስልጡንነት ለወጠ ተብሎ አይደለም። ሊሰጠው የሚችለው ቀጥተኛ ትርጉም ጠፍቶ በሌላ ሰው ሰራሽ ፍጡራን ተተካ የሚለው ነው። በእግዚአብሔር የተፈጠረው የሰው ልጅ ከዚህች ፕላኔት ቀስ በቀስ ዝርያው ይወገድና በሰው ሰራሽ ፍጡር ይተካል ማለት ነው። ይህ ሰው ሰራሽ ፍጡርስ ዝርያው እስከምን ድረስ ይቀጥላል? መልሱ በሂደት የሚታይ ስለሚሆን አሁን ላይ ትንታኔ ለመስጠት ይከብዳል። ቁም ነገሩ የሰው ልጅ ሰው ሆኖ በመፈጠሩ ምን ጥቅም አስገኝቶለት አለፈ የሚለው ስለሆነ እሱንም በቀጣይ ማየት እንችላለን።

ይህ ብቻ አይደለም የሚያስከትለው ስጋት። በምርምሩ የተገኘው ሰው መሰል ፍጡር በአፈጣጠሩ ምናልባትም ከሰው የተለየ ቢሆንስ?። ለምሳሌ በመጽሐፍ ቅዱስ በመጽሐፈ ሄኖክና በአሪት ዘፍጥረት ምእራፍ ስድስት እንደምናነበው ማለቴ ነው። በተለይም በመጽሐፈ ሄኖክ ያለው የሰው ልጆች አፈጣጠር በጣም አስደንጋጭ በሆነ መልክና ቅርጽ ተገልጿል። የመጽሐፍ ቅዱስን ትንታኔ መጽሐፍ ቅዱስን እያየን እንነጋገርበታለን። ከፈቀዳችሁ ማለቴ ነው። ለምን የሚል ጥያቄ ብታነሱም መልሴ ምርምርና እምነት ስለሚቃረኑ የሚለው ሆኗል። ከዚያ በፊት ግን ሊከሰት ቢችልስ? በሚለው አሳብ ላይ እንወያይ።

በላብራቶሪ የተገኘው ግኝት አጠቃሳይ ይዘቱ ብቻ ሳይሆን ባህሪውም ሆነ አመጋገቡ ከአሁኑ ሰው ጋር የማይመሳሰል ሆኖ ማንኛውንም ፍጡር ሰውን ጭምር ማለቴ ነው በመብላት የሚያስወግድና እራሱን የሚያቆይ ቢሆንስ? አለዚም ደግሞ መርዛማ ነገር ሆኖ በዚህች ምድር ላይ ያለን





ማንኛውንም ፍጥረት እየመረዘ ቢፈጀውስ? እነዚህ ሁሉ ግምታዊ ስጋቶች ናቸው። ምናልባትም እኮ ተመራማሪዎቹ ራሳችሁ በፈጠራችሁት ፍጡር ልትጠፉ አለዚያም ልትበሉ ትችላላችሁ።

ከግምት ማስገባት ያለባችሁ ከላብራቶሪ ከመውጣቱ በፊት ነው። ከሚሊዮን ዓመታት በፊት ተፈጥሮ የነበረውን የሰው ልጅ ለውጥና ያስከተለውን ጥፋት እንደማጣቀሻ እንውሰድ። ምናልባትም በዚያ ዘመን የተከሰተውና በመጽሐፍ ቅዱስ በመጽሐፈ ሄኖክ የተጠቀሱት ሰውን ከነነፍሱ ይውጡ የነበሩት ሰው መሰል ፍጡራን አመጣጣቸውን አናውቅም።

ስለሆነም እንዴት ወደዚህ ዓለም መጥተው በመጨረሻም ምን ዓይነት ጥፋት እንዳስከተሉ ከጥቅሱ ማየት ይኖርብናል። በኔ እምነት ይህ ክስተት በራሱ በሰው ልጅ ያልተገባ ሙከራ የመጣ ሊሆን እንደሚችል ነው። ይዘቱ ይለያየ እንጅ የሰው ልጅ በራሱ መንገድ ተመራምሮ ካአገኛቸው ውጤቶች አብዛኛዎቹ ይህችን ዓለም ከስጋት ላይ የሚጥሉ ሆነዋል። ከዚያ በፊት የነበረውን የሰውን ልጅ የመመራመር ብቃት ለመረዳት ባንችልም በመጽሐፈ ሄኖክ ያየናቸው በሰው አምሳል ተፈጥረው ሰውን በመመገብ መልሰው ለማስወገድ ደርሰውም ነበር። በርግጥ በዚያን ዘመን ስለነበረው የቴክኖሎጂ እድገት ታሪክ በራሱ ያስቀመጠው ማስረጃ ባይኖርም በሰው ልጅ የምርምር ውጤት የተገኙ ስህተቶች ሊሆኑ ይችላሉ የሚል ግምት አድሮብኛል። ስለ ሁሉም ነገር በእረፍት ሰዓት በድጋሚ የምንወያይበት ይሆናል። እነዚያ ፍጡራንም እንዴት ሊጠፉ እንደቻሉ መጽሐፍ ቅዱሱ የሚጠቁመን ይኖራል ብዬ እገምታለሁ። ለሁሉም ከሚቀጥለው ጉብኝቴ በኋላ በስብሰባው አዳራሽ ሁላችንም እንገናኝ።”

ዝም ብለው የጠበቁትን ያህል በቁጣ ገነፈሉ ኘሮፌሰሩ።

“ይህንን የምርምር ዲዛይን የፈጠርከው አንተ መሆንክን መዘንጋትህ አስገረመኝ። ለማንኛውም እንዳልከው በረፍት ላይ በሰፊው እንነጋገርበታለን” አሉትና በጥርጣሬ አስተዋሉት።

በተለያቸው በብዙ ዓመታት ቢያገኙትም በትንሽ ደቂቃዎች ውስጥ በጥላቻ እንደተመለከቱት ገብቶታል።

ከነበረበት አገር ባልጠሩትና ወደ እዚህ ስፍራ ባላመጡትም ነበር። የመጀመሪያው የቡድኑ መሪ እንደመሆኑ ፈልገው እንዳገኙት ደስታቸው ወሰን አልነበረውም።

እንደመጣላቸው ሲጠይቁትም ተስፋቸው ብዙ ነበር። አሳዛኙ ነገር የመጀመሪያውን እሱነቱን ይዞ ያለመምጣቱ ሆነና አበሳጫቸው እንጂ።

ይህ ሰው ሁሉንም ነገር እርግፍ አድርጐ ትቶ ወደ ሕዝብ ሲደባለቅ የቀደመ እሱነቱንና የነበረው የጥበብ ምጥቀቱ ርቆታል ማለት ነው። ኘሮፌሰሩ በሃሳብ ተዋጡና ተመለከቱት።

# ምዕራፍ ሦስት

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከተመሰረተበት ከሃምሳ ስምንት ዓመተ ምሕረት ጀምሮ ለግማሽ ምእተ ዓመት ያህል ከሰኞ እስከ ቅዳሜ በእሑት የሥራ ቀናት በቀን ለአሥራ ሁለት ሰዓታት ለደንበኞቹ አገልግሎት እየሰጠ ቆይቷል። የባንኩ ደንበኞች ጥሬ ገንዘብን ብቻ ሳይሆን ወርቅን አልማዝንና የከበሩ ማእድናትን በአደራ ያስቀምጣሉ። ከፈለጉም ወርቁን ወደ ገንዘብ፣ ገንዘቡን ወደ ወርቅ በመለዋወጥ ማስቀመጥ ይችላሉ። ከደንበኛው ጋር በሚደረግ የውል ስምምነት መሰረትም ንብረቱን ከአስቀመጠው ግለሰብ ወይም አካል በስተቀር ልጅ አለዚያም ሚስት ወይም ባል የደንበኛውን ንብረት በምንም መንገድ እንዲያውቁት አይደረግም።

ያስቀመጡትን ንብረት መልሰው ለመውሰድ በሚፈልጉበት ጊዜም የባንኩን የአገልግሎት ዋጋ ከፍለው ንብረታቸውን በፈለጉት መንገድ በገንዘብ አለዚያም ይዘቱን፣ ዓይነቱንና ደረጃውን ሳይለውጥ ያስቀመጡትን ጥሬ ዕቃ ዓይነትና ደረጃውን ሳይለውጥ በአስቀመጡት መልኩ መረከብና መውሰድ ይችላሉ። ምሥጢራቸው እንደተጠበቀላቸው እነሱ በፈለጉበት ጊዜ ከባንኩ አውጥተው ለመውሰድ የሚከለክላቸው ነገር የለም። ይህ አንጋፋ ብቸኛ ባንክ በዚህ መልኩ ደንበኞቹን ሲያገለግል ቆይቷል።

በዚያን ቀን ከባንኩ የመጨረሻው ፎቅ የተቀመጠው ሰው በዚህ መልኩ ለመስተናገድ የመጣ ደንበኛ አልነበረም። የእንቁላል ቅርጽ ባለው ሰፊ ኮሪደር የሚርመሰመሱትን የተለያዩ አገራት የባንኩን ተገልጋዮች በዓይኑ እየተከታተለ የነበረው ሰው ሌላ ጉዳይ ነበረው። አንጋፋው ባንክ በአንድ ጊዜ ብቻ ከአምስት መቶ በላይ ሰዎችን የማስተናገድ አቅም ሲኖረው አሰራሩም ቢሆን እጅግ የተቀላጠፈ ስለመሆኑ ደንበኞች ይመሰክሩለታል። በአሰራር ዲዛይኑ ለየት ያለው እና ከተሠራ ግማሽ ምእተ ዓመት ያሳለፈው ማራኪ ሕንፃ "ወርቃማው ባንክ" ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ስያሜው የተሰጠውም የሕንፃው የውጭ አካል ወርቃማ በሆኑ የነሃስ ብረቶች የተጌጠ በመሆኑ ነው።

የሕንፃው ጣሪያ አንድ ሜትር ያህል ውፍረት ባለው ኮንክሪት የተገነባ ሲሆን የመሶብ ቅርጽ እንደያዘ ወርዶ ሁለተኛው ፎቅ ላይ ሲደርስ ጣሪያው ይገጥማል። መጨረሻው ፎቅ ሆኖ ከጣሪያው እስከ ወለሉ የሚደረገውን ማንኛውም እንቅስቃሴ ለመመልከት እጅግ ምቹ ነው። ከአምስት መቶ በማያንሱት የደንበኞች መስተናገጃ የሚደረገውን እንቅስቃሴም ሆነ ደንበኛው ስንት ብር እንደሚያወጣና እንደሚያስገባ ከገንዘብ ከፋዩ ጋር እኩል መቁጠር ይችላል። የደንበኞች ማስተናገጃ ባንኮኒው ሳይቀር እንደ ጣሪያው ሁሉ በጦር ዲዛይን ቅርጽ የተሠራና ኢትዮጵያ በጦርነት ያሳለፈችውን ረጅም ታሪኳን



ማጉርሚሳቢብ

በመዘክርነት የሚጠቁም ነው የሚመስለው።

ለእንግዳ መቀመጫ የተዘጋጁት ፎቴ ወንበሮች ፊታቸውን ወደ ባንኮኒው አድርገው ጀርባቸውን ክብ ቅርጽ ለአለው ክፍት ቦታ በመስጠት ዞረው የገጠሙ ናቸው። ወደ ባንኩ የገባ ማንኛውም ሰው የሕንፃውን ጠንካራ አሠራር ተመልክቶ ጣሊያናዊውን የሕንፃ ባለሙያ ባርኔሮን ሳያደንቅ የሚወጣ ሊኖር አይችልም። አንዳንድ ሰዎች ስለሕንፃው ያላቸውን አስተያየት ሲገልጹ የጣሊያን የሕንጻ ጥበብ ያረፈበትና ውድ ዋጋ የወጣበት ነው ይላሉ።

በስተምስራቅ ከሦስት መቶ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘው የመከላከያ ሚኒስቴር ቢሮ የሚከፍለው ሰፊው የመኪና መንገድ ሲሆን ባንኩና የመከላከያው ቢሮ ሕንፃ ውስጥ ለውስጥ በተሠራ ዋሻ ይገናኛል ተብሎ ይታመናል። የባንኩና የመከላከያው ቢሮ በዋሻ እንዲገናኝ የተደረገበት ምክንያትም በባንኩ የመጨረሻ ግራውንድ ወይም ዋሻ ውስጥ የሚቀመጡ ወርቅና አልማዝን የመሳሰሉ ውድ ዕቃዎች በመከላከያ የጸጥታ ሠራተኞች እንዲጠበቁ ለማድረግ ነው የሚል ግምት አለ። ኢትዮጵያ ሆቴልን ጨምሮ በመሬት ውስጥ ዋሻ እንዲገናኙ ተደርገው የተሠሩ ሲሆን የመከላከያ ባለ ሥልጣናት ያለምንም ችግር ወደ ሆቴሉ እየሄዱ ማረፍ ይችላሉ። የጥንካሬያቸውን ደረጃ በተመለከተም የመከላከያ ሚኒስቴር ሕንፃ የጣሪያው መከደኛ ቆርቆሮ ከመሆኑ በስተቀር እንደ ባንኩ ሁሉ በጠንካራ ማቴሪያሎች የተገነባ ልዩ ሕንፃ መሆኑ ነው የሚነገርለት። በንጉሡ ዘመን ከተሠሩትና ጠንካራ ናቸው ተብለው ከሚገመቱት ህንፃዎች የሀገር ግዛት ሚኒስቴር የአሁኑ የሀገር ውስጥ ደኅንነት ቢሮንና የብሔራዊ ቲአትር ተመሳሳይ ናቸው። አፄ ኃይለ ሥላሴ ወደ ውጭ አሸሽተውታል የሚባለው ወርቅም በዚሁ ዋሻ እንደሚገኝ ነው የሚታመነው። በአፄ ምኒልክ የተገነባውና ታላቁ ቤተ መንግሥት ተብሎ የሚጠራውም ሆነ በአፄ ኃይለሥላሴ የተገነባው ሁለተኛው ኢዮቤልዩ ቤተመንግሥት የአሰራር ጥንካሬውን በተመለከተ የነዚህን ሕንፃዎች ያህል ጥንካሬ የላቸውም ተብሎ ነው የሚገመተው።

የጣሪያውን ክብ እንደጠበቀ ወርዶ ከመጨረሻው ወለል የሚደርሰውና የመጠነኛ ሳሎን ያህል ስፋት ያለው ስፍራ የመከላከያ ብረት የተገጠመለት ሲሆን ደንበኛው ተቀምጦ ተራ ሲጠብቅ ከታች ወደ ላይም ሆነ ከላይኛው ወደታች መተያየት ይችላሉ። ሕንፃው የቆመው በሰው ሰራሽ ሃይቅ አለዚያም ባህር ላይ በመሆኑ በዋሻው የተቀመጠው ንብረት የሚጠበቀውም በውኃው ውስጥ በሚኖረው ዘንዶ ነው የሚል አፈ-ታሪክ አለው። ከመጨረሻው ወለል ዋሻው መግቢያ ላይ ሁለት ተሽከርካሪ ባለ ጥቁር ቆዳ ፎቴ ወንበሮች ሲኖሩ የቀረው ባዶ ቦታ መጠነኛ ስፋት አለው። አንደኛው ጠረጴዛ ሁል ጊዜ ሰው አልባ ሲሆን በሁለተኛው ጠረጴዛ አንዲት በመካከለኛ ዕድሜ ላይ የምትገኝ የቀይ ዳማ ሴት ተቀምጣ ከፊት ለፊቷ ያለውን

የካዝና በር በዓይነቁራኛ ትመለከታለች፡፡ አልፎ አልፎ ኢንተርኔት የምትጠቀም ቢሆንም ብዙ የሥራ ውጥረት ያለባት አትመስልም፡፡ የቤተ መቅደስ በር መዝጊያ ያህል መጠን ያለው ትልቅ ካዝና እንደተዘጋ ስለሚውል ሰው ሲገባና ሲወጣ አይታይም፡፡

የግራውንዱ መዝጊያ የሚከፈተውም ሆነ ተመልሶ ሊዘጋ የሚችለው በተገጠመለት የቴክኖሎጂ መሳርያ ሲሆን በሰው ኃይል ይዘጋና ይከፈት ተብሎ ቢሞከር የማይታሰብ ነው፡፡ የደርግ መንግሥት ወርቁን ለማውጣት የሶብየትና የኩሪያ ባለሙያዎችን በማምጣት የሞከረ ቢሆንም አልቻለም ነው የሚባለው፡፡ ኢህአዴግ ፍለጋ ያድርግ አያድርግ የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ የተከፈተውን በር ለመዝጋት አለዚያም ለመክፈት ከተፈለገ ከጠረጴዛው ስር ያለውን ፔዳል በእግሯ ስትረግጠው ከድምጽ በፈጠነ ቅጽበት በሩ ይዘጋና ከግንቡ ጋር ተመሳሳይ ቅርጽ ይይዛል፡፡ ከበሩ ወደ ውስጥ ሲገባ የሚገኘው በኤሌክትሪክ ብርሃን የተሞላ መለስተኛ አዳራሽ የግንቡን ጠርዝ ይዞ ዙሪያውን በመደርደሪያ የተሞላ ሲሆን በመደርደሪያዎችም የተለያዩ ዶክመንቶች ስለተገጠገጡ መጽሐፍት አዳራሽ አለዚያም ቤተ መዘክር ነው የሚመስለው፡፡ በስተቀኝ ታጥፎ ሀያ ሜትር ያህል ከተሄደ በኋላም በቀይ ሴራሚክ የተሠራ ደረጃ ይገኛል፡፡

"ወደዚህ መጠጋት ክልክል ነው" የሚል የማስጠንቀቂያ ጽሑፍ የተለጠፈ በመሆኑ የጸጥታ ሠራተኞቹም ሆኑ የባንኩ ሥራ ኃላፊዎች ወደዚያ መቅረብ አይችሉም፡፡

ከተቀመጠበት ተነሳና በዝግታ እየተራመደ ክቡን ኮሪደር ይዞር ጀመር፡፡ ወደዚያው የባንኩ የጸጥታ ሠራተኛ ከሴትዮዋ ጋር ሲነጋገር ተመለከተ፡፡ ሴቷንና የጸጥታ ሰራተኛውን እየተመለከተ የነበረውን ሰው እንቅስቃሴ በዓይነቁራኛ ይፈትሽ ያዘ፡፡ ሁሉም ነገር በነበረበት የቀጠለ ቢሆንም ውስጡ ተረበሸበት፡፡ እያነጋገራት ያለው ሰው ሰፋ ያለ የዝናብ ካፖርት የደረበና ከብብቱ ውስጥ ከባድ ዕቃ ያንጠለጠለ ነበር፡፡

"ተሳክቷል" አለ ፡፡ ያለ ጥርጥር ሁሉም ነገር ወደ እውነት እየተለወጠ ያለበት ደቂቃ ነው አጉተመተመ፡፡ ከትንሽ ጊዜ በኋላ ሁሉም ነገር ያበቃል፡፡ በካፖርቱ ውስጥ የባሌስትራውን ብረት እንዳንጠለጠለ ከሴትየዋ ጋር ከተነጋገሩ በኋላ በሩን ስትከፍተው አልፎ ወደ ግራውንዱ ዘልቆ ሲገባ ተመለከተው፡፡ የልቡ ምት በከፍተኛ ፍጥነት ሲደልቅ ተሰማውና መላ ሰውነቱን ትኩስ ላብ ሲያጠምቀው በደስታ ረክቶ ፈገግ አለ፡፡ ርምጃውን በመቀጠል በስተምስራቅ በነበረው ደረጃ ላይ ቆመ፡፡ ጥቁር ሱፍ የለበሰና የአፍሪካዊ ቀለም ያለው ሰው ከታች ወደ ላይ ደረጃውን ወጣና እርምጃውን ፈጠን አድርጎ ትከሻውን በግማሽ ገጭቶት ይቅርታን በሚጠይቅ ዓይነት መለስ ብሎ በሁለት እጁ እንደማቀፍ አድርጎ ወደ ጆሮው በመጠጋት "ጨዋታው በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ ነው፡፡ ወደ





ግራውንዱ ገብቷል" ብሎት በተቃራኒው መተላለፊያ መዞሩን ቀጠለ፡፡

ትከሻውን ገጭቶት ከተላለፉት ሰው ጋር በዓይን ጥቅሻ ተያይተው ተላለፉና ጀርባ እንደተሰጣጡ በአንድነት ሰዓታቸውን ተመልክተው በስሜት እንደ ተግባቡ ሁሉ በተመሳሳይ መልኩ ራሳቸውን በመነቅነቅ የጊዜውን መድረስ ለየራሳቸው አበሰሩ፡፡ ሁሉም ነገር ከሰዓቱ ጋር አብሮ እየተከናወነ በመከነፍ ላይ ነው፡፡ ከትንሽ ደቂቃዎች በኋላ የነገሩ ማብቂያ ፊሽካ ይሰማል፡፡ መጀመሪያ ቆሞበት ከነበረው የደረጃው ጠርዝ ትይዩ እንደ ደረሰም ወደ ደረጃው አመራ፡፡ ብቸኛው ዓለም አቀፍ ባንክ የደንበኞቹን አገልግሎት እየሰጠ ከወትሮው ባልተለየ ሁኔታ ሁሉም ነገር በነበረበት እኳኋን ውደቱን ቀጥሏል፡፡ የላይኛውን ክብ ኮሪደር እየዞረ የነበረው ሁለተኛው ሰው ወደ መጨረሻው ግራውንድ ሲመለከት ደስታ ይሁን ድንጋጤ በቅጡ ያልተረዳው ነገር ውስጡን ረበሸውና ልቡ በኃይል ትደልቅ ጀመር፡፡ የመጨረሻው ዙር ላይ በመድረሱ ጡዘቱ እየጨመረ በጣም እየፈጠነ ነው፡፡ ነገሩ ሁሉ ከሃሳብ ወደ ድርጊት ተለውጧል፡፡ በካዝናው በር ወደ ግራውንዱ ገብቶ የነበረው ሰው በገባበት አኳኋን ትከሻውን ወደ ግራ በኩል አጉብጦ ሲወጣ በጥንቃቄ ተመለከተው፡፡ የልቡ ፍጥነት ጨመረች፡፡ ሁሉም ነገር ወደ መጨረሻው እየተቃረበ በመሆኑ የልቡም ንዝረት ጨምሯል፡፡ የጨዋታው ፍፃሜ ምን ይሆን? "እሱን የሚያውቀው ዲያብሎስ ብቻ ነው" አለ ለራሱ፡፡ ሁሉንም ነገር በድል እንወጣዋለን እንዲህ እያልን እንድንዘምርልህ፡፡ "በጥልቁ ያለህ አባታችን ሆይ ስምህ ይረገም መንግሥትህ ትጥፋ ፈቃድህ በጥልቁ እንደሆነች እንዲሁ በገሀነብ ትሁን የጠየቅንህን ሁሉ ሳትታክት ስጠን" ጨዋታው ሊጠናቀቅ ነው፡፡ ወደፊት እንጂ ወደ ኋላ የማይታሰብ የምጥ መጨረሻ ሆኗል፡፡

ከእርኩሱ ቅዱስ ይሻላል፡፡ "ገብርኤል አንተ እርዳን" በርግጥ ይህንን ተግባር ገብርኤል ይደግፈው አይደግፈው እርግጠኛ አይደለም፡፡ ያም ሆኖ ቅዱስ አይጨክንም፡፡ ሴትዮዋን እጅ እንደመንሳት ብሎ በጀርባዋ በኩል አለፈና ደረጃዎቹን መውጣት ሲጀምር ተመለከተው፡፡ "መልአኩ ገብርኤል አንተ እርዳን..." እየደጋገመ ቃላቱን በለሆሳስ ማነብነብ ቀጠለ፡፡ ከአሁን በኋላ የእርኩሱ መንፈስ አገልግሎት ማብቃት አለበት፡፡ ቅዱስ ገብርኤል ከአንተ ጋር እንደራደር፡፡ እባክህ አትጨክን፡፡ ከሱ ጋር የነበረው ሰው በደረጃዎቹ እየተንደረደረ ወርዶ ከባንኩ የጸጥታ ተቆጣጣሪ ጎን ቆሞ በየመስኮቶቻቸው ሆነው እየተቀበሉ አለዚያም እያስረከቡ ያሉትን ደንበኞች ይመለከት ጀመር፡፡ ሆኖም እይታና ቀልቡ ያለው ከነሱ ላይ አልነበረም፡፡ ከነሱ ላይ ያፈጠጠው ደመ ነፍሱ ብቻ ነው፡፡ መንፈሱ የምትይዝ የምትጨብጠውን አጥታ ትቃትታለች፡፡ መከረኛ ,ነፍሱ፡፡ በአንዳች የስሜት አየር ተነፍታ ልትተረተር ነው፡፡

የግራውንዱን ደረጃ እየወጣ ያለው ባለረጅም ካፖርት ሰው

መራመድ ያቃተው ለዋስ ሆኖበታል።

ደረጃዎቹን ጨርሶ የላይኛውን ወለል እንደረገጠ በስተምስራቅ በኩል ባለው መውጫ በር በእርጋታ ተራመደ። ሴቷም በዓይኗ እየተከተለችው ነበረች። ሌሎች እንቅስቃሴዎችንም እንዲሁ የምትከታተል ትመስላለች። በጸጥታው መካከል የሚሰማት ከፍተኛ የሆነ የረብሻ ድምጽ አለ። ከየት እንደሚመጣ አታውቅም። ሰውየው እየተጠነቀቀ በዝግታ እርምጃ የቀጠለው በሎጥ ተመሳሳይ ቢሆንም ረጅሙን የውጭ ደረጃ ቀልቁል እየወረደ ነበር።

ከመጨረሻው ፎቅ ላይ ሆኖ ይከታተል የነበረው ሰው እየተንደረደረ በመውረድ ላይ እንዳለ ከአንዱ ሰው ጋር ትከሻ ለትከሻ ተላተመ። ሰውዬውን ይቅርታ ጠይቆት መንገዱን ሊቀጥል ሲል የተገጨው ሰው የሆነ ቃል እየተራገመ ነበር። "ዕድሜ ልክህን ስትጐተት የምትኖር ደደብ" ስለምትረከበው ብዙ ሚሊዮን ብር እያሰበች ቆይታ ፊቷን ስትመልስ በድንጋጤ ተኮማተረች። የግራውንዱ በር ክፍት ነበር። እየተርበተበተች እግሯ ስር ያለውን ፔዳል ስትለቅቀው እንደነበር ተዘጋ።

"አምላኬ ባልተጨበጠ ሀብት ልቤ" እንደማቃሰት እያለች ቀና ብላ ወደ መውጫው ተመለከተች። ሁሉም ነገር በነበረበት እንደቀጠለ ቢሆንም ውስጧ ተረብሿል። ሚዛኑን አስቶ እንዳይጥለው በጥንቃቄ እግሩን እያነሳ ረጅሙን ደረጃ ወርዶ ከአስፋልቱ አጠገብ ቆማ ከነበረች ፔጆ ውስጥ ሲገባ ከመሪው አጠገብ የተቀመጠው አፍሪካዊ ቀለም ያለው ግዙፍ ሰው ፈገግ ብሎ ተመለከተው። የድራማውን መጠናቀቅ የሚያበስረው መጋረጃ ከበስተኋላው ተንሸራትቶ ሲዘጋ እየታየው ነበር ወደ መኪናዋ የገባው።

"ሁሉም ነገር በታቀደለት መልኩ የተጠናቀቀ ይመስላል።"

በካፖርቱ ውስጥ ያንጠለጠለውን የሸራ ቦርሳ ወደ ወንበሩ እያንሸራተተ በእፎይታ ተነፈሰ። መርሴዲሱ ሲንቀሳቀስ ፔጆዋም በተመሳሳይ ፍጥነት ከቆመችበት ወደ ኋላዋ ተንሸራትታ ተንቀሳቀሰች። መስመሯን ስትይዝ መርሴዲሱም ወደ ተመሳሳይ አቅጣጫ አፍንጫውን ደገነ። ብሔራዊ ቲአትር አጠገብ ሲደርሱ ተመሳሳይ ፍጥነት ጨምረው አካባቢውን ጥለው ለመጥፋት እንደቀስት ተወረወሩ እስከዚያ ድረስ ሁሉም ነገር በነበረበት በጸጥታ እየተከናወነ ነበር።

"ሁሉም ነገር ይዘቱን ሳይለውጥ ተከናውኗል" አፍሪካዊው መሪ የጨበጠው ሰው ድጋሚ አናገረው።

"ያልጠበቅሁት ሂደት ነው" በረጅሙ ተንፍሶ መለሰለት።

"ሴትዬዋን አላመንኳትም ነበር" አለ አፍሪካዊው ሰው።

"እኔም ጥርጣሬው ነበረኝ።"

"ስትዘገይ መደንገጥ ጀምሬ ነበር። ግራውንዱ ምን ይመስላል።"

"እስከ ተወሰነ እርቀት ድረስ ነበር የገባሁት።"

"ይጨልማል እንዴ።"





"በብርሃን ኩሬ የተሞላ ነው።"

"ቀጥሎ ያለው ግራውንድ ባህር ነው የሚባለውስ እውነት ነው?"

"እንደዚያ ሲባል እሰማለሁ።"

"ባህሩ ምንድነው?" አለ አፍሪካዊው።

"ንጉሡ አልማዙን የሚጠብቅላቸው ዘንዶ አስቀምጠውበታል ተብሎ ያወራል።"

"ምን ያህል እውነት ነው?" አለው እየተገረመ።

"ርግጠኛ መሆን አይቻልም" ሲል መለሰለት ሳቅ ብሎ።

# ምእራፍ አራት

ጠባቧ የስብሳብ አዳራሽ በምሁራት ተጨናንቃለች:: ተመራማሪዎቹ ለምሁሩ ጥያቄ መልስ ከመስጠታቸው በፊት እርስ በራሳቸው ተያይተው በሃሳቡ መግባባታቸውን መናበብ ነበረባቸው:: እናም ሁሉም ነገር በጸጥታ ተውጧል:: አንዱ የሌላውን አሳብና ፍላጎት አንብቦ ለመተማመን የወሰደባቸው ጊዜ ከሁለት ደቂቃ ያልበለጠ ነበር:: የጄኔቲክ ተመራማሪው ቡድን መሪ ፕሮፌሰር የንባብ መነፅራቸውን ከዓይናቸው ላይ በጥንቃቄ አንስተው በጣቶቻቸው ጫፍ ዓይኖቻቸውን አሻሽተው ረጋ ብለው ንግግራቸውን የጀመሩት የተዳከመ በሚመስል ስሜት ነበር::

"በአሁን ሰዓት ይህንን ምርምር በፋይናንስ በኩል ሊረዳው የሚችል አካል የለም:: በተለይም በዚህ የምርምር ዘርፍ በኩል ከፍተኛ ድጋፍ በመስጠትም ሆነ ምርምሩ እንዲካሄድ ሙሉ ፍላጐት የነበራት አሜሪካ አሳቧን ቀይራ ምርምሩን ከማውገዟ በተጨማሪ በአገሯ የተጀመረውን የምርምሩን ተቋም እንዲዘጋ አድርጋለች:: ለዚህ ምርምር ከፍተኛ ድጋፍ የነበረው ከቡሽ በፊት የነበረው የአሜሪካን አስተዳደር እንደ ነበር ሁላችንም የምናውቀው እውነታ ነው:: ቡሽ ወደ ሥልጣን በመጣበት ጊዜ የእምነት አባቶች በአስነሱት ተቃውሞና ነቀፋ ምክንያት ተቋሙ ሙሉ በሙሉ እንዲዘጋ እና እኛም ከአገር እንድንሰደድ የአሜሪካ አስተዳደር ፈርዶብናል:: ምርምሩን እንዲዘጋላቸው ያወገዙት እነሱ እንደሚሉት ፈጣሪን አስቆጥቶ መዓትን የሚያስከትል በመሆኑ አልነበረም:: አሳባቸው ይህ ቢሆን ኖሮ እነሱ ራሳቸውን መፈተሽ በቻሉም ነበር::

ሕዝብን አደናቁረው ዕድሜ ዘንት ዓለም የነሱ አምላኪና ተገዥ አድርገው ለመቀጠል ነው:: ምንም እንበል ምን አሸናፊዎቹ እነሱ ሆነው ምርምራችንን አቋርጠን ለመሰደድ ተገድደናል:: ይህ እርምጃ የተወሰደበት ዋናው ምክንያት የምርምሩ ውጤት በሃይማኖት መሪዎች በኩል የተወገዘና የተነቀፈ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን አሜሪካንን እምነት የለሽ ስለአስመሰላትም ነበር:: የሰው ዘር የማራባት ምርምሩን በትክክል ሊደግፍ ይችላል ብለን የምንገምተው ከሰባት ቢሊዮን የአለም ህዝብ ከአንድ በመቶ አይበልጥም:: በኢትዮጵያ የምድር ውስጥ ዋሻ በመደበቅ ምርምራችንን የምናካሂደው እንደ ፍልፈል ራሳችንን ከሁሉም ነገር ሰውረን ፀሐይና ዝናብ ሳናይ ነው:: ራሳችንን ሰውረን የምንገኝ በመሆናችንም የገንዘብ ማግኛ ዘዴያችንም ሕጋዊ መሆን አይችልም::

በርግጥ ገንዘብን በተመለከተ ራሳችን የፈጠርነው የገንዘብ ማምረቻ የተለያየ ተቋም አለን:: ተቋማችን ዘርፈ ብዙና በጠንካራ ሠራተኞች የተመሠረተ በመሆኑ ሥራችንን እስከምናጠናቅቅ የገንዘብ ችግር





ይገጥመናል የሚል ስጋት የለኝም:: ለተቋሙ ጥሬ እቃዎቹን እንደ ልብ ለማግኘት የኢትዮጵያ ሁኔታ የራሱ የሆነ አስተዋጾ እንደአለው ሳልጠቅስ የማላልፈው ጉዳይ ነው:: በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሁኔታ አመቺ ነው ስል ለመግለጽ የፈለግሁት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ሰው ለቁስ ነገር ያለውን ጥመኝነት ለመግለጽ ነው:: ከምሁር እስከ ባለ ሥልጣን ብንመለለከት ከሰው ልጅ ይልቅ ለቁሳቁስ ቅድሚያ የሰጠ በመሆኑ በቀላሉ ገንዘብና ቁሳቁስ እያሳዩ የፈለጉትን ማግኘት ይቻላል::" አሉ ፕሮፌሰሩ እንግዳውን እየተመለከቱ::

"ከኢትዮጵያ የምታገኙት ጥሬ ዕቃ አለ ማለት ነው? ካለስ ምንድነው?" እንግዳው ምሁር መልሱን ለመስማት ተቁነጠነጠ::

"ከሰው ጀምሮ ሁሉንም ነገር በቀላሉ ወደ ገንዘብ ቀይረህ መጠቀም ትችላለህ:: ተቋማችን የሰውን የውስጥ አካል ለመለዋወጫነት በድብቅ ወደ ውጭ እየላከ ነው:: ይህንን የሚሠሩ አካላትም ተመድበዋል:: ወደ ገንዘብ ለውጠን ከጥቅም ላይ ካዋልነው በተጨማሪ በሺህ ኪሎ ግራም የሚቆጠር አልማዝና ወርቅ በእጃችን ላይ ይገኛል:: ከወርቁ በተጨማሪም ሌሎች የገንዘብ ማግኛ ዘዴያችን የሐሰት ዶላር ማዘጋጀት ነው:: የአሜሪካንን ዶላር እያስመሰለ የሚሠራ ሰው አዘጋጅተን በቀን ብዙ ሚሊዮን ተመሳሳይ ወረቀቶችን እያመረተልን ይውላል:: ንጹሑን ወረቀት በቀለም ውስጥ ነክሮ መልሶ ሲያጥበው የአሜሪካ ዶላርን መስሎ ይወጣል:: አንዳንድ ግለሰቦች ሐሰተኛውን ዶላር በእውነተኛ የኢትዮጵያ ብር ለመለወጥ ትንሽ እንኳን ሳያቅማሙ ይፈጽሙታል::"

"ዶላሩ ሲተሻሽ ወደ ወረቀት አይለወጥም ማለት ነው:: ማለቴ ዶላር እንደሆነ ይቀጥላል?"

ወረቀቱ በብርነት የሚቀጥለው ለተወሰኑ ደቂቃዎች ከበዛም ለሰዓት ብቻ ነው:: ከዚያ ወደ ወረቀትነት ይለወጣል:: እኔ የቀመስኩትን ሌላው ይቅመስ በማለት አለዚያም ከሕግ ተጠያቂነት ለማምለጥ በደላቸውን ችለው ይቀመጣሉ:: እንጂ አይተነፍሱም::

እንደ ደላላ ሆኖ የራሱን ጓደኛ በማምጣት የሱን ኪሳራ ያቀምሰዋል:: ልብ ለልብ ስለሚግባቡም ፍንጭ ላለመስጠት ይጠነቀቃሉ:: በዚህ የተንኮል አካሄዳቸውም ሁሉም ነገር ተሸፋፍኖ ምሥጢር እንደሆነ ነው የሚቀጥለው::"

ምሁሩ ሁሉንም ነገር ሲያዳምጥ ከቆዩ በኋላ ቦርሳውን ከፍቶ መጽሐፍ ቅዱስ በማውጣት መጽሐፈ ሄኖክ ላይ ያለውን ቃል መመልከት ጀመረ:: ተመራማሪዎቹ ለመሳቅ ቢከጅላቸውም አልሳቁም:: የሕፃን መሳይ አስተሳሰቡ ከማስገረም አልፎ አሳዝኗቸዋል:: ከአቀረቀረበት አንገቱን ቀና አድርጎ በጥንቃቄ እየተሿሿረ ተመለከታቸው:: የሁሉም እይታ ከላዩ ላይ ነው ያለው::

በመጽሐፈ ሄኖክ ያሉትን አሥራ ስምንት ሰዎችና አሁን ከፊቱ የተቀመጡትን አሥራ ስምንቱን ተመራማሪዎች እያነፃፀረ መናገር ስለጀመረ አእምሮው የተነካ ወፈፌ መሆኑን አረጋገጡ፡፡ በነሱ መካከል ያለው ልዩነት የዘመን ርቀት ካልሆነ በቀር በእሱ ግንዛቤ ተግባራቸው አንድ ነው፡፡ እነሱ የተሰማቸው ባይገባውም በራሱ ትክክል ነበር፡፡

እንደሞኝ ቆጥረውት ዝም ብለው እደሚያዳምጡት ቢገባውም ግድ አልነበረውም፡፡ በነሱ መንገድ ሞኝ ሊሆን ይችላል፡፡ እየሠሩት ያለውን ጥፋት ሊያልፋቸው አይችልም፡፡ በዚህ ውስጥ የመጀመሪያው ግንባር ቀደሙ ሰው እሱ ራሱ ቢሆንም እጁን አውጥቷል፡፡ ከአሜሪካን መንግሥት ፈቃድና ድጋፍ አግኝተው የጀኔቲክ ምርምር ተቋሙን በሚጀምሩበት ወቅት ደስተኛ የነበረው ራሱ ነበር፡፡ ይህንን እውነታ ቢጠየቅ አይክድም፡፡ የአሜሪካን መንግሥት ተቋሙ እንዲቋረጥ ተመራማሪዎቹም ሀገር ጥለው እንዲሰደዱ ሲፈርድባቸው ተሰደደ፡፡

ይህ ለሱ በወቅቱ ያሳዘነው መርዶ ነበር፡፡ አሁን ግን እንዲህ ያለ ስሜት አይሰማውም፡፡ ምርምሩ በነበረበት ቀጥሎ ቢሆን ኖሮ እንደ ሰዶምና ገሞራ ሰዎች የጥፋት ተጠያቂ በሆነም ነበር፡፡ በአሜሪካን መንግሥት የቀጥታ ትእዛዝ በይፋ ከተዘጋ በኋላ ወደ ሶቭዬት ሕብረት ሞስኮ ሲሄድ ባልደረቦቹም በዋሽንግተን ቀይተው ከሁለት ዓመት በኋላ ጉዞዋቸውንና ዓይናቸውን ወደ ኢትዮጵያ አደረጉ፡፡

እሱም ሁሉንም ነገር እርግፍ አድርጎ በመተው መጽሐፍ ቅዱስን መከታተል ጀመረና እራሱን ለፈጣሪ ስራ ማስገዛት ተቀዳሚ ተግባሩ ሆነ፡፡ መክብብ እንደተናገረው መሆኑ ነው፡፡ "ሁሉም ነገር የከንቱ ከንቱ ነው" በራሺያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የስብከተ ወንጌል ኃላፊና መምህር ከሆነ በኋላ ምርምሩን አቋርጦ ሲሰደድ የተሰማው የመረረ የሀዘን ስሜት በፈጣሪ ቅዱስ ቃል ተጠገነለትና ከኃዘኑ ተፈወሰ፡፡

"የሰው ልጆች ከበዙ በኋላ እንዲህ ሆነ፡፡" የመጀመሪያውን የመግቢያ ሐረግ ሲጨርስ ቀና ብሎ የምርምር ባልደረቦቹን ተመለከታቸው፡፡ በማዘን አለዚያም በትዝብት እየተመለከቱት ነበር፡፡ ጭንቅላቱን በማዘን እየነቀነቀ ንባቡን ካቆመበት ቀጠለ፡፡

"የእግዚአብሔር ቁጣ ገንፍሎ በምድር ላይ የጥፋት ውኃ እስከፈለሰበት ጊዜ ድረስ ጥፋቱም እንደቀጠለ ነው የቆዬው፡፡ የዚያ ዘመን ተመሳሳይ የሆነ ምርምር በዚህ ቦታ እየተደረገ ሳየው ያ ጥፋት ስለታወሰኝ ነው ታሪኩን ልነግራችሁ የፈለግሁት፡፡ በርግጥ እኔ ስናገር የምታደምጡኝ የምነግራችሁ ታሪኩ ስሏችሁ ሳይሆን ሞኝነቴ ደንቋችሁ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ዋሻ ውስጥ የፈጠራችሁት ግኝታችሁ ለዚህች ዓለም የመጨረሻ ጥፋት ሊሆን እንደማይችል ምን መተማመኛ ይኖራችኋል?" ያሰበውን አልጨረሰም፡፡

ፕሮፌሰሩ አቋረጡት "ለዚህ ምርምር የመጀመሪያው ሰው





መሆንክን የዘነጋህ መሰለኝ" እጃቸው ተንቀጠቀጠ፡፡ ሽማግሌው፡፡

"አሁን ግን አይደለሁም የምናገረው ትናንትን ሳይሆን ነገን ከዛሬ ጋር እያመዛዘንሁ ነው ይህ በእናንተ አመለካከት ተራ ሊባል የሚችል መሆኑ ይገባኛል፡፡ ጥፋተኛ መሆናችሁን ተረድታችሁ እንድትቀጥሉ እውነቱን ልነግራችሁ እንጂ እናንተን መክሬ ለመመለስ ይሳካልኛል የሚል እምነት ኖሮኝ አይደለም የምናገረው፡፡

ምርምራችሁን በዚህ ለማድረግ ፈልጋችሁ ወይስ አጋጣሚ የፈጠረው ነው፡፡ በርግጥ በሌላው የሰለጠነው ዓለም ተቀባይነት ስለአጣችሁ ኢትዮጵያን እንደመሸሸጊያነት መርጣችኋት ሥራችሁን ቀጥላችሁ ይሆናል፡፡ እኔ ግን እንደ አጋጣሚ አልወሰደውም፡፡ ምናልባትም በዚህ ሥራችሁ ውስጥ ያላወቃችሁት አንድ ኃይል ይህንን ቦታ ለምርምራችሁ ልዩ ስፍራ አድርጎ አዘጋጅቶላችኋል የሚል ግምት አለኝ፡፡ ለምን ብላችሁ እንዳትጠይቁኝ፡፡"

ምሁሩ ከመጽሐፍ ቅዱስ እያጣቀሰ የጀመረውን ገለፃ እንደጨረሰ በረጅሙ ተነፈሰና ከወንበሩ ላይ ተስተካክሎ በመቀመጥ የጥንት ባልደረቦቹን ተራ በተራ መመልከት ጀመረ፡፡

ሰረቅ እየተደራረጉ ይተያዩ ስለነበር እርስ በርስ የሚሳሳቁም መሰለው፡፡ ትንሿን የስብሰባ አዳራሽ እስጨንቆ ሊያፈነዳት የደረሰ ረጅም ጸጥታ ስለነገሰ፡፡

ተመራማሪዎቹ አንገታቸውን አቀርቅረው በዓይናቸው ወለሉን እያሰሱ እጅግ ብዙ ደቂቃዎችን በጸጥታ አሳለፉ፡፡

ጊዜው በዚህ መልኩ እየተሽቀዳደመ ቢሆንም ከተመራማሪዎቹ አንዳቸውም ለመልስ የሚሆን ማብራሪያ ለመስጠት አልደፈሩም፡፡

ሁሉንም ሲመለከታቸው ቆየና አንገቱን በዝግታ እየነቀነቀ በትዝብት ዓይነት ተናገረ፡፡

"እያልኩ ያለሁትን የሰማችሁ አልመሰለኝም፡፡ በፍፁም እያዳመጣችሁኝ አይደላችሁም" ተራ በተራ እየተመለከታቸው ቅሬታውን ሲገልጽላቸው በመሰራረቅ እርስ በርሳቸው ተያዩ፡፡

አድራሻውን አፈላልገው እንዲመጣ ያደረጉት እነሱ ቢሆኑም ከዶክተሩ በስተጀርባ ኢንተርፖል ስላለመኖሩ ማረጋገጫ አልነበራቸውም ሊኖራቸውም አይችልም፡፡

"እኔ በበኩሌ" አሉ ፕሮፌሰሩ "እኔ በበኩሌ መስማት ያለብኝን ያህል ሰምቼሃለሁ፡፡ መስማት ብቻ ሳይሆን ለምን እንደምትናገርና ለማን እንደምትናገር፣ የነማንን ተልዕኮ ልታስፈጽም የመጣህ መሆንክን ጭምር ተረድቻለሁ፡፡ የተናገርከው አንተ ብትሆንም የንግግርህ ቃል ባለቤት ሌላ መሆኑን ነው የሚጠቁመው፡፡ የምትለው ሁሉ ከአንተ ልብ የመነጨ አይደለም፡፡ እቅዱን ሌሎች አወጡት አንተ በዚህ ቦታ ተገኝህና የነሱን የልባቸውን አሳብ አስተላለፍክላቸው፡፡ ከሰማሁት ማብራሪያህ የተረዳሁት

ቢኖር ይህንን ነው:: በቃ እኔ እንደተረዳሁት ከሆነ መቋጫው ይሄው ነው::

ይህ ሁሉ ዳር ዳርታ ለዚህች ዓለም ሕዝቦች የታሰበ በጎ ምግባር ሳይሆን የእኛን የተሳካ ሙከራ ለማጨናገፍ የተደረገ የተንኮል ሴራ ነው:: ልነግርህ የምፈልገው ውጤቱ አንተ ከምትለው በላይ ችግር ቢፈጥርና ጥፋትን የሚያስከትል ቢሆንም ምርምሩ በጀመረበት የሚቀጥል መሆኑን ነው::

ሊከሰት ይችላል የምትለው አደጋ የሰው ልጆች አሁን እያስተናገዱት ከአለው መከራና ስቃይ የከፋ ሊሆን አይችልም:: የምትናገረውን ስሰማ የቀድሞ አንተነትክን እስከመጠራጠር ደርሻለሁ:: የምርምሩ ዲዛይንና ንድፍ አውጭ የአጠቃላይ ጽንሰ ሃሳቡ አመንጭ አንተ ነበርክ:: የዚህ ሁሉ ባለቤት ራስህ መሆንክን እንዴት ዘነጋኸውና መልሰህ አውጋዥ ልትሆን ቻልክ? ይህ የማይታመን ቀልድ ነው::

የአሜሪካን መንግሥት በዓለም ዙሪያ ያለውን ነቀፋ በመፍራት ምርምሩ እንዲቋረጥና ተቋሙ እንዲዘጋ በወሰነበት ወቅት በመበሳጨትህ አልነበረም ወደ ሶቭየት ሕብረት ለመኮብለል የተገደድከው? ፕሮጀክታችን በዚህ መልክ ሲዘጋ ተንሰቅስቀህ አልቅሰህ ነበር:: ከዚህ ሁሉ በኋላ ምን ቢሰማህ ነው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ሰባኪ ሆነህ አህጉር በማቋረጥ ከተደበቅንበት ስፍራ ድረስ ዘልቀህ ልታጨናግፈን የምትሞክረው:: በዓለም ዙሪያ ታስሰን አድራሻችን በመጥፋቱ ግንኙነት ሊኖረው ይችል ይሆናል ብሎ በማሰብ ኢንተርፖል የአንተን ዱካ ሲከታተል ቆይቷል ማለት ነው:: ምንም ይሁን ምን የአንተ አመጣጥ ከዚህ ውጭ ሊሆን አይችልም በርግጥ አድራሻህን ፈልጌ የጠራሁህ ራሴ ነኝ:: ያ ማለት አንተን ከኢንተርፖል ጋር ግንኙነት ይኑርህ አይኑርህ ማረጋገጫ የለንም:: አይኖረውም ብሎ መደምደም አይቻልም::

ወደዚህ ለመምጣትህም ሆነ ይህንን ተቋም ለማየትህ ብቸኛው ተጠያቂ እኔ እራሴ እንጂ አንተም ሌሎችም አይደሉም:: ስለጠራሁህ ብቻ እኛን ከሚያድኑን ወገኖች ጋር ግንኙነት የለህም ብሎ ለማመን የማይታሰብ ጉዳይ ነው:: እያሳየኸን ከአለው ለውጥ ስመለከተውም ከበስተጀርባህ ሌላ ኃይል መኖሩን በግልጽ ተረድቻለሁ:: የሚገርመው የቀበሮዋን ተረት በመድገም የመጽሐፍ ቅዱስ ስብከት ይዘህ እኛን ለማሳመን ያደረግኸው ከንቱ ብህትናህ ብቻ ነው:: ለማያውቅሽ... ምንድነው... የሚል የኢትዮጵያኖች አባባል አለ:: የበፊት አቋምህን ስለማውቀው የአሁኑ ለውጥህ የሚጠቁመኝ በሰው ልጅ መከራ እየቀለዱ መኖርን የሚፈልጉ ኃይሎች ከበስተኋላህ እየተከተሉህ አድርገውሃል:: ወደዚህ ስጠራህ ይህንን ባለማሰቤ ሲበዛ ጅላጅል ነኝ::

አሁን ያየሁትን አስተሳሰብክን ይዘህ ትመጣለህ ብዬ አስቤ ስላልነበር መሰለኝ የተጃጃልኩት አለዚያም እያረጀሁ መሆን አለብኝ:: ያም ሆኖ





በአንተ ላይ ለሚደርሰው ማንኛውም ችግር ከሕሊና ወቀሳ የነፃሁ መሆኔን እዚህ ያሉት ባልደረቦቼም እንዲገነዘቡልኝ እጠይቃለሁ:: በሌላ በኩል በአሁኑ ሰዓት ከአንተ የምፈልገው እውነቱን እንድትነግረኝ ብቻ ነው::”

ዶክተሩ ትዕግስቱ መሟጠጡን በሚገልጽ እኒኒን እጁን አነሳ:: “ሁሉም ግምትህ ትክክል አይደለም:: ይህንን ምርምር ለመሥራት ስለነበረኝ ጉጉት የሰጠኸኝ አስተያየት ትክክል ነው:: አዲስ ሰው የመፍጠር ጉጉት ያደረብኝ የመጀመሪያው ሰው እንደ ነበርሁ የማይካድ ሃቅ ስለሆነ ውሸት ነው ልልህ አልችልም:: ማንኛችንም ብንሆን ትክክል መስሎን እንጀምራለን ያለመሆኑን ስንረዳ የመተው ሥልጣኑ አለን:: ለሰው ልጆች የማይጠቅም መሆኑን ዘግይቼ ስረዳ የነበረኝን ሃሳብ ሰረዝሁ:: በእኔ እምነት ያ ዘመን በሙሉ የባከነ ጊዜ ነው:: አንድ አሳብ ትክክል አለመሆኑን በተረዳንበት ጊዜ ለመለወጥ የመወሰን የሕሊና ዳኝነት አለብን:: እናንተን ይቅርታ ሊያስጠይቀኝ የሚችል ሥራ ስላልሠራሁም ይቅርታ አልጠይቅም:: አሳብክን ያስለወጠህ ኃይል አለ ለምትለው በእርግጠኝነት እናገራለሁ አሳቤን እንድለውጥ ያደረገኝ ወይም የጠየቀኝም ሆነ እናንተን አድኖ ለመያዝ እኔን ከፊት አስቀድሞ የተከተለኝ ማንም የለም:: እንደ ማንኛውም ሰው ስለማስብ ማንም ሳይነግረኝና ከማንም ትእዛዝ ሳይሰጠኝ በራሴ ውሳኔ አሁን የነገርኩህን እርምጃ ወስጃለሁ:: በራሴ ሕሊና መሪነት ይሆናል ብዬ ያላመንኩበትን አይሆንም ብዬ ለመወሰን ማንም እያስገድደኝም:: ያስገደደኝም ማንም ኃይል አልነበረም:: ሊኖርም አይችልም:: እውነቱን ንገረኝ ብለኸኛል:: እውነታው ይኼ ነው:: ስንሰደድ በቀጥታ የገባሁት በራሻ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ምርምር ክፍል ውስጥ ስለነበር ስለተጨባጩ ሁኔታ ተረድቼ መጥፎ ተግባሬን እንድቀይር ረድቶኛል:: መጽሐፍ ቅዱስን እያጠናሁ ለአራት ዓመታት ያህል በራሻ መንፈሳዊ ኮሌጅ ቆይቻለሁ:: እንደ ወጣሁም በአንድ ትልቅ ካቴድራል ውስጥ የስብከተ ወንጌል አላፊ በመሆን እየሰራሁ በነበርኩበት ወቅት ነው የአንተ መልእክት የደረሰኝ:: ደብዳቤህ ሲደርሰኝ የተሰማኝ ደስታ ወሰን ስላልነበረው አንተን ፍለጋ ወደ ኢትዮጵያ መጣሁ::

‘ከበስተኋላህ ኢንተርፖል ሊኖር ይችላል’ ብለኸኛል:: መጠራጠር መብትህ ስለሆነ ለምን ተጠራጠርህ የሚል ቃል አይወጣኝም:: ለሁላችሁም የምሰጣችሁ ተመሳሳይ የሆነ መልስ ነው:: ፈልጌ አመጣሁህ ስላልከው በመፈለግህ እና ወደ ኢትዮጵያ መጥቼ ተቋሙን እንድመለከት በማድረግህ አመሰግናለሁ:: ቢያንስ ትክክል እንዳልነበርሁ መናገሬም ለኔ እንደ ሕሊና እረፍት አድርጌ ስለምቆጥረው ደስተኛ ነኝ:: ስለዚህ እኔን ወደ እዚህ በመጥራትህ ባለውለታዬ ነህ ማለት ነው::”

ፕሮፌሰሩ ከወንበራቸው ላይ ተወራጩ:: “የምትለው ሁሉ ለራስህ ትርጉም ሊኖረው ከመቻሉ በቀር ለእኔ ሊታመንልኝ አይደለም በፍጹም

እየገባኝ አልነበረም፡፡ በአንተ ላይ ያለኝ እምነት እንደ ጠቀስኩልህ ስለሆነ በፍጹም ላምንህ አልችልም፡፡ የምታደርገውን መንገታገት አቁምና እውነቱን ለመናገር እራስህን አሳምነው፡፡

እንደ ፍልፈል በጉድጓድ ብንቀበርም ስለ ጠቅላላው የዓለም የመረጃ ሁኔታ የማናውቅና የማንረዳ እንዳይመስልህ፡፡ የተባበረው የወንጀለኞች ክትትል የኢንተርፖል ስብስብ እኛን ለመያዝ በመላው ዓለም የመገናኛ መስመሩን ዘርግቶ እኛን ፍለጋ በማነፍነፍ ላይ ነው እውነታውን ለማውጣት ፈቃደኛ ስላይደለህ ከዚህ ላይ ይብቃን፡፡"

ከተቀመጡበት ተነስተው አዳራሹን ለቅቀው ሲወጡ ሲሎቹም ተከተሏቸው፡፡ በተሰጠው የመቆያ ክፍል ከሶፋው ላይ ተጋድሞ አይኖቹን እንደ ጨፈነ ከተለያየ አቅጣጫ የሚመጣ የመቀስና የሳህኖች ኳኳታ እያዳመጠ ያንጉላጅ ጀመር፡፡

ፕሮፌሰሩ ቁርስ ይዘውለት ሲመጡ ሳህንና ብርጭቆው በመጋጨቱ እሱን አድናለሁ ሲሉ ትሪው ከመሬት ላይ በማረፉ ክፍሉን በጠበጠው፡፡

"ስላስደነገጥኩህ ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡ የሸማግሌ ነገር ትሪ እንኳን ለመያዝ እየተቸገርሁ ነኝ" ሳቅ አሉ፡፡

"እንግድነቴ አስቸገረህ ያልተመቸሁ እንግዳ በመሆኔ ይቅርታ መጠየቅ ያለብኝ እኔ ነኝ፡፡" አለ ሁኔታቸውን ሲመለከት ከልቡ አዝኖ፡፡

"በፍጹም ያንን አላሰብኩም፡፡" ቅር ያላቸው መሆኑን ገለጹለት፡፡

የታገተ መሆኑን አስረድተው መውጣትና ወዴትም መንቀሳቀስ የማይችል መሆኑን ሲገልጹለት ከልብ በመነጨ ስሜት አዘነባቸው፡፡ ዶ/ር ሪቻርድ ዊነር፡፡





# ምእራፍ አምስት

በኢትዮጵያውያን አባባል "ትክሻቸውን የመጥፎ ነገር መንፈስ እየተጫናቸው" ያሉት ሳይንቲስቶች የእንግዳውን መምጣት ተከትሎ ክፉኛ ተረብሸዋል፡፡ ከሳተላይት መልእክት የሚቀበለው የመረጃ ሳጥንም ያመጣው አዲስ ዜና አለ፡፡ በልዩ ጥበብና ዘዴ በተቀበረው የመልእክት መቀበያ ማግኔት ተጠልፎ ያለ ምንም ችግር ወደ መጨረሻው ግራውንድ እንዲገባ የተደረገው ኢንተርኔት በዓለም ዙሪያ የተከናወነውን መረጃ ያለምንም ችግር ይሰበስባል፡፡ ባለ ሙያው የናሳ የጠፈር ምርምር ጣቢያ ባልደረባ የነበረ ሲሆን ተመራማሪው ናሳን ለቅቆ ከተሰወረ ከጥቂት ዓመታት በኋላ የአሜሪካን መንግሥት መሞቱን አስታውቋል፡፡

የአሜሪካን መንግሥት ዜና አገልግሎት ይህንን መግለጫ የሰጠው የኤፍ ቢ አይና ሲ አይ ኤን የመሳሰሉት ምርጥ የመረጃ ሠራተኞች መላውን ዓለም አስሰው የደረሰበትን ባለማግኘታቸው የተሰጠ የውሸት መግለጫ መሆኑን የሚጠቁሙ ፍንጮች አሉ፡፡ ጥቁር አሜሪካዊው የናሳ የጠፈር ምርምር ባለሙያ በሕይወት ስለመኖሩ የሲ.አይ.ኤ መሥሪያ ቤት በትክክል ያውቃል፡፡ በቴሌቪዥን መግለጫውን የሰጠው ናሳን ለቅቆ ተሰወረ ላለማለት ሲሆን የአንድ በድንገት የሞተ ሰው አጽምን በማሳየት የቀብር ሥርዓቱን ያሳየው የሌላ አገር የጠፈር ምርምሮች እንዳይፈልጉት የተጠቀመበት ዘዴ ነው የሚል አስተያየት ሲሰማ ቆይቷል፡፡ በርግጥ ለማደናገርያ ተብሎ የአንድ ሰውም አስከሬን በሳጥን እንደ ተቀለፈ ለሕዝብ እይታ እንዲቀርብ ተደርጐ በመረጃ መሥሪያ ቤቱ በኩል የተሰጠው ምክንያት በቂ ስላልነበር የመሞቱን ዜና ጥርጣሬ የጎላ አድርጎት ነው የቀረው፡፡

"እንግዳችን እና የቀድሞ የምርምር ባልደረባችን እንደምን አደርክ?" መነጽራቸውን ከጠረጴዛው ላይ እያስቀመጡ ጠየቁት፡፡ ፕሮፌሰሩ፡፡

"እግዚአብሔር ይመስገን ኢየሱስ ክርስቶስ ክብሩ ይስፋ" ዶክተሩ ለፈጣሪው አለዚያም ለምሁራኑ እጅ በመንሳት ተነስቶ ቆመ፡፡

"ተቀመጥ ተቀመጥ" ፕሮፌሰሩ እጃቸውን አርገበገቡና እንዲቀመጥ ጋበዙት፡፡

"ሁላችንም ብንሆን የክርስቶስ ስም በሚጠራበት ወቅት ብድግ ማለት ይገባናል፡፡ ስለሱ ክብር፡፡ እግዚአብሔር ይመስገን፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ ጌታ ነው፡፡ ይህንን ጥበብ ለሰጠን አምላክ ይህችን ቀን ለባረካት ጌታ አንድ ጊዜ ከተቀመጥንበት ተነስተን ለጉባኤያችን መሳካት እንጸልይ፡፡ ጉባኤያችንን እንዲባርክልን ፈጣሪን እንለምነው" ሁሉም ተነስተው ቆሙ፡፡

ጸሎቱ ብዙ ደቂቃን ባለመፍጀቱና ወደ መቀመጫቸው በመመለሳቸው እድለኞች እንደሆኑ ተሰምቷቸዋል፡፡ ያለ ጥርጥር ይህ ሰው የአስተሳሰብ

ምህዋሩ እየተዛባበት ነው:: በነሱ እምነት ምሁሩ የአእምሮው አንድ አካል ሥራውን አቋርጧል::

"እግዚአብሔር ይህችን ቀን ባርኳታል:: አያችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁልጊዜ እኛን ይፈልጋል..." አጠር ያለ ማብራሪያ የሰጠው ወንበሮቻቸው ላይ ከተቀመጡ በኂላ በመሆኑ ትዕግሥታቸውን አልተፈታተናቸውም::

"መኝታው እንዴት ነበር ተመቸህ?" ለመጀመሪያ ጊዜ ፊት ለፊት ገጹን እየተመለከቱ ጠየቁት ኘሮፌሰሩ::

"እግዚአብሔር ይመስገን:: በጣም ነው የተመቸኝ:: አምላካችን ባለበት ስፍራ ሁሉም ነገር ምቹ ነው:: ክርስቶስ ሲያጽናናኝ ነበር ያደረው:: እሱ ያሳለፈውን መከራ እየነገረኝ ነበር::"

"በአሁን ሰዓት የምናደርገው ውይይት በሁላችንም ሕይወት ውስጥ ትርጉም ስላለው በጥሞና መነጋገር ይኖርብናል:: አንተን በተመለከተ ብዙ ጥያቄዎች አሉን:: እንዳልከውም ሌሊቱን ሙሉ ያሳለፍከው ከእግዚአብሔር ጋር ከሆነ ሁሉንም ጭንቀታችንን ይገልጽልሃል የሚል እምነት አለኝ"::

በምጸት ይሁን ከልባቸው በውል ባይገባውም ለኘሮፌሰሩ አባባል በቅን መለሰ::

"ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሊባርከን ወደኛ መጥቷል::" አይኖቹን ወደ ጣራው አቅንቶ መናገር በመጀመሩ እርስ በርሳቸው በመተያየት ተጠቃቀሱ::

"እንደሱ አይደለም ዶክተር:: ትንሽ የለቀቅህ ይመስለኛል:: አንጎልህ በትክክል መልእክት እያስተላለፈና እየተቀበለ አይመስለኝም... ፊትክን መልስና እኔን ተመልከተኝ:: ወደኔ ተመልከት ጤንነትህ የተጓደለ ይመስለኛል:: ጓደኞቼም እንደዚሁ ሳያስቡ አልቀሩም:: እባክህ ፊትህን ወደኔ መልስ..." የፌዝ በሚመስል ቅላፄ የተናገሩት ኘሮፌሰሩ::

"ልክ ነኝ ኘሮፌሰር አንጎሌ በትክክል እየሠራ ነው:: በአሁን ሰዓት አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እየጐበኘን ይገኛል::"

ምሁራኑ የዶክተሩ የአንጐል ክፍል የተወሰነው የሆነ ነገሩ እንደተቃወሰበት ማረጋገጣቸውን ለመተማመን በድጋሜ በፈገግታ ተያዩ::

"እግዚአብሔር ከዚህ ድረስ ሊመጣ አይችልም:: እኛ እኮ ያለነው በከፍተኛ ጥልቀት ውስጥ ነው:: በጣም ልቀት ባለው ስፍራ ነው የምንገኘው ክርስቶስ በዚህ ጥልቅ ቦታ እኛን ለመጎብኘት ሲል አይገኝም::"

ይህንን የተናገረው እስራኤላዊው ተመራማሪ ነበር:: አነጋገሩ የፌዝ መሆኑ ስለገባው ተበሳጨ ዶክተሩ::

"የጥልቁ ክብደት እንደሱ ላለው ጀግና ምኑም አይደለም:: ለፈጣሪ ወሰን ዳርና ድንበር አልተበጀለትም:: ጥልቅ አያግደውም:: ክብር ለሱ ይሁን:: አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በላይ በሰማይ በታች በጥልቁ እንደሚኖር አባታችን ነብዩ ዳዊት ተናግሮታል::" ከመቀመጫው ተነሳ ዶክተሩ::





"እምን አያግደውም:: ጀግናም ነው:: ግን ያለንበት ስፍራ በጣም ጥልቀት ስላለው ወደዚህ አይመጣም ለማለት ነው::"

በስሜት እየተወራጨ ኘሮፌሰሩ የተናገሩትን የድፍረት ቃል በመቃወም በክፍሉ ውስጥ እየጮኸ መናገሩን ቀጠለ:: ከመጠን ባለፈ ስሜት ተውጦ እንደ ቆሰለ አውሬ በመቅበጥበጥ ሰላማቸውን ስለበጠበጠው የሚላቸውን ለመቀበል እርስ በርሳቸው በዓይን ጥቅሻ ተነጋገሩ:: እንደዚያ ካላደረጉ እብደቱ ይብስበትና ነገሩ መቋጫ ሊጠፋለት ነው:: በተለይም እስራኤላዊው በጥላቻ እየተመለከተው በነበረበት ወቅት ኘሮፌሰሩ ደገሙት::

"ንስሐ መግባት ያስፈልጋል:: የክርስቶስን ክብር በዋዛና በፌዝ መጥራት ትልቅ የሆነ መቅሰፍት ነው:: ፍጻሜው ተቃርቧል:: መንግሥቱ ደርሳለች:: በድፍረት እያናገራችሁ ያለው በውስጣችሁ የሰረጸው የአውሬው መንፈስ ነው" አመልካች ጣቱን ወደ እስራኤላዊውና ኘሮፌሰሩ በመቀሰር የበቃውን ያህል ሲደነፋ ቆይቶ ወደ መቀመጫው ተመለሰ::

"የመጡ አዳዲስ መረጃዎች ካሉህ ብትነግረን መልካም ነው:: በእንግዳችን በኩል አንዳንድ ስጋት ስላደረብን ነው እየተወዛገብን ያለነው የሁላችሁም የስጋት ስሜት ከኔ የተለየ ይሆናል የሚል ግምት የለኝም::"

ሁሉንም በዓይናቸው ዳሰሷቸው:: ኘሮፌሰሩ::

ኢንጂነሩ መልስ ከመስጠቱ በፊት ከሳተላይት የተቀበላቸውን መረጃዎች ማስታወሻውን ከፍቶ ለትንሽ ጊዜ ማየት ነበረበት:: በጥንቃቄ ሲመረምር ቆይቶ ዜናውን ረጋ ብሎ እንደሚከተለው መልኩ ማቅረብ ጀመረ::

"ከወትሮው በተለየ በትናንትናው ምሽት በርከት ያሉ መረጃዎችን ለመጥለፍ ችያለሁ:: በሳተላይት የተላለፉት ዜናዎች ስለ አዲሱ እንግዳችንም መጠነኛ የሆነ ዘገባ ነበራቸው::"

የባለ ሙያውን ትንታኔ በትዕግሥት ይከታተሉ የነበሩትን የቀድሞ ባልደረቦቹን ለማየት ቀና አለ እንግዳው ምሁር:: 'በከንቱ የሚደክሙ ባተሌዎች' እያለ ስለነሱ ከንቱነት በማሰብ ላይ እንደነበር የሳተላይት ባለ ሙያው 'በእንግዳችን በኩል' የሚለውን ሐረግ ሲናገር ከጆሮው በመግባቱም:: "በእኔ በኩል ምን?" እራሱን ጠየቀ:: በዚህ ዙርያ ከደሙ ንጹህ ነኝ:: እነዚህ ሰዎች በተለያዩ ዘዴዎች እየተጠቀሙ በኔ ላይ ምርመራ ጀምረዋል:: እውቀታቸውን ሊጠቅም በሚችል ተግባር ላይ ቢያውሉት እንዴት መልካም በሆነላቸውም ነበር:: በረጅሙ ተንፍሶ ያዳምጥ ጀመር::

የትንቢቱን መፈጸሚያ ተግባር እያከናወኑ ያሉ ከንቱዎች ናቸው:: ትልቅ ስህተት ነው:: ባልሆነና በማይጠቅም ነገር ላይ እንድትደክሙ እግዚአብሔር የፈጠራችሁ ከንቱዎች::

"መንፈሳቸው ወደኛ አቅጣጫ የሚያነጣጥር ይመስልሃል?" የጀመሩትን ሳይጨርሱ ወደ እንግዳው ዓይናቸውን ወረወሩና በጥንቃቄ ተመለከቱት::

"የቀስታቸው ጫፍ ወደ እኛ አቅጣጫ የተነጣጠረ ይመስለኛል:: እንግዳችንን በተመለከተም የት እንዳለ በትክክል ባይረዱም ከመነሻው

ጀምረው ተከታትለውታል። በርግጥ በአሁን ሰዓት የት እንዳለ በትክክል ስፍራውን ያወቁ አይመስለኝም። ዜናው እንደሚለው ከኢንተርፖሎች እይታ የተሰወረው ከዚህ ሕንፃ ከመግባቱ በፊት ነው።"

"አልገባኝም?" አለ እንግዳው "ስለምንድነው የምታወራው?" ግራ በመጋባት እየተመለከተ ኢንጂነሩን ጠየቀው ዶክተሩ።

"የሚያሰጋህ ስለ ሌለ አትደናገጥ። የአንተ ድርሻ እኛ የምንነግርህን ማዳመጥ ብቻ ነው። ከአሜሪካን ስትነሳ ጀምሮ የኢንተርፖል አባሎች ልዩ ክትትል አድርገውብህ እስከ ኢትዮጵያ ተከትለውህ ሸራተን አልጋ ስትይዝም አብረውህ ይዘዋል። ከሸራተን በመውጣት አልባሌ ሆቴል አልጋ ስትይዝ ከኢንተርፖል የጸጥታ ሠራተኞች ክትትል ልትሰወርባቸው እንደቻልክ በተላለፈው ዜናቸው ላይ ገልጸዋል። ስለ አንተ ዝርዝር ሁኔታ የዘገቡት እስከ እዚህ ድረስ ያለውን ሂደት ብቻ ነው።"

"አልገባኝም።" አለ ዶክተሩ "እንዴት ሊከታተሉኝ ቻሉ?" ግራ በመጋባት ሁሉንም እየተመለከተ ስሜታቸውን ለማጥናት ሞከረ።

"የዚህ ምርምር የቀድሞ ዲዛይነር ባለቤት ስለነበርህ ሊሆን ይችላል ክትትል ያደረጉብህ። ምናልባትም እየተከታተሉህ ኖረዋል። በአሁኑ ሰዓት የአንተ በእምነት ሥራ ላይ መጠመድ ለነሱ እንደ ሽፋን ነው የሚቆጠረው።" አይኑን ከሱ ላይ ነቅሎ የባልደረቦቹን ፊት ተመለከተ ኢንጂነሩ።

"ዝም በልና አዳምጥ። ጣልቃ እየገባህ አታደናቅፈው። ጉዳዩ ለእኛ እጅግ አሳሳቢያችን በመሆኑ በትክክል መስማት እንፈልጋለን።" አሉ ፕሮፌሰሩ።

የሁሉም ፊት እንደ ተኮሣተረ በማየቱም አንዳች ፍርሃት ውስጡን ሲያቀዘቅዘው ተሰማው።

"ከአሁን በኋላ ጣልቃ እንዳትገባ!" ፕሮፌሰሩ ጣታቸውን ቀስረው አስጠነቀቁት።

"በራሴ ጉዳይ ማን ይጠይቅልኝ ታዲያ?" አለ ግራ በመጋባት።

"በተጠየቅህ ጊዜ ትናገራለህ" አሜሪካዊው ተመራማሪ በኃይለ ቃል ጣልቃ ገብቶ በመናገሩ ጀርመናዊው ለመገሰጽ ሞከረ።

"እናንተ ባሳችሁ እኮ ለምን አንድ ሰው ብቻ አይናገርም?" አለ ቻይናዊው።

"የሀገር ውስጥ ደኅንነት መሥሪያ ቤቱ ባለ ሥልጣን ከኃላፊነቱ መነሳቱን የኢትዮጵያ መንግሥት መግለጫ ሰጥቷል።" አለ ኢንጂነሩ።

"በጣም የሚገርም ነገር ነው። የደኅንነት መሥርያ ቤቱ ከነበረበት የኃላፊነት ቦታ ለቀቀ ነው የምትለኝ?" ሽማግሌው ቆዳቸው የበለጠ ሲሸበሸብ ፊታቸው አመዳማ ሆነ።

"የኢትዮጵያ መንግሥት የደኅንነት መሥርያ ቤቱን በድንገት አንስቶ ወደ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ቢሮ ያዛወረው በደኅንነት ቢሮው ውስጥ ያሉትን ወዳጆቻችንን ደርሰባቸው ሊሆን ይችላል። በአሸባሪዎች ሰበብ ከኃያላን





የጸጥታ ባለሙያዎች ጋር ለማቀራረብ የኢትዮጵያ መንግሥት ከፍተኛ ጥረት ላይ ነው ያለው።"

ከኃያላን የጸጥታ ሠራተኞች ጋር በጥምር ለመሥራት የአሜሪካንን መንግሥት ድጋፍ እንደጠየቀ ቀደም ሲል ጠቅሰህልኝ ነበር" ፕሮፌሰሩ አሩ-ቅ እያሰቡ መለሱለት።

"ልክ ነው ፕሮፌሰር። የዓለም ኃያላኑ መረጃዎቻቸውን በሰበብ ወደ ኢትዮጵያ እያስገቡ መሆናቸውን የተቀበልኩት መረጃ ይጠቁማል። "ኢንተርፖል" በዜና ዘገባው የጠቀሰውም ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በስፋት እየሠራ መሆኑን ነው።"

"እንደ ሽፋን የተጠቀሙበት የዜና ዘገባ የትኛውን ነው? ማለቴ ቀጥታ ጉዳዩን ጠቅሰው ለኢትዮጵያ መንግሥት ገልጠውለታል እንዴ?" አሉ ፕሮፌሩ።

"የመረጃ ሠራተኞችን ወደ ኢትዮጵያ የላኩት ተሰውረውብናል የሚሏቸውን ዜጎቻቸው የት እንደ ደረሱ ከኢትዮጵያ መንግሥት በኩል በቂ የሆነ መረጃ በማጣታቸው ይመስላል። ኢንተርፖል የተሰወሩት ግለሰቦች ሁኔታ ከበስተጀርባው ምሥጢር ሊኖረው እንደሚችል ለኢትዮጵያ መንግሥት መግለጹን አስታውሷል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዓለም ዙርያ ትኩረት የተሰጠበት ዜና የተለያዩ አገራት ዜጎች ኢትዮጵያ ውስጥ ከገቡ በኋላ ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ በድንገት እየተሰወሩ የደረሱበት ስለመጥፋቱ ነው። በተለይም አሜሪካና እንግሊዝ በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ጫና ለማሳደር በመጣር ላይ ናቸው። ለኢትዮጵያ መንግሥት ራስምታት በመሆን ባልታሰበና ባልተጠበቀ ሁኔታ የፖለቲካውን ምህዋር ወደ እነሱ አቅጣጫ ለማዞር ማስጠንቀቂያ ጭምር በመስጠት ላይ እንደሚገኙ መረጃው ይጠቁማል። የጥንት ወዳጅነታቸውም ቢሆን በቀደመው መልኩ አይደለም ያለው። የኢትዮጵያ መንግሥትም ጫና ስለበዛበት ይመስላል ለመረጃ ሠራተኞቻቸው አገሩን ክፍት አድርጓል። ይህ ችግር እንዳለም የኢትዮጵያ የደኅንነት መሥርያ ቤትም በሙስና ተከስሶ ዋናው የእዝ መምሪያው ወደ ጠቅላይ ምኒስቴር ቢሮ እንዲዛወር ተደርጓል። መረጃው ይህንን ይበል እንጂ እውነታው. . . ።" አንጠልጥሎ ተወው።

"እውነታው ስትል?" ፕሮፌሰሩ መነጽራቸውን አውልቀው በሞጨሞጩ ዓይኖቻቸው ኢንጂነሩን ተመለከቱት።

"የመረጃ መስርያ ቤቱ በሙስና ጨቅይቷል ተብሎ መከሰሱን ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ የትኛውም የመንግሥት መሥርያ ቤት ከሙስና የጸዳ ያለመሆኑን በመንግሥቱም ሆነ በዓለም ህዝብ የአደባባይ ምሥጢር ሆኗል። ቱባ ቱባ ባለ ሥልጣናቱ እንደ ውቅያኖስ ሙስናን እየዋኙበት እያሉ የጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ በድንገት ተነስቶ ሙስናን እንደ ሰበብ በመጠቀም የደኅህንነት መሥሪያ ቤቱን ከነበረበት አንስቶ በራሱ ስር ማድረጉ ለማንም የማይታመን ቀልድ ነው።" ትንሽ እንደማሰብ ብሎ ቀጠለ ኢንጂነሩ።

"የኢትዮጵያ መንግሥት የመረጃና የደኅንነቱን መሥሪያ ቤት የማዘዣ ጣቢያው ወደ ጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ እንዲዛወር ማድረጉ ብቻ ሳይሆን የተደረገው ስር ነቀል ለውጥ በራሱ ብዙ ጥርጣሬን ያጭራል። ይህ ዓይነት ስር ነቀል ለውጥ ምናልባትም በደህንነትና በኤምግሬሽን መስርያ ቤት ውስጥ ያሉትን የእኛን ወዳጆች ስለ ደረሰባቸው ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አሳድሮብኛል። እንደዚያ ከሆነ ደግሞ..." ንግግሩን ገታ አድርጐ ሁሉንም ተመለከተ ኢንጂነሩ።

"እንደዚያ ሊሆን አይችልም።" መነጽራቸውን መልሰው በማጥለቅ አጮልቀው ተመለከቱት።

"እየሆነ ይመስለኛል። በምሥጢር ይዞት ካልሆነ በቀር የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት እውነተኛውን ጉዳይ ደርሶበታል።" አለ ኢንጂነሩ።

"እንዴት እንዴት? እስቲ በደንብ ዘርዝረህ አስረዳኝ" ፕሮፌሰሩ ጆሮአቸው ብቻ ሳይሆን አፋቸውም በስሜት ተከፍቶ የበለዙ ጥርሶቻቸው ወደ ውጭ ሲፈጥጡ ሞጭሟጫ ትናንሽ ዓይኖቻቸው ከጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ እንደቀረ ጭላጭ ውኃ በርቀት መታየት ጀመሩ።

"በአገር ውስጥ የደኅንነት መሥርያ ቤት በኩል ያሉት ወዳጆቻችን በሙስና እየተወነጀሉ ወደ ዘብጥያ እየወረዱ ይመስለኛል። በፊት የነበሩት የጸጥታና የመረጃ አባላትም ያለምንም ሥራ ደመወዝ እየተከፈላቸው ቢሮ ለቢሮ እየወጡና እየገቡ ይውላሉ በማለት መረጃው ፍንጭ ሰጥቷል። በአሁን ሰዓት የደኅንነትና የጸጥታ ሥራውን እየሰሩ ያሉት በደኅንነትና በጸጥታ ሙያ በአሜሪካን መንግሥት ሰልጥነው በቅርብ ወደ ሀገር የገቡት ባለሙያዎች ሲሆኑ የሚታዘዙትም አዲስ በተቋቋመውና በጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ ስር በሚመራው አዲሱ የመረጃና የጸጥታ ጊዜያዊ ቢሮ ነው። ጠንከር ያሉትን ሥራዎች ጣልቃ እየገባ በመሥራት ላይ ያለው የውጭዎቹ የመረጃ አካል መሆኑን ጭምር የሳተላይት መረጃዬ ያመለክታል።"

"በጣም የሚያሰጋን ይመስላል" ፕሮፌሰሩ የተከፈተ አፋቸውን በሁለት እጆቻቸው መዳፍ ሳይታሰባቸው እፍን አድርገው ያዙና ወደ ጣራው አንጋጠጡ።

"ከዚህ እንዳለን ልንታፈን እንችላለን የሚል ስጋት አለኝ። ለመዳን ከተፈለገ ያለን የመጨረሻው አማራጭ ምርምራችንን በአፋጣኝ ጨርሰን ወደ ተግባር መቀየር ነው። ችግር ላይ ብንወድቅም እንኳን ምርምሩ ለውጤት መብቃት አለበት።" አለ እስራኤላዊው ተመራማሪ።

ፕሮፌሰሩ መልስ ከመስጠታቸው በፊት አንገታቸውን እያሂዷሩ ሁሉንም ባልደረቦቻቸውን ተመለከቱ። የዝምታ ጽልመት መውደቁን ሲመለከቱም ስጋታቸው በእጥፍ እየጨመረ ያለ መሰላቸውና





ልባቸውን በውል ያልገባቸው ድካም ሲሰማው የማጥወልወል ዓይነት የመረረ ምራቅ አፋቸውን ሲሞላ ታወቃቸው።

"ምርምሩ እኮ መቶ በመቶ ተጠናቅቆ በአሁኑ ሰዓት የቀረው በተግባር ላይ መዋል ብቻ ነው። ሁሉም ነገር አልቋል። የቅድሚያ ሙከራ ሥራውን አልፎ የመጀመሪያው የመፍጠር ሥርዓት ተከናውኗል። የሚቀረን የማዳቀሉ ሥራ ብቻ ነው።" ጃፓናዊው ሲያቆም ጀርመናዊው ተመራማሪ ማስረዳቱን ቀጠለ።

"የማዳቀል ሥራውን በተመለከተም ለመስጠት የወሰንነው ፈቃደኛ በሆኑ ሴቶች ላይ መሆን እንዳለበት ተግባብተናል። ፈቃደኛ የሆኑ ሴቶችን ለማግኘትም ሴቶቹን በተለያዩ ጥቅሞች መደለል ይኖርብናል። ከዚህ በኋላ የዘር ፍሬው በማኅፀናቸው እየተሰጣቸው ጽንሱ እንዲዳብር ማድረግ ነው። ለዚህ ሥራ የሚውል ከፍተኛ ገንዘብ ስለመደብን ምንም ችግር አይኖርም የሚል እምነት አለኝ። የማዳቀል ሥራውን የሚሠሩልን ባለሙያዎች በአዲስ አበባ ከተማ በሁለት ቦታና በሌሎች በአሥራ ዘጠኝ የአውሮፓና የአፍሪካ ሀገራትም በተመሳሳይ መልኩ ተዘጋጅተው እየጠበቁ ናቸው። በነዚህ ክሊኒኮቻችን መጠቀም ከቻልን በአጭር ጊዜ ውስጥ የማዳቀሉን ሥራ እንጨርሰዋለን ብዬ አምናለሁ።"

"ይህንን ከማድረጋችን በፊት ማንቁርታችንን እንዳያንቁን እሰጋለሁ። መድኃኒቱ ቀደም ብሎ ወደየክሊኒኮቹ መግባት ይኖርበታል። በጣም በፈጠነ ሁኔታ የማንፈጽም ከሆነ በሁሉም አቅጣጫ መንገዱ እየተዘጋ ከዚህ ለመውጣት ይቸግረናል።" እስራኤላዊው ማስጠንቀቂያ ጭምር አስተያየት ሰጠ።

"ተወያይተን የምንወስነው ይሆናል። በቅድሚያ ሴቶቹ እየተመለመሉ እንዲመጡ ተደርገው ክትባቱ ቢሰጣቸውና እስኪጸንሱ እንክብካቤ እየተደረገላቸው እንዲቆዩ ቢደርግ የተሻለ ይመስለኛል።" አሜሪካዊው የራሱን አሳብ ሰጠ።

"ሁላችሁም ያቀረባችሁትን እንደ አማራጭ እንወስደዋለን። ጊዜ ወስደን መወሰን ስለሚገባን በዚህ ዙሪያ ስለምናደርገው ውይይት የሚኖራችሁን የተለየ ሃሳብ ከሰዓት ይዛችሁ መቅረብ ይኖርባችኋል። እኔና እንግዳችን ትንሽ ማውራት ያለብን ስለ መሰለኝ ከዚህ ልቆይ። ከኢንጂነር ጋር የነበረን ውይይትም በዚሁ ይብቃና ወደ ስራህ ተመለስ። የአንተ የሥራ ድርሻ ከእኛ ጋር ተቀምጠህ ለማውራት የሚመች አይደለም። አይንና ጆሮአችን ብቻ ሳትሆን ደም ስራችንም ነህ ብል የማጋንነው አይመስለኝም።"

ሳቅ ብለው የበለዙ ጥርሶቻቸውን ሲያሳዩት ኢንጂነሩ ከተቀመጠበት ተነሳና በግንባሩ ተሰናብቷቸው በሩን ከፍቶ ወጣ።

ሁሉም በዚህ መልኩ ክፍሉን እየለቀቁ ወጡ።

# ምእራፍ ስድስት

"በዚህ በኩል ንዳ" ከፊት ለፊቱ ያለውን በውኃ የተበላ ጠጠራማ መንገድ በአመልካች ጣቱ እየጠቆመው ተናገረ ሳምሶን ደበሌ ፡፡

"መጠምዘዣው ጠባብ ይመስላል፡፡ የአጥሩ ግንብ የመንገዱን ጠርዝ ይዞ ነው የተሠራው..." ስምኦን ወልዴ፡፡

"ሌላ ምርጫ የለህም" ሲል ቀጭን ትእዛዝ ሰጠው፡፡

የግንቡ ጠርዝ የመኪናዋን ኮፈን ገንጥሎት ኩርባውን ቢያልፍም ተመሳሳይ ሁኔታ ነው የገጠማቸው፡፡ የአጥሩን ግንብ ተጠግቶ የቆመ መኪና ይታያል፡፡ መንገዱን በግማሽ ስለ ሸፈነው ማሳለፉ አጠራጣሪ ነው፡፡ የመንገዱን ዳር ይዞ የቆመው ደብል ገቢና ሃይሉክስ ቶዮታ ጠቅላላ አካሉ በአቧራ የተሸፈነ በመሆኑ በዚያ ስፍራ ለብዙ ቀናት እንደ ቆመ ይጠቁማል፡፡ መስታወቶቹም በተመሳሳይ መልኩ አቧራ አለዚያም ጭቃ ለብሰዋል፡፡

"ወደ ጠርዙ ተጠጋና ንዳ" ሲል አዘዘው ስምኦን፡፡

"በጣም ጠባብ ነው..." ሳምሶን ደበሌ አመነታ፡፡

"ሌላ ምርጫ የለህም..." መመሪያና ትእዛዝን በደባለቀ ስሜት ተናገረው፡፡

እንደ ምንም ብሎ አለፈና ነፃ ወደ ሆነው የጠጠር ንጣፍ መንገድ ሲገባ ያለ ሥርዓት የተነጠፈው ድንጋይ መኪናዋን እስከሚበቃት አንጠራት፡፡

"ወደ ግራና ቀኝ እንዳትታጠፍ ቀጥታ ንዳ፡፡ የት ስትደርስ እንደምትጠመዘዝ እነግርሃለሁ" ትእዛዞቹ የበላይነት መንፈስ ስለ ነበራቸው መሪ የያዘው ሰው በሸቀ፡፡ ያም ሆኖ ምንም አልተናገረም፡፡ መንዳት ነው ያለበት፡፡

ለሀያ ደቂቃ ያህል በጠጠራማው መንገድ ሲንገጫገጩ ቆይተው በሁለት አቅጣጫ የሚታጠፍ መስቀለኛ መንገድ ላይ ደረሱ፡፡ በስተደቡብ ያለውን መጠምዘዣ እንዲይዝ ነግሮት ትንሽ እንደተጓዙ ወደ ዋናው አስፋልት የሚያወጣ ዳገታማ ቦታ ላይ ደረሱና መኪናዋን አቆማት፡፡

በአቧራ የተሞላው ዳገት መኪና ማስወጣቱ አጠራጣሪ ነበር፡፡ መሪውን በሁለት እጁ እንደጨበጠ ተመለከተው፡፡ "በጭራሽ የሚሞከር አይመስልም፡፡" ለራሱ ነበር የተናገረው፡፡ ቢሆንም መሞከር አለበት፡፡ ዙርያ ገባውን ተመለከተው፡፡ በግራ በኩልም ያለው የውኃ መውረጃ ወንዝ ነው፡፡ ከተንሸራተተ ከቆሻሻው የወንዝ ውኃ መግባታቸው የማይቀር ነው፡፡

"ወደ ኋላ ተመልሰን..." አቋረጠው፡፡

"ሌላ አማራጭ የለም፡፡ ወደ ፊት መቀጠል አለብህ" በጥርሶቹ መኃል ተናገረ ስምኦን፡፡





"ብንገለበጥስ..." እልህ ተናነቀው ሳምሶን፡፡

"ዲያቢሎስ ያውቃል፡፡" አለው በሹፈት፡፡

"መቀለድ ትችላለህ፡፡" አለው እየተበሳጨ፡፡

"መቀለዴ አይደለም፡፡ ይልቅ ፍጠን" መኪናዋ ኃይለኛ ማጓራት አሰምታ አቧራማውን ዳገት እንደ ዝንጀሮ ቧጥጣው ወደ ኋላዋ ተንሸራትታ ተመለሰች፡፡

"እንደገና ሞክር፡፡ ሌላ ምርጫ የለንም፡፡"

በእርግጠኝነት የሚለውን ለማመን አልቻለም፡፡ በኃይል ተነፈሰና የነዳጅ መስጫውን ሲረግጠው እንደ መንጠር ብላ ዳገቱን ልሳው ወጣችና አስፋልቱን ረገጠች፡፡

በቀኝ በኩል እንዲታጠፍና መስመሩን እንዲይዝ በአመልካች ጣቱ ከመጠቆም በቀር ቃል አላወጣም፡፡፡ ያለ ምንም ንግግር ለአሥር ደቂቃ ያህል በዋናው መንገድ ሲጓዙ ሁሉም ነገር ጸጥታ የሰፈነበት ነበር፡፡

"መገንጠያህ እየቀረበ ነው፡፡ ቀዝቀዝ አድርግና በቀኝ በኩል ታጠፍ፡፡፡ መንገዱ ከበፊቱ የበለጠ ጠባብ ነው" አስጠነቀቀው፡፡

"ወዴት ነው እየሄድን ያለነው?" በጥርጣሬ እየተመለከተ ጠየቀው፡፡

"ወደ አንጥረኛው ቤት" በኃይል እየተነፈሰ መለሰለት ስምኦን፡፡

"ምን ልንሠራ?" ረጋ ብሎ ጠየቀው ሳምሶን ደበሌ፡፡

"አንድ ጎራዴ እዲሠራልኝ ጠይቄዋለሁ፡፡"

"የምን ጎራዴ?" ግራ የገባው መሰለ፡፡

"ወደ ውጭ አገር የሚላክ ጎራዴ" በፊት መስታወት ተመለከተው፡፡

"አትቀልድ..." እንደ መሳቅ ብሎ በግማሽ ተመለከተው፡፡

"ቀልዴን አይደለም፡፡ አሜሪካዊው ወርቁን በጎራዴ ቅርጽ እንዳሰራለት ጠይቆኛል፡፡"

"ምን እያወራህ ነው?" እሱም ፊቱን በመስታወት ለማየት ሞከረ፡፡

ላንቃህ እስከሚሰነጠቅ ደህና ጉርሻ ውጠሃል ማለት ነው፡፡ ብቻህን እንደ በላህ ብቻህን ሁሉንም ነገር. . ." ውስጡን አጉተመተመ ሳምሶን፡፡

"ቀድመህ ለምን አልነገርከኝም ታዲያ?" በጉድን ተመለከተው፡፡

"አሁን ነገርኩህ አይደል እንዴ? ምን ልዩነት አለው?" ሲል ጠየቀው፡፡

"እንዳልከው መቼም ብሰማ ለውጥ የለውም" አለው በመሰላቸት፡፡

"በጎራዴ መልክ እንዲሠራለት ዲዛይኑን ሰጥቶኛል፡፡ ወጭውንም የሚሸፍነው ራሱ ነው፡፡" ወሬ ማራዘሙ የበለጠ አበሸቀው፡፡

"የወርቅ ጎራዴ ምን ማለት ነው? ከመቼ ወዲህ ነው ወርቅ ጎራዴ ሆኖ መሥራት የጀመረው?" ሲል ጠየቀው፡፡

"ለአንገት መቅሊያ የሚያገለግል እውነተኛ ጎራዴ ሳይሆን ከሀገር ለማውጣት እንዲያመች በእውተኛው ጎራዴ ተመሳስሎ የሚሠራ ጉራዴ ነው፡፡" አለው እየሳቀ፡፡

"የጉምሩክ ተቆጣጣሪዎች ጎራዴውን መመልከታቸው ይቀራል እንዴ?" እሱም ሳቅ አለ::

"እንዳልከው የጉምሩክ ሠራተኞቹ ካፎቱ አውጥተው ማየታቸው የማይቀር ስለሆነ ወርቁ በጎራዴ ቅርጽ ተሰርቶ ከወጣ በኋላ ላዩ በአልሙኒየም ብረት ይለብሳል:: እጀታውም እንዲሁ ላዩ በብር እንዲለበጥ እና እንዲሠራ ተነጋግረን ተስማምተናል::"

"በምትፈልጉት መልኩ ሠርቶ ለማስረከብ አሳቡን ተቀብሎታል:: ማለቴ በትክክል እሠራዋለሁ ብሎ አምኖበታል?" መሪ የጨበጠው ሰው ጥያቄው መሰረታዊ ስለ ነበር እውነቱን ሊነግረው ፈለገ::

"ዲዛይኑን ስንሰጠው እንደሚሠራው አምኖ ተቀብሎናል:: አሜሪካዊው ራሱም የጌጣ ጌጥ ሥራ ባለሙያ ስለሆነ ሊረዳው ይችላል:: አንጥረኛው የተፈለገው ለማንጠርያ መሳርያዎቹ ነው:: ሙያውን አሜሪካዊው ስለሚችል ችግር እንደማይኖር ነግሮኛል" አለ ስምኦን::

"ፈረንጁ አብሮት ይሠራል ማለት ነው?" አለ ሳምሶን::

"እየተመላለሰ ይጐበኘዋል:: ካስፈለገም አብሮት ይሠራል::"

"ብረት ቀጥቅጦ ቢሠራና በላዩ ወርቁን አፍስሶ ቢሰጣችሁ ማረጋገጫ ስለማይኖር አብሮት ቢሠራ ይሻለዋል::"

"ይህንን እንደሚያደርግ አሜሪካዊውም አምኖበታል::"

እንደ መሳቅ አለ:: "መልካም ሥራ ይሁንላችሁ::"

"እስከሚጠናቀቅ ድረስ አብሮት እንዲሆን እነግረዋለሁ::"

"ሥራውን ከአስረከበ በኋላ ለፖሊስ ቢጠቁምስ?"

"ሥራውን ሲጨርስ ሌላ ዘዴ ይፈለግለታል::"

"ልታስወግዱት ፈለጋችሁ እንዴ?" ግራ በመጋባት ጠየቀው::

"የመጀመሪያ ምርጫችን ላይሆን ይችላል::"

"ሁኔታው ከበድ ያለ ይመስለኛል::" በቅሬታ መለሰለት ሳምሶን::

"አሳባችንን መለወጥ አንችልም::"

"የምንሄደው ሥራውን ለማስጀመር ነው?" በተደበላለቀ ስሜት ጠየቀው::

"ወደሚያነጥርበት ስፍራ ልንወስደው ነው:: የመሥርያ ማሽኖቹን አዘጋጅቶ ይጠብቀናል:: እንዲሠራልን የተስማማነው እኛ በመረጥነው ስፍራ ስለሆነ እራቅ ያለ ቦታ አዘጋጅተናል::"

"በዛሬው ቀን ሊጀምር ነው እያልከኝ ነው?" የሰማውን የተጠራጠረ መሰለ ሳምሶን ደበሌ::

"አሜሪካዊው በትንሽ ቀናት ውስጥ ተሠርቶ እንዲሰጠው ይፈልጋል:: በጣም ነው እየተጣደፈ ያለው:: ያጣደፈው ምክንያቱ ምን እንደሆነ ሊገባኝ አልቻለም::" አለ ስምኦን::





"ቀደም ሲል ለምን አልነገርከኝም ታዲያ?" የቀድሞውን ጥያቄ ሲደግምለት ፊቱን ቅሬታ አጠላበት::

"ምሥጢሩን ይዤ እንድጠብቅ ስለ አስጠነቀቀኝ ነው:: ቅር ትሰኛለህ የሚል ግምት አልነበረኝም::" ሳቅ ብሎ ተመለከተው::

"አሁንስ እንድትነግረኝ ፈቀደልህ እንዴ?" በፌዝ ቅላፄ ጠየቀው::

ፌዙ ቢገባውም "እንደዚያ ነበር::" ሲል መለሰለት::

"ጐራዴውን አሜሪካን ስንዘምት ማርከን ይዘነው እንመለሳለን::"

"ይሳካል የሚል እምነት ነው ያለኝ::" ሲል በምፀት መለሰለት::

"ሥራውን ጨርሶ ካስረከባችሁ በኋላ ለፖሊስ ይጠቁማል::"

"ሽምቀቆ ሳናጠልቅለት በዘፈቀደ አንለቀውም::"

"ምን ዓይነት ሽምቀቆ?" ቃሉን ጥብቅ አደረገው::

"ሲደርስ እንወያይበታለን::"

ከመንታው መንገድ ላይ በመድረሳቸው ውይይታቸው ተቋረጠ::

"ወደ ቀኝ ታጠፍና ከግንቡ ስር ተጠግተህ ቁም::"

"የአንጥረኛው መኖርያ ቤት ይህ ነው እንዴ?" በረጅም የግንብ አጥር የተከበበውን ባለ ሁለት ፎቅ ዘመናዊ ሕንፃ እየተመለከተ በአርምሞ ጠየቀው:: "ይኼ ነው::" አለው በማድነቅ ቅላፄ:: "ጎበዝና ጠንካራ ሰው ነው::"

ጥንካሬው በምን መንገድ እንደገለጽለት ባለማወቁ ነው አይደለም በማለት አስተያየቱን ለመስጠት አልፈለገም::

በስልኩ ትንሽ እንደ ተነጋገረ ትንሹ በር ተከፈተና አሮጌ ጋወን ያጠለቀ ኮስማና የሚመስል ሰው ወደነሱ አቅጣጫ እየተራመደ ሲመጣ በደብዛዛው ብርሃን ሲመለከት ራሱን ተጠራጠረው::

ኮስማናው ሰው ከመድረሱ ቀደም ብሎ ወረደና የኋላዋን በር ከፍቶ ጠበቀው ስምኦን::

ያዘለውን ትልቅ የሸራ ቦርሳ ከመኪናዋ ሁለተኛ በር በመጣል ፊቱን መልሶ እየገፋ ወደ ውስጥ ሲያስገባው ከባባዶቹ ብረቶች ተንገጫገጩ:: ውስጥ ገብቶ ከዕቃው አጠገብ ሲቀመጥ የተቃራኒውን በር ከፍቶ ስምኦንም ገባ:: ጎን ለጎን ሲቀመጡ አንጥረኛው ለመጨረሻ ጊዜ ይመስላል በረጅሙ ተነፈሰ:: መንፈሱ ክፉኛ የተረበሸ ለመሆኑ ሁሉም ነገሩ ያስረዳል::

ሳምሶን በፊት መመልከቻ ከሲታ ሪዛም ፊቱን አስተዋለው:: ለዚህ ግቢ እንኳንስ ባለቤት ዘበኛ መሆኑም አጠራጠረው::

"ዕቃዎችህ የተሟሉ ናቸው?" ከውጭ በገባው ብርሃን አተኩሮ ለመመልከት አንገቱን ወደ ፊት ቀደም አደረገ ስምኦን::

"ያስፈልጋሉ የምላቸውን የያዝሁ ይመስለኛል:: የክፍያውንስ ጉዳይ ምን አሰባችሁበት? ሥራውን እስከማጠናቅቅ ሩቡን ያህል" አለ ገብረክርስቶስ::

ክፍያው ይሁን አለዚያም ለመሥራት የነበረው ፍላጎት በመቀነሱ ደስተኛ ያለመሆኑን ፊቱ ምስክርነት መስጠት ጀምሮ ነበር:: ሳቅ አለ ስምኦን እሱን ተከትሎ እሱም ሳቀ::

"ሁሉንም በቼክ እንፈርምልሃለን::"

"በቅድሚያ የቀብድ ክፍያ ያስፈልጋል እኮ::" በቅሬታ ሲናገር ጨፍጋጋ ፊቱ የበለጠ እየጨፈገገ ማስፈራሪያ መሰለ:: በመበሳጨት ይመስላል ሽበታም ፀጉሩን በጥፍሩ ደህና አድርጐ እየቆፈረውም ነበር::

"ለምን ቀብዱ አስፈለገህ? ቼኩን ዛሬውኑ ፈርመን እናስረክብሃለን:: ከዚያ እንደ ደረስን የሃምሳ ሺህ ብር ቼክ በስምህ ፈርሞ እንዲሰጥህ ከደንበኛዬ ጋር ተነጋግረንበታል::" አለው ስምኦን::

"በራሴ ቤት ብ···ጋላችሁ ለሁላችንም ደኅንነት የተሻለ ይሆን ነበር::" የዶሮ መኀራጉርን በመሰለው ጥፍሩ ፀጉሩን መቆፈር አላቆመም:: ገብረክርስቶስ ግደይ ቅር የተሰኘ ይመስላል::

"ምስጢሩ እንዲጠበቅ ለማድረግ ሲባል እንጂ የተለየ አሳብ ኖሮን አይደለም::" አለው ስምኦን::

"ምሥጢር ላይጠበቅ ይችላል የሚል ጥርጣሬ አድሮባችኋል ማለት ነው?" የቅሬታ የሚመስል ጥያቄ አቀረበለት ገብረክርስቶስ::

"ያለማመንና የመጠራጠር ጉዳይ ሳይሆን መከናውን ያለበት በተሰወረ ስፍራ በመሆኑ ነው:: ሥራውን ሌሊት እየሰራሁ አጠናቅቃለሁ ብለህ ብታስብም ልጆችህና ባለቤትህ ሊያዩህ ይችላሉ:: 'ልጆችህም አባታችን እየሠራ ያለው ምንድነው?' ብለው መጠየቃቸው የማይቀር ነው:: ብትከለክላቸውም በሌለህበት ገብተው ያዩታል:: ከዚያ በኋላ ምሥጢር መሆኑ አከተመለት::"

ተናግሮ ሲጨርስ ትከሻውን በመዳፉ ቸብ አደረገው::

"ያም ሆኖ ለደኅንነቴ በጣም እሰጋለሁ:: ከበድ ያለው የውል ስምምነት ከፍተኛ አደጋ ያለው ይመስለኛል:: ብቻ አንተ የከፉ ጊዜ ወዳጄ ስለሆንህ የከፈልኩትን ያህል ዋጋ ብከፍልም ብዙ አያስጨንቀኝም::" ጥሩ ግብረገባዊ አነጋገር ነበር:: ሳቅ አከለበት::

"እንዳንተ ባለ ወዳጄ ላይ ክፉ ነገር ከሚደርስ እራሴን ዋጋ ለማስከፈል ወደ ኋላ አልልም::"

"ለአንተ በአለኝ አክብሮትና እምነት ነው የገባሁበት ለከፋ ነገር አጋልጠህ እንደማትሰጠኝ እተማመንብሃለሁ::" አለ ገብረክርስቶስ::

"የምታልመው ሁሉ የተቀደሰ ነው:: ጨለምተኝነት ያለባቸውን ሰዎች ስለማልፈልግ ነው ወደ አንተ ዘንድ እንድመጣ ያደረገኝ:: ይህንን ያህል እምነት ስትጥልብኝ ኩራት ተሰምቶኛል::" ሲል አሞካሸው::

"ለገንዘብ ጥቅም ብቻ አይደለም በዚህ ውል የተስማማሁት:: ለአንተ ከአለኝ አክብሮትና ከነበረን የቆየ ወዳጅነት በመነሳት እንደ ሆነም ተገንዘብልኝ:: ሕይወትን ሊያሳጣ በሚችል የውል ስምምነት የገንዘብ ጥቅም ብቻ መታየት የለበትም:: ይህ ስምምነት ሕይወትን ሊነጥቅ የሚችል ነው:: የሕይወትን ዋጋ የሚጠይቅ ስምምነት በሚደረግበት ወቅት





ከገንዘብ በዘለለ የጠበቀ ወዳጅነት ወሳኝ ነው::"

በቅሬታ መልክ ያቀረበው አስተያየት እንደዋዛ የሚታለፍ አልነበረም:: እራሱን ከፍና ዝቅ በማድረግ ለበሳል አስተያየቱ ያለውን የላቀ ግምት አሳየው ስምኦን::

"ወደ አንተ የመጣሁት በቆየው ወዳጅነታችን በመተማመን ጭምር እንደ ሆነ እየጠቀስክልኝ በመሆኑ ተደስቻለሁ:: እንዳልከው የሕይወትን ዋጋ የሚጠይቅ ስምምነት ከገንዘቡ በላይ የጠበቀ ወዳጅነትን ይጠይቃል::" በድጋሚ ተንጠራርቶ ትከሻውን በመዳፉ ደለቀው::

ደስ ያለው በሚመስል የአካል ንቅናቄ ከመኪናዋ ወንበር ላይ ተቁነጠነጠ ገብረክርስቶስ:: በእርግጥም ወዳጅነትና መተማመን የሚለው ቃል ከመሸንገያ ባለፈ እውነት ቢሆን ኖሮ አስፈላጊ ነበር:: "ከብዙ ውለታ ትንሽ መተማመን" ይበልጣል:: ከብዙ ዓመታት በፊት በአንድ መጽሐፍ ላይ ይህንን ጥቅስ እንዳነበበው ያስታውሳል::

ለበርካታ ሰዓት ከተጓዙ በኋላ ከዋናው ጎዳና በስተቀኝ በኩል አንድ ግዙፍ ሕንፃ ታያቸው:: መኪናዋ ዋናውን መንገድ በመልቀቅ ወደ ሕንፃው መግቢያ በር ታጠፈች::

ስምኦን የሕንፃውን መግቢያ በር በዝግታ አንኳኳ:: ግዙፉ የብረት በር ተከፍቶ የሌሊት ጋዎን ያጠለቀ ረጅም ዘበኛ ብቅ አለና ተያይዘው ወደ ውስጥ ገቡ:: ከጥቂት ቆይታ በኋላ ባለ ጥቁር ጸጉር የውጭ አገር ዜጋ ይዘው ሲመለሱ አንጥረኛው በትኩረት ተመለከተው:: ነጩ እንግዳ ወደ መኪናዋ ገብቶ ከሹፌሩ ጎን ሲቀመጥ ከሳምሶን ጋር ሰላምታ ተለዋወጡ:: ደስ ያለው ይመስላል:: ቋንቋ ለቋንቋ ባይግባቡም ወደ ኋላው ተንጠራርቶ እየሳቀ አንጥረኛውን ጨበጠው::

የሕንፃውን አካባቢ ለቅቀው ከወጡ በኋላ የአዲስ አበባ ሰሜናዊ ምእራብ አቅጣጫን በመያዝ ለበርካታ ሰዓት ተጉዘው የመሃል አዲስ አበባ ከተማን ጨርሰው የቀበና ወንዝን ተሻገሩ:: እንግሊዝ ኤምባሲ ከመድረሳቸው ትንሽ ርቀት ላይ ወደ ሰሜን ምስራቅ የሚዘልቀውን ጎዳና ትተው ወደ ተራራው በሚወጣ ቀጭን አስፋልት ዳገቱን መውጣት ሲጀምሩ የመኪናዋ ሞተር ማጓራት ጀመረ::

"ወደ መጣችበት ተንሸራትታ እንዳትመለስ ተጠንቀቅህ ንዳ::" አለው ስምኦን::

መንገዱ ቀጥ ያለ ከመሆኑ በተጨማሪ በውኃ የተበላና ጠባብም ነበር:: ከብዙ አሰልቺ ጉዞ በኋላ ከተራራው ጥግ ደረሱና ከመኪናው ወርደው ወደ ተራራው ጫፍ በእግራቸው ጉዞ ጀመሩ::

የተራራው እናት በተለያዩ ዛፎችና በለምለም የሰንበሌጥ ሳር የተሸፈነ ሰፊ ሜዳ ነበር:: በጨለማ ግርማ የከበደው አካባቢ የሌሊቱን አየር እየተቀበለ ኃይለኛ ቅዝቃዜ ይረጫል:: የተራራው ዙርያ በደን የተሸፈነ ስፍራ

ነው፡፡ በስተምስራቅ ጠርዝ ደኖቹን ተንተርሶ ያለው ቤትም በጨረቃዋ ብርሃን ደብዘዝ ብሎ ይታያል፡፡ ከአነስተኛ ቤት የሚወጣ መጠነኛ ብርሃን የተመለከቱት ረባዳው ላይ ሲደርሱ ነበር፡፡ በቤቷ ውስጥ ያለው ሽማግሌ በር ከፍቶ እንዳስገባቸው ተቀጣጥሎ የተንተረከከ የከሰል እሳት ላይ ነበር ዓይናቸው ያረፈው፡፡ የከሰል ፍሙ ተከትሏቸው የገባውን ቀዝቃዛ አየር ወደ ኋላ ስለመለሰው ከውስጥ የታመቀ ሙቀት ተቀበላቸው፡፡ በሥርዓት የተደረደሩት ወንበሮችና የተቀጣጠለውን ከሰል ሲመለከት ቀደም ሲል ዝግጅት የተደረገበት መሆኑ ለአንጥረኛው ግልጽ እየሆነለት መጣ፡፡ ሁሉም ነገር የታሰበበት ነው ሲል እራሱን በዝግታ እያወዛወዘ ደስ ይላል በማለት ከራሱ ጋር ተነጋገረ፡፡

ይህንን ሙቀት ባያገኝ ኖሮ ብርዱ ይጐዳው ነበር፡፡ ጠቆር ያለ መልክ ያለውና ዕድሜው በስድሳዎቹ መጀመሪያ ላይ የሚገመት ጠንካራ ተክለ ሰውነት ያለውን የቤቱን ባለቤት ያስተዋለው መገረም በታከለበት ማድነቅ ነው፡፡ በዚያ ምድረ በዳ የሚኖረው አዛውንት የፊት ገጽታው ደስተኛ ይመስላል፡፡ ይህ ሁሉ ደስተኛነት ከምን ሊመነጭ እንደሚችል መገመት አልቻለም፡፡ ኑሮው ከአራዊት ጩኸት ጋር ነው፡፡ የአናብስቱ ድምጽ ሲያስገመግም ይሰማዋል፡፡

በቤቱ ውስጥ ከሱ ውጭ ምንም ሰው ባለመኖሩ ብቻውን ለመኖሩ እርግጠኛ ነው፡፡ እናስ ታዲያ እንዴት ደስተኛ መሆን ይቻላል፡፡ ከሳሎኑ በሁለት አቅጣጫ የተዘጉ በሮች ስለ ነበሩ አንደኛው የሰውዬው የመኝታ ክፍል ሊሆን እንደሚችል ገመተ፡፡ ሁለተኛው ምናልባትም በተለያዩ የተዘረፉ ቁሳቁሶች የተሞላ ሊሆን ይችላል ሲል አሰበ፡፡ እኔስ በየትኛው ክፍል ውስጥ ይሆን የሚዘጋብኝ? ለምን ያህል ጊዜስ ይሆን የምቆየው ሲል ራሱን በተደጋጋሚ መጠየቁ አልቀረም፡፡ ምናልባትም የመጨረሻ ዕጣው በዚሁ ጫካ ውስጥ ሊያከትም ይችላል፡፡

ይህንን ሲያስብ ኃይለኛ ቅዝቃዜ ተሰማውና እንደማንቀጥቀጥ ያለ ስሜት ትከሻውን አንጥሮት አለፈ፡፡ ሌላ ኃሳብ ከሀገር እስከሚመጡ ድረስ በዚሁ አግተው ሊያቆዩኝ ይችላሉ፡፡ የምን በጫካ ውስጥ መጣል ነው፡፡ ይህንንስ የሰይጣን ጆሮ አይስማው፡፡ በነብር ጅራት እየተጫወተ መሆኑ የገባው ዘግይቶ ነው፡፡ አደገኛ ሁኔታ ውስጥ መግባቱ የታወሰው ሁሉን ነገር ተነጋግረው ከጨረሱ በኋላ ስለ ነበር ቃሉን አጥፎ ውሉን ማፍረስ በራሱ የባሰ አደጋን እንደሚያስከትል ተረድቷል፡፡ ከጥቅሙ የበለጠ አደጋው ከፊቱ እየታየው ቀጠለ፡፡

የቤቱ ባለቤት ከፈረንጁ ጋር ሰላምታ የተለዋወጠው በተቀላጠፈ እንግሊዝኛ ነበር፡፡ ሰውየው በዚያው ነዋሪ ሊሆን አይችልም፡፡ ይህ ቤት ለሕገ-ወጥ ሥራው የተዘጋጀ ጊዜያዊ ጉጆ እንጅ የዚህ ሽማግሌ መኖሪያ ቤት አይደለም ማለት ነው፡፡





የተማረ ሰው ከዚህ ጫካ ውስጥ ብቻውን ሊኖር አይችልም ሲል አሰበ፡፡ ምክንያቱ የረቀቀ ቀልድ ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን ትንሽ ፊደል ከቆጠሩ ምኞታቸው የቅንጦት ኑሮ መሆኑን ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ ለሱ መንገር "ለቀባሪው አረዱት" እንደሚሉት ተረት ስለሆነ በዚህ ሊታለል አይችልም፡፡ ሰውዬው የተማረ ብቻ ሳይሆን ማንኛውንም ነገር የተገነዘበ ነው፡፡ ምን እየሠራ እንደሆነ መገመት ቀላል ነው፡፡ የዘረፉትን ዕቃ የሚያጠራቅሙበት ስፍራ ሆኖ ሽማግሌው በጥበቃ እዚህ ይገኛል ማለት ነው፡፡

"ይህ ሚስተር ሆልከረፍት ይባላል፡፡ በስራው ሊረዳህ የተዘጋጀ ባለሙያ ነው፡፡ እሱም የቤቱ ባለቤት አፈወርቅ ደስታ ይባላል፡፡ የሚያስፈልግህን ማንኛውንም ነገር ያለምንም ማፈርና መግደርደር ጠይቀው፡፡ ከሚስተር ሆልከረፍት ጋርም እያስተረጎመ የሚያግባባችሁ እሱ ነው፡፡"

ገብረክርስቶስ ከወጥመድ የገባች አይጥ መሆኑን እየተረዳው መጣ፡፡ የሕይወት መስመሩ ከዚህ በኋላ ለመቀጠሉ እርግጠኛ አይደለም፡፡ ስምኦን መመሪያ መስጠቱን ቀጠለ፡፡

"እኔና ሳምሶን ወደ አዲስ አበባ እንመለሳለን፡፡" ወደ ሳምሶን እየጠቆመ ተናገረ፡፡

ሰፊ ማብራሪያውን በሚሰጥበት ወቅት አእምሮው ተወጥሮ ብዙ ነገሮችን እያሰበ ነበር ገብረክርስቶስ፡፡

"ተግባብታችሁ በመሥራት ከሦስትና ከአራት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ ሞክሩ፡፡"

ሦስቱን ሰዎች ተራ በተራ እየተመለከታቸው ማብራሪያና ትእዛዝ ሲሰጣቸው ያዳምጡት የነበረው እንደ ትእዛዝ ተቀባይ በመሆን ያለ መቃወም ነበር፡፡ ፈረንጁ ራሱን ይነቀንቃል፡፡ አማርኛ ይሰማል ማለት ነው፡፡

"ውሻ ሰላቶ" ሲል አጉተመተመ የእውቀት ብቻ ሳይሆን የቋንቋም ቀበኛ የመሆናቸው ምሥጢር እያስገረመው፡፡

ከሹፌሩ ጋር ተከታትለው እንደወጡ የቤቱ ባለቤትና ፈረንጁ በእንግሊዝኛ ትንሽ ቃላት ተለዋውጠው የሚቀጥለውን በር በመክፈት እንዲገባ ጋበዙት፡፡ ገብረክርስቶስ የተመለከተውን ለማድነቅ አለዚያም ለመንቀፍ አቅም ስላልነበረው አንድም ቃል ትንፍሽ ሳይል ከሸራ ቦርሳው ዕቃውን እያወጣ ያስተካክል ጀመር፡፡

ማንጠሪያና የቅርፅ ማውጫው በመልክ በመልኩ አስተካክሎ እንደጨረሰም ከምድጃው ላይ ከሰሉን አግፈጠፈጠ፡፡ ሠርቶ እንዲያጠናቅቅ የተሰጠው ጊዜ አጭር ስለሆነ መቸኮል አለበት፡፡ የቅርጽ ማውጫያው የሸክላው ዕቃ እንደየመጠኑ ተዘጋጅቷል፡፡ ከወርቅ ሰሪው የሚጠበቀው በተሰራው ቅርጽ ማውጭያ ውስጥ ወርቁን እያቀለጠ እንዲረጋ ማድረግ ብቻ ነው፡፡ ቅርጽ ይዞ ከወጣ በኋላም ነጭ አልሙንዩም ማልበስ ይጠበቅበታል፡፡ ሥራው እንደተጠናቀቀ በተዘጋጀው ግራይንደር ይሞረድና በሁለቱም ፊት

ስለት ያለው ሰይፍ ሆነ ማለት ነው።

እጀታውም እንደዚሁ በላዩ ላይ ብር ይፈስበትና የብር እጀታ ጎራዴ ይሆናል። ከዚያ በኋላ የሃምሳ ሺህ ብር ቼክ ተፈርሞለት ወደ መጣበት ይመለሳል። ብቻ የሰይጣን ጆሮው ይደፈን። እነዚህንና ሌሎችንም እያብሰለሰለ ዕቃዎቹን በጥንቃቄ ሲያስተካክል ፈረንጁ ከአጠገቡ ቆሞ ሁሉንም ነገር ይከታተላል። ወደ ንጋት ሲቃረብ አጠቃላይ ሥራው ተጀመረና ፈረንጁም ወርቁን ወደ ቅርጽ ማውጫው ማስገባት ቀጠለ። በቅርጽ ማውጫው ለረጅም ሰዓት የሚቆይ በመሆኑ የቅርጽ ማውጫዎቹ በርከት ብለው ነበር የተዘጋጁት። በዚህ መልኩ የቀጠለው ሥራቸው የምሳም ሆነ የቁርስ ሰዓት የተከበረበት አልነበረም።

እስከ አራተኛው ቀን ምሽት ድረስ ያለ ምንም ረፍትና ፋታ እንዲሰሩ ግድ ሆነባቸው። በአንድ ሳምንት ውስጥ ሁሉም ጉራዴዎች ቅርፃቸውን ይዘው ሲወጡ የፈረንጁ የፊት ገጽ እንደ ፀሐይ አበራ። ሁሉም ነገር ባሰበው መንገድ በመከናወኑ ከፍተኛ እርካታ ተሰምቶታል።

ዓለም ለሁሉም እኩል ደስታን አትሰጥምና ገብረክርስቶስ በበኩሉ ውስጡን መንደድና መቃጠል ጀምሯል። ምንም እንኳን ዕድሜውን ሙሉ በወርቅ ማቅለጥ ሥራ ያሳለፈ ቢሆንም እንደዚህ ደረጃውን የጠበቀ በርካታ ወርቅ ገጥሞት አያውቅም። በጉምጅት ቅናት እያረረ ነው ሥራውን ያገባደደው። ወርቅ እንደተራ ብረት ተቀጥቅጦ የጦር መሳሪያ ሲሰራበት ማየት . . . ያስብ ያስብና የማንዘፍዘፍ ትንፋሽ ያወጣል ገብረክርስቶስ። እየተቃጠለ ያለው ታድያ በሀገር ኃብትነቱ ሳይሆን የኔ በሆነ በሚል የቅንዓት ስሜት ነበር።





# ምእራፍ ሰባት

"እየተሠራ ያለውን ሥራ ጌታ አልፈቀደውም የሚል እምነት አለኝ። ወደ ተግባር ከመለወጣችሁ በፊት በጥልቀት ብታስቡበት የኔ ምክር ነው።እያስበረገጋችሁና፣ እያስፈራራችሁ ያለው ማንም አሳድዶአችሁ ሳይሆን የራሳችሁ ያልተገባ ሥራ ነው። ውስጣችሁ ክፉኛ እየፈራ ነፍሳችሁ እረፍት አጥታ ስመለከት አዝኛለሁ። የምትሠሩት ሥራ እግዚአብሔር የማይፈቅደው መጥፎ ተግባር በመሆኑ አሁንም ደግሜ ልምከራችሁ። ወደተግባር ከመቀየራችሁ በፊት ደጋግማችሁ ለማሰብና ከድርጊታችሁ ለመቆጠብ ክርስቶስ እንዲረዳችሁ በጸሎት እጠይቃችኋለሁ።" አቋረጡት።

"አእምሮህ እንደተወጣጠረ እየተረዳሁት ነኝ። ምክንያት በሌለው ተረት ተረት ዓይነት ወሬ ጊዜውን ሰጥቶ ከአንተ የሚከራከር ሰው እንደሌለ ተረዳ። ለምትናገረው ሁሉ ቅድሚያ ማሰብ ይኖርብሃል። ሳይንስ በቲዮሪ የሚባክን ጊዜ እንደሌለው በአሳለፍከው ረጅምና አሰልቺ የምርምር ዘመን የተረዳኸው ይመስለኛል። ቲዮሪና ፍልስፍና ዘመንና ጊዜውን የሚፈጀው ለነገሮች ምሳሌ በመስጠት አሳቦችን እርስ በርሳቸው እያጣረሰ ስምና መልክ በማውጣት ያልተጨበጠ የማይዳሰስ ተስፋን በማሳየት ነው። ቲዮሪ እራሱ ይፈጥራል እራሱ መልሶ አቃርኖ ያፈርሳል። የቲዮሪና የፍልስፍና መንገድ ሁል ጊዜ ግምት እንጂ የስሌት ልኬት መስፈርት የለውም። መጥፎ በሽታ አንተንም ተሳፍሮ ንቁ አእምሮህን አዝጎታል።

ክርስቶስ አልፈቀደም ብለሃል። መቼ ጀምሮ ነው ክርስቶስ ከዙፋኑ ወርዶ ለምንሠራው ሥራ ሁሉ የፍቃድ ሰርተፍኬት ሲሰጥ ያየኸው? እንዲህ ያለው ቧልት ስፍራ የለውም። ለምንሠራው እውቀትና ጥበብን ይሰጣል እንጂ ፎርማን ሆኖ ከዚህ እስከ እዚህ በቂያችሁ ነው እያለ ሲያከፋፍልና ሲያደላድል የታየበት ጊዜና ዘመን የለም። የሰው ልጅ በራሱ ጥረት ሁሉንም ነገር እንዲሠራ ከሌላው እንስሳ በተሻለ በሚያስብ አእምሮ ፈጥሮታል። የተሻለ ነገር እየሠሩ መኖር የእኛ ውሳኔና ድርሻም ነው። ቧልተኞች የሕዝብን አስተሳሰብ ወደኋላ እየጎተቱ የነሱ ተገዥና አምላኪ የማድረግ ስልታቸው የረቀቀ ነው። በአለፉት የሰው ልጅ ዘመናት ታሪካቸው ቀልድ በመሆኑ የሌላው ረጅም ለቅሶ ለነሱ ሳቅ ሆኖ ቆይቷል። ለምንና እንዴት ብሎ በጥያቄ አያስቸግራቸውም። ራሳቸውን ከሌላው የተለዩ አድርገው ስለሚገምቱ እነሱ ከሌሉ እሱ መኖር እንደማይችል በድፍረት እየተናገሩ ለማስተማርም ብዙ ጥረዋል። ይህንን ውሸት ያልተቀበላቸውንም አሰቃይተዋል ገድለውትማል። የአሁኑ ዘመነኞችም የሚመጡትን በርካታ የትውልድ ሽግግሮች በተለመደው ማስመሰያዎች እያወናበዱ በድንቁርና ለመግዛት የነሱን ብልጠት እያሳዩን ነው።

ፈጣሪ ሰውን ሲፈጥረው ይህችን ዓለም ተደስቶና ያሻውን ሠርቶ ይኖር ዘንድ እውቀቱን አልገደበበትም፡፡ የገደብ ልኬት ያለው በእኛ በሰው ልጆች ዘንድ ነው፡፡ በተሰጠን ጥበብ የሕዝብን አስተሳሰብና ልማድ አጥፍተን ሁሉንም የሰለጠነ ሕዝብ ለማድረግ ስናስብ ሊያደናቅፉን ይፈልጋሉ፡፡" ሲጨርሱ በሲቃ ተንፍሰው ተመለከቱት ፕሮፌሰሩ፡፡

"ቢፈልግ ኖሮ ማንም ረዳት ሳያስፈልገው ከእናንተ በተሻለ መልኩ የሠለጠነ አድርጎ መፍጠር ይችል ነበር፡፡" አለ በመሰላቸት፡፡

"ጥበብ መስጠቱ በራሱ ሥልጡንና የነቃ ሕዝብ እንደሚፈልግ በቂ ማረጋገጫ አይደለም እያልከኝ ነው?፡፡ በአሁን ሰዓት እየተከራከርክ ያለኸው በመጥፎ መንፈስ ተጠምደህ ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ፡፡ የሌላ ዓለም ፍጡራኑን ለማጥመድ ይህንን የምርምር ዲዛይን የነደፍከው አንተ በመሆንህ እነዚያ ክፉ መንፈሶች አጥቅተውሃል ማለት ነው፡፡ የምታስበው በጤነኛ አእምሮህ እንዳልሆነ ተረድቼልሃለሁ፡፡

በዓለም ላይ በሰውና በሰው መካከል ያለው የበላይና የበታችነት መንፈስ ፈጣሪን ክፉኛ አስቀይሞታል፡፡ አንዱ አንደኛውን ለማጥፋት የሚገምደው የተንኮል ገመድ መንግሥታት በሚመሩት ሕዝባቸው ላይ የሚፈጽሙት የበላይነትና የእኔ አውቅልሃለሁ አምባገነንነት መንፈስ አምላክን አስከፍቶታል፡፡ ከሚመሩት ሕዝብ የተሻሉ ሆነው ሳይሆን ተጸንሰው የተወለዱት በእነዚህ መንፈሶች በመሆናቸው ነው የሚጨክኑት፡፡ ምርምራችንን በምንጀምርበት ወቅት የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳለበት ትናገር እንደ ነበር አስታውሳለሁ፡፡ በሁሉም ሥራችን ውስጥ ድካሙ የኛ ቢሆንም የእሱ የጥበብ እጅ አሻራ አርፎበታል በማለት ትናገር ነበር፡፡ ፍጡሮችን መቋቋም የሚችል ትውልድ ለመፍጠር የነበረህ ሕልም ቀላል የሚባል አልነበረም፡፡

ወደ ራስህ ተመለስና እንደ ቀደመው ለማሰብ ሞክር፡፡ በምንኖርበት ዓለም ገና ያልተመለሱ ብዙ ጥያቄዎች አሉ፡፡ ፈጣሪ አልፈቀደላችሁም የምትለው ከልብህ ከሆነ በእውነት በነዚህ ተንኮለኞች ተመርዞና ተቃውሶ አእምሮህ ተዛብቷል ማለት ነው፡፡ አንዱ በአንደኛው ተመቅኝቶና ቀንቶ ተንኮልን የማያስብ ትውልድን ለውጦ ከሌሎች ዓለማት ፍጡራን ጋር በመግባባትና በመዛመድ የሚኖር ሕዝብ መፈጠር አምላክን የሚያስቀይም አይደለም፡፡ በፍራቻና በጥርጣሬ ሳይሆን በፍቅርና በመተባበር በፕላኔቶች ላይ ከነዚህ ፍጡራን ጋር እንዴት መንሸራሸር እንደሚቻል በነበረህ ንድፍ ላይ እንዳስቀመጥከው አስታውስ፡፡ የመነሻውን ንድፈ ሃሳብ የወሰድነው ከአንተ ነው፡፡ በእምነት መጋረጃ ራሳቸውን ደብቀው ከፈጣሪ ተሹመናል የሚሉ ገዥዎች የአስተሳሰብ ምህዋርክን አዙረው መንገድና አላማህን በማስለወጥ ወደ እዚህ ላኩህ፡፡ በእምነት ስም የገዥነት መደባቸውን እያስፋፉ ያሉ መጥፎዎች መሆናቸውን ዘንግተሃል፡፡





እንደ ወንጀለኛ እያደኑን ያሉት ወገኖች ለዓለም ሕዝብ ተጨንቀውና ለፈጣሪ ሥራም አስበው ሳይሆን በነዚህ መንፈሶች የተጸነሱ በመሆናቸው ነው፡፡ በነዚህ መንፈስ ተጠምደው አለዚያም ተጸንሰውና ተወልደው የነበሩ ፈርኦን፣ ሄሮድስና ሂትለርን የመሳሰሉ መሪዎች ዓለማችን እንድታስተናግድ እንደተፈረደባት ይታመናል፡፡ ጥንታውያን ባቢሎንም እንደዚሁ ነበሩ፡፡

አንበሳን ከሰው ጋር እያታገሉ ይዝናኑ የነበሩት መንግሥታት ጭምር አልፈዋል፡፡ እነሱ ሲያልፉም እውቀታቸው የፈጠረውን መሳሪያ በሕዝብ ላይ በመሞከር የሚዝናኑ ተፈጥረዋል፡፡ የተንኰል ጡጦአቸውን እያጠቡ ያሳደጓቸው የሌላ ዓለም ፍጡራን መሆናቸውን ማስረጃ መጥቀሱ የሚያስፈልገው አይመስለኝም፡፡ በፈጠሩላቸው የጦር መሳርያ ሕዝባቸውን በማስገደድ በነፃነት የመኖርና የመናገር መብቱን በመንፈግ እስትንፋሱን አፍነው ሲያሻቸውም የራሳቸውን የመግደል ሕግ አውጥተው ወንጀለኛ ብለው የሚረሽኑ ገዥዎችም የነዚሁ መጥፎ መንፈስ ውላጆች ናቸው ትል ነበር፡፡ ሕዝብ ከሕዝብነቱ የተረፈው ምን ነገር አለ? ጠኔውን በነሱ የጥጋብ ብስና ከማስታገስ የዘለለ በዜግነቱና በሰውነቱ ከቶ ምን ተረፈው? ጠኔን እያሸተተ ረሃብን እያገሳ ሲያዛጋ እየተመለከቱት ደልቶሃል፣ ተመችቶሃል እያሉ ይሳለቁበታል፡፡"

ዶክተሩ አቋረጣቸው፡፡

"እየተደረገ ያለው ለሕዝቦች የሚጠቅም ባለመሆኑ መፍትሔ የሚሰጥ አይመስለኝም፡፡ የፈጣሪን ሕግ የተከተለ ባለ መሆኑም የበለጠ ቁጣን ሊያስከትል ይችላል፡፡ ሊጠቅም ይችላል ብለን ብናስብም እንኳን በፍጹም ፈጣሪ አይቀበለውም፡፡ የፈጣሪን ቁጣ ሊያገነፍለው የሚችል ሥራ ይሆንና ይህችን ምድር የቁጣ መቅሰፍት ሊወርድበት ይችላል የሚል ስጋት አለኝ፡፡ እንደነገርኩህ ፈጣሪ ቢፈቅድ ኖሮ የሰው ልጅ ካልደረስንባቸው ፍጡራን እኩል የመጠቀ አእምሮ እንዲኖረው አድርጎ ለመፍጠር የከለከለው አልነበረም፡፡ ስላልፈቀደ አሁን ያለውን ያህል እውቀት ሰጥቶ ፈጥሮታል፡፡ እንዲያውቅ የተፈቀደው ይህንን ያህል ብቻ ስለሆነ ከዚህ በላይ ቢያውቅ የሚጐዳው ነው የሚሆነው፡፡ የሰው ልጅ አሁን ያለውን የተንኮል ጥበብ በሌብነት ሰርቆ የወሰደው ከሲኦል ግዛት ያስወረወረውና ከነበረው ክብሩ ያዋረደው ነው፡፡ የነበረውን እውቀት አይበቃኝም ብሎ ብዙ ሲመኝ አዳም ቅጣት ተቀብሏል፡፡ በአርማጌዶኑ ጦርነት ተሸንፎ ወደ እዚች ምድር ከተወረወረበት ጊዜ ጀምሮ የተንኮል ጥበብን እያስተማረ አሁን ላይ ደርሷል፡፡"

ፕሮፌሰሩ ትዕግሥቱ አልቋል በሚል እጃቸውን አወናጨፉ፡፡

"እንዲህ ያለው የምኞች ዓይነት ጭዋታ በዚህ ስፍራ ተቀባይነት የለውም ብዬ ነግሬህ ነበር እኮ፡፡ በእውነቱ በጤናህ እንዳልሆነ ስለተረዳሁት ነው ትዕግሥት ሰጥቼ ያዳመጥኩህ፡፡ የምትለውን አድምጬ ሁሉም ነገርህ

ትርኪ ምርኪ ሆነብኝ:: ልክ እንደ ሕፃን ሆነሃል::" የምትለውና የምታስበው ያረጃና ያለፈበት የአጉል አስተሳሰብ ውጤት ነው:: ዓለማችን ለውጥ ያስፈልጋታል:: አዲስ ለውጥ መምጣት አለበት:: ሁሉም ነገር ዘመን ያለፈበት የታሪክ ድግግሞሽ ነው የሆነው:: ሁሉም ነገር ከተጣፈ ቡልኮ የተለየ አይደለም:: ለብዙ ሚሊዮን ዓመታት ብዙ የታሪክና የትውልድ ድግግሞሽን ዓለማችን ስታስተናግድ ለብዙዎች ስቃይ እና መከራ ሆና ቆይታለች:: የትናንቱ በዛሬው ሲያከትም የነገው በዛሬው እንደ አዲስ ይጀምራል:: አሁን ያለው ጥንት ነበረ:: ጥንት የነበረውም ወደ ፊት ይመጣል:: ይህች ዓለም ብርሃን ያስፈልጋታል:: እውቀታችን የፈቀደልንን ያህል አዲስ ነገር መፍጠር አለብን::

አዲሱ ፍጥረትም እንደማንኛቸውም ፍጡራን በብርሃን ፍጥነት ማሰብ የሚችል መሆን አለበት:: እንደሌላው ኘላኔት ፍጡራን በብርሃን ፍጥነት ለመብረርና ጥልቁን ለመመርመር የሚችል የሠለጠነና የመጠቀ አእምሮ ያለው ትውልድ ለዚህች ዓለም ያስፈልጋታል:: የሰው አእምሮ ያልደረሰባቸው ብዙ ነገሮች አሉ:: ከነዚያ ሥልጡን ፍጥረታት ጋር በእኩል አስተሳሰብ በመልካም ወዳጅነት መኖር እንዲጀምር የሚችልበትን ሁኔታ ለመፍጠር የምናደርገው ጥረታችን ይቀጥላል:: ሕዝብ ሁሉ መሰልጠን አለበት:: በሥልጡን መካከል መመቀኘት፣ መራብ፣ መጠማት የለም:: በስልጡን መካከል ጸብ፣ ክርክር፣ ስስትና ሙሰኝነት ቦታ አይኖራቸውም::

እነዚህ ነገሮች የደንቆሮዎች ግብር ናቸው:: ሁሉም ሥልጡን ከሆነ ማንም የማንንም አይመኝም:: የሰው ልጅ በእስከ ዛሬ ታሪኩ በነበረችው ትንሽ እውቀት አንዱ ሌላውን ለማጥፋት ጥሯል እንጂ የእኩልነት መንፈስን ለመፍጠር የሠራው የለም:: ኃይልና እውቀት እያላቸው በሰው ልጅ ላይ መጥፎ ነገር የማይሰሩ ፍጡራን እንዳሉ እናምናለን:: ሁሉን ያወቀ ማንንም አይጎዳም:: የሰው ልጅ ባለማወቁ የማይውጠውን እስከ መጉረስ ይደርስና ታንቆም ይሞታል:: ስግብግብነቱ ያለ ማወቁ የፈጠረበት እዳ ነው:: አዳምን ልትወቅስ ሞክረሃል::

ይህ እንደ ትልቅ ስህተት ነው የሚቆጠረው:: አዳም እጸበለስን ባይሠርቅ ኖሮ የሰው ልጅ ከዚህ በባሰ ድንቁርና ውስጥ እየኖረ ነበር ማለት ነው:: አዳም በስርቆት ወንጀል ቢቀጣም ለእኛ የእውቀት ብልጭታን ስለ ሰጠን እንደ አንድ ጀግና እንጂ እንደ ሌባ ማየት አይገባንም:: ሚስቱም ሄዋን እንደዚሁ ጀግና ነች::"

ዶክተሩን ፍንቅል ያለ ሳቅ ወስዶት ከወንበሩ ላይ ሲርገፈገፍ በነበረበት ሰዓት ኢንጂነሩ እየተቻኰለ ገብቶ ከፊታቸው ሲቆም ፕሮፌሰሩ ደነገጡ::

"ምን አዲስ ነገር አለ?" በመደነጋገር ሳይታወቃቸው ከተቀመጡበት ተነስተው የቆሙት በቅጽበት ነበር::





"አዲስ ነገር ተፈጥሯል ፕሮፌሰር::" እሱም በተቻኮለ ስሜት እየተጣደፈ መለሰ::

"ደሞ ምን ተፈጠረ?" በኃይል ተነፈሱ::

"ከሳተላይት የተቀበልኩት አዲስ ዜና ትንሽ የሚያስደነግጥ ይመስላል::"

ኢንጂነሩ ስጋቱን ያለ ምንም ማመንታት ገልጦ ለፕሮፌሰሩ ሲነግራቸው ትንንሽ ዓይኖቻቸው ወደ ውስጥ እየጠለቁ ተመልሰው በወንበራቸው ተቀመጡ::

"የሚያስደነግጥ አልከኝ? እስኪ ግልጽ አድርገው::" ወደ ውስጥ ጠልቀው የገቡ ዓይኖቻቸውን ለመክፈት ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም::

"ኢንተርፖል ከኢትዮጵያ መንግሥት የጸጥታ ሠራተኞች ጋር በመተባበር መግለጫ አውጥቷል:: መግለጫው በምስል የተደገፈ የአንድ ሕንፃን አካል ያሳየ ነው:: ምስሉ ያሳየው የሕንፃው አካል በትክክል የት እንደሚገኝ ባያስረዳም ከተለያዩ አገራት ወደ ኢትዮጵያ ገብተው የት እንደ ደረሱ ሳይታወቅ የጠፉት ዜጎች በዚያ ሕንፃ ውስጥ ባልታወቁ ኃይሎች ታግተው እንደሚገኙ የደረሰበት መሆኑን ነው መግለጫው ያብራራው::"

ኢንጂነሩ ተናግሮ ሲጨርስ በኃይል በመተንፈስ ጭንቀቱን ለማቅለል ሞከረ::

"አልገባኝም" አሉ ፕሮፌሰሩ "ይህ ሁኔታ በትክክል እየገባኝ አይደለም:: እስኪ እንደገና ረጋ በልና ልታስረዳኝ ሞክር::"

አልገባኝም ይበሉት እንጂ በትክክል እንዳልገባቸው ያውቃሉ::

"ሕንፃውን በምስሉ ቢያሳይም ያለበትን ቦታ መግለጽ አልቻለም:: እንደ ገባኝ ከሆነ ሕንፃው ያለበትን ቦታ ለማወቅ በራሱ ገና ብዙ መሥራትን ይጠይቃቸዋል ብዬ እገምታለሁ:: እንደሚታወቀው የሳተላይት መረጃን ለመተርጐምና በትክክል ለመረዳት የራሱ የሆነ ሙያዊ ባሕርይ የሚጠይቅ ነው:: ምስሉ የሚሰጣቸው መረጃዎች ውስብስብና ለመመልከትም ከእይታ የፈጠኑ በመሆናቸው እነዚያን ምስሎች በትክክል ለመተርጐም የሚችል የራሳቸው ባለሙያ ሊኖራቸው ቢችልም እንኳን ጊዜ ሊወስድ ይችላል ማለቴ ነው::"

"ልክ ነህ" አሉ ፕሮፌሰሩ "ሕንፃው ያለበትን ቦታ በትክክል ስለማያውቁት በሙያው የሰለጠነ ባለሙያ እስከሚያገኙ ድረስ ጊዜ የሚወስድ ነው:: ኢንተርፖል የቱንም ያህል ቢለፋ ቦታውን ደርሶበት ወደ ህንፃው በቀላሉ መድረስ አይችልም::"

ፕሮፌሰሩ ከተቀመጡበት ተነስተው ወደ ምርምር ክፍሉ ሲሄዱ ዶክተሩም ተከትሏቸው ገባና ዲዛይኑን እያገላበጠ ሲመለከት ለሁለተኛ ጊዜ ሳቅ ፈነቀለው::

"ምነው ዶክተር?" መነጽራቸውን እያስተካከሉ ጠየቁት::

"ጭራ አብቅላችሁለታል" አለ ትንፋሹ በሳቅ ኃይል እየተቆራረጠበት::

"ትክክል ነህ:: ዲዛይኑን ከአንተ የቀድሞ ዲዛይን የለወጥነው በጭራው ብቻ ነው::"

"ለምን ጭራ ማብቀል አስፈለጋችሁ? ምን ዓይነት አስቀያሚ ፍጡር ነው እየፈጠራችሁ ያላችሁት? ልቀመጥስ ቢል እንዴት ይቀመጣል:: ልብሱንስ ቢሆን እንዴት አድርጎ ሊለብስ ነው?" ውስጡን የሳቅ ሳግ እየተናነቀው ችግሮቹን ጠየቃቸው::

"እንደ ውሻ ጎንበስ ማለት ይችላል:: ልብሱንም ቢሆን ሰፊው አድርጎ የጭራውን መውጫ ይተውለታል::" በዚህን ጊዜ በሕይወቱ ስቆት የማያውቀውን ያህል ሳቅ ሳቀ:: ብቻውን አልነበረም ለመጀመሪያ ጊዜ ፕሮፌሰሩም አብረውት ሳቁ:: እሳቸውን ተከትለው በዚያ ክፍል የነበሩት በሙሉ ሳቁ...::

"አስቀያሚ ፍጥረት ነው የምትፈጥሩት::" አለ ዶክተሩ በድጋሚ::

"ትክክል ነህ ጭራው ትንሽ ሳያስጠላ አይቀርም::" አለ እስራኤላዊው::

"ለምንድን ነው ይህንን ያደረጋችሁት?" አለ ዶክተሩ::

ሁሉም ስለሳቁ ክፍሉ በሳቅ ማዕበል የተናጋ መሰለና ቆየ::

"ለኩራት እንዲያመቸው ብለን ነው:: እየሀ ጭራ ለኩራት ይጠቅማል:: መኩራት ቢፈልግ ጭራውን እያቆመ እንደ ወደቴ ዝንጀሮ ለመቴነን ይረዳዋል::" አለ አሜሪካዊው::

"እንግዲያውማ እየፈጠራችሁ ያላችሁት ሰውን ሳይሆን ዝንጀሮን ነው::" በምርምር ክፍሉ የነበረው ሳቅ በሌላ ክፍል ያሉትንም በመጥራቱ ተሰባስበው በመሳቅ ላይ እያሉ ሌላ መርዶ መጣላቸው::

ኢንጂነሩ ባልተጠበቀ ሁኔታ ስለገባ የሁሉም የሞቀ ቀልድ አዘል ሳቅ ተቋረጠና የፕሮፌሰሩ እይታ ወደሱ ሆነ:: በደቂቃዎች ልዩነት ነበር የተመለሰው::

"ምን ተፈጠረ?" አሉት በማይሰማ ድምጽ::

በሕንፃው ውስጥ በአሉት ሠራተኞቻችን መካከል መከፋፈል ተፈጥሮአል:: የተወሰኑት ኃብት በማሸሽ ላይ ናቸው:: አለ ኢንጂነሩ::

"እኮ እንዴት? ስለምን ኃብት ነው የምትነግረን?" አሉት ፕሮፌሰሩ::

"ሁሉም የየድርሻቸውን ይዘው ለመበታተን በመጣደፍ ላይ ናቸው::"

"እንዴት አወቅህ?" በጥርጣሬ ተመለከቱት::

"ኢንተርፖል ደርሶበታል::"

"በዜናው ሰምተኸዋል ማለት ነው?" ፊታቸውን የበለጠ ሸበሸበው::

"የተቀበልኩት መረጃ በዚህ ዙሪያ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥቷል::"

"እስቲ በዝርዝር አስረዳን?" አሉት::

"ስምኦን የተባለው የሠራተኞቻችን መሪ ለአሜሪካዊው ወርቅ በተለየ





ቅርጽ ሲያሠራና ወደ ውጭ ሲያወጣ መሆኑን ኢንተርፖል ደርሶበታል::"

ፕሮፌሰሩ በረጅሙ ተንፍሰው ግንባራቸውን ከጠረጴዛው ላይ ሲደፉ ሲመለከት ዶክተር ሪቻርድ ኀዘን ተሰማውና:: ራሱን ነቀነቀ::